# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የንጉሰ ነገሥቱ ቤት ዘረፋ፣ ጥቁር ኮት ለባሾች፣ ሚቼ ገኸ

በመጨረሻው ምዕራፍ በጣም ወሳኝ ሁኔታዎች ከተዘገቡ በኋላ፣ ወታደሮች ከየሬጅመንታቸው ተበትነው ለሁለት ወይም ለሶስት በመሆን፣ የሚዘረፍ ንብረት ለማግኘት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ጀመሩ:: ብልጠት በተሞላበት ሁኔታ በነጠላ ወይም በቡድን በመሆን እያንደንዱን ቤት መበርበር፣ የቤት ዕቃዎችን መገለባበጥ እናም በግድየለሽነት የቅዱሳን ምስሎችን ይሰባብሩ ነበር::

ወዲያ ወዲህ ሲሉ፣ ወደ ንጉሰ ነገሥቱ መኖሪያ መጡ:: ጠንካራ፣ እንደ በረት የመሰለ ግን ባለ ፎቅ ሆኖ የሳር ከፍከፍ ያለው ነበር:: በአጠገቡም፣ የንጉሡ ወጥቤት፣ የከብቶች በረት፣ መካዝኖች፣ የሴቶቹ መኖርያ ቤትና እራት ማዕዘን ያለው ትልቁ እስር ቤት ይገኛሉ::

በግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው ሴቶች አንድ ላይ ስብስብ ብለው ተገኙ:: ሴቶቹ ከንጉሰ ነገሥቱ ቤት የመጡ ናቸው:: ልብስ በለበሱና ባለበሱ ደንገጥሮቹ ተከባ፣ የሰሜንና የትግሬ ገኸ የነበሩት የደጃች ውቤ ልጅ፣ እቴጌዋ ጥሩ ወርቅ ውቤ አለች:: ሀያ ስድስት እመት ወይም ወደዛ ገደማ ዕድሜ የሚሆናት፣ ጠየም ያለች ከሁሉም በሳይ የምታምር ነች፤ ነገር ግን ገርጠት ብላ ከሳም ብላለች:: በተማረኩ ሰዎች፣ ስለ ባህሪዋ ወሬ ተዛምቶ ስለነበር፣ ወታደሮቹ እንዳዩዋት የሚገባትን ክብር እንዲሠጧት ነው ያደረጋቸው:: ለረዥም ጊዜ፣ ቴዎድሮስ ካልጠጡ በስተቀር፣ እቴጌዋ ለቴዎድሮስ እንደጠባቂ መልአክ ነበረች:: አንድ ወታደር አጥብቆ እንደ ገለፀው፣ እቴጌዋ እንደ "ደጉ መፅሐፍ" መካሪ ነበረች:: ጠባቂና ለሚፈልጉት ነገር በሙሉ የማታሰልስ፤ ግዳጅ ሲመጣ እንደ ባሏ ደፋርና ጀግና ነበረች:: ቴዎድሮስ ወደመቅደላ ለመምጣት ደብረታቦር ላይ ሆነው በሚዘጋጁበት ጊዜ እቴጌዋ መቅደላ ትኖር ነበር:: ሁለት ጊዜ የሚሆን፣ በዝነኛው[143] የሸዋው ንጉሰ ምኒሊክ ከአርባ ሺ ጦር ጋራ (ምናልባትም የተጋነነ ቁጥር ይሆናል) ቦታው ተከቦ ነበር፤ እለቆችና ሽማግሌዎቹ እጅ እንስጥ ብለው መክረው ነበር፤ ነገር ግን እቴጌዋ በየቦታው

---

[143] (ምን ይልክ) ምኒልክ መቅደላ በነበሩበት (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

እየተገኘች[144] ለንጉስ ነገሥት ባሏ የማትታክት ታማኝና አክባሪ ስለነበረች፣ የምኒልክ ከበባም ዋጋ ሳያገኝ፣ የከፉ መካሪዎች ሀሳብም ውድቅ ሆነ፡፡

ከደንገጥሮቹ ጋር እየተጫወተ የነበረው፣ የኢትዮጵያ ዙፋን አልጋ ወራሽ፣ ጠንካራና ብልህ የሆነ የሰምንት አመቱ ልዑል አለማየሁ ነበረ፡፡ የሁለቱን መኖር ሰር ሮበርት ናፒየር እንደሰማ፣ ካፒቴን ስፒዲ[145] (ባሻ ፈለቀ) ሀላፊነት ወስዶ የሚያስፈልጋቸው ነገር እንዲደረግላቸው እንዲያደርግ ትዛዝ ተሠጠው፡፡

ወታደሮች ወዲያና ወዲህ ሲዘዋወሩ፣ የተወሰኑት፣ ብዛት ያላቸው፣ አያንዳንዳቸው ሀያ ጋሎን የሚይዙ መአዛ ባለው ጠጅ የተሞሉ እንስራዎች ያገኛሉ፡፡ በደስታ በሚጮሁበት ጊዜ ሌሎች ሃምሳ የሚሆኑት የተገኘውን ጠጅ ለመጠጣት ተቀላቀሏቸው፡፡

በመቅደላ፣ በሁሉም ቦታዎች ላይ፣ የተለያዩ የወታደሮች የግርግር ቡድኖች በአይነት ተሰማርተውበታል፡፡ ግድየሌላቸው፣ ንብረት ፈላጊዎች፣ ሰካራሞች፣ ሞራላቸው የወደቀ፣ እዛኞች፣ ስነ ሥርአት የያዙ፣ አላማ የሌላቸውና፣ የእስረኛ ቡድኖች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁሉንም በዝርዝር ለመግለፅ አድካሚ ስለሚሆን፣ ከነሱ ውስጥ መገለፅ የሚገባቸውን ነካ ነካ አደርጋለሁ፡፡

የጠጪዎቹ ወይም የሰካራሞቹ ቡድን በንጉሡ አዳራሽ ተሰብሰበዋል፣ ንጉሡ ለራሳቸውም ሆነ ለሴቶቹ ያዘጋጁትን በርከት ያለ መጠጥ ለመቅዳት ነው፡፡ ብዛት ያላቸው እንደ ብራንዲ ኮሰተር ያለ ምርጥ አረቄ የያዙ እንስራዎች ተገኙ፤ እናም አረቄ በመቅመስ የሚታወቁ ሰዎች በጉጉት እያነሱ መቅመስ ጀመሩ፡፡ እየደጋገሙ ቀመሱ፣ እናም እንደሚጠበቀው በብዛት የጠጡት አረቄ ውጤት መታየት ሲጀምር ጊዜም አልወሰደም፡፡ ነገር ግን ከሚገባው በላይም አልነበረም፤ ምክንያቱም ጥብቅ የሆነ የእንግሊዝ ሠራዊት ህግ አለ፤ ሰክሮ የተገኘ ሰው ከባድ ቅጣት ስለሚያስቀጣም ነበር፡፡

ሌላው የወታደሮቹ ቡድን ደግሞ ወደ ንጉሡ ቤተመንግስት አዳራሽ ዘለው በመግባት በየቦታው ተበተነው የነበሩ ቁጥራቸው የበዛ ዕቃዎችና ንብረቶች ወሰዱ፡፡ ያገኙትንም አንድ ባንድ እያነሱ ከተመለከቱ በኋላ፣ ወይ ወደ ኪሳቸው ያስገባሉ አለዚያም ይወረውራሉ፡፡ የወረወሩትን ደግሞ ሌላው ተከትሎ እንደነሱ መርምሮ ወይ ወደ ኪስ አለዚያም መልሶ ይወረውረዋል፡፡ ከዚያ ሁሉ በጣም ትንሽ ነው ወታደሮቹ መያዝ የሚችሉት፤ ምክንያቱም

---

144 እቴጌዋ ለባሏ ስትል (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

145 በመቅደላ፣ ቴዎድሮስ፣ የባሻ ፈለቀን ስም ሲሰሙ በጣም እንደተናደዱ ተዘግቧል፡፡

ሲመለሱ ከባድ ሻንጣዎች በጀርባቸው ተሸክመው በሙቶ የሚቆጠሩ ማይሎች መጓዝ ግዴታቸው ነበር፡፡



*ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቃ)* ከልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር
ስፒዲ የያዘው የፊታውራሪ ገብርዬን ጋሻ፣ የለበሰውም የገብርዬን ለምድ ነው

ከቤተመንግስቱ ትይዩ የመቅደላ እስር ቤት አለ፤ በጣም ጠንካራ ድር ፎቅ ቤት ሆኖ ከውስጡ ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡ በጠጡት አረቄ ብርታት የተሰማቸው ወታደሮች በፍጥነት እየዘለሉ ወደ በሮቹ ሄዱና ሰባበሯቸው፡፡ እየጠለቀ ያለው የፀሀይ ጮራ ወደ ውስጥ መግባት ሲጀምር፣ አሰቃቂ የሆ ከፍል ተጋለጠ፡፡

ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ላይ ያልዋለው ከፍል በተወላጆቹ እስረኞ ተጨናንቆ ነበር፡፡ አንዳንዶች በየግዛቶቹ ትልቅ ማዕረግ የነበራቸው ናቸው፡፡

ሲመለሱ ከባድ ሻንጣዎች በጀርባቸው ተሸክመው በሞቶ የሚቆጠሩ ማይሎች መጓዝ ግዴታቸው ነበር፡፡



*ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቃ) ከልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር*

ስፒዲ የያዘው የፊታውራሪ ገብርዬን ጋሻ፣ የለበሰውም የገብርዬን ለምድ ነው

ከቤተመንግስቱ ትይዩ የመቅደላ እስር ቤት አለ፤ በጣም ጠንካራ ድርብ ፎቅ ቤት ሆኖ ከውስጡ ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡ በጠጡት አረቄ ብርታት የተሰማቸው ወታደሮች በፍጥነት እየዘለሉ ወደ በሮቹ ሄዱና ሰባበሯቸው፡፡ እየጠለቀ ያለው የፀሀይ ጮራ ወደ ውስጥ መግባት ሲጀምር፣ አሰቃቂ የሆነ ክፍል ተጋለጠ፡፡

ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ላይ ያልዋለው ክፍል በተወላጆቹ እስረኞች ተጨናንቆ ነበር፡፡ አንዳንዶች በየግዛቶቹ ትልቅ ማዕረግ የነበራቸው ናቸው፡፡

ልዑሎች፣ ደጃዝማቾች፣ ገበሬዎች አንድ ላይ ሆነው በመደናገጥ ቆመዋል፤ በእግር ብረት እንደታሰሩ ናቸው[146]:: ለትንሽም ጊዜ ቢሆን በመደናገጥ፣ ከእስረኞቹ ባላነሰ ሁኔታ ግራ በመጋባት ወታደሮቹ ሁኔታውን ተመለከቱ:: በእግር ብረት የታሰሩ እግሮችን ሲያዩ፣ በርህራሄ፣ ድምፅ በሌለው ጥሪ ወደ ግዴታቸው እንዲመለሱ ሆነ:: በተቻለ ፍጥነት፣ ወታደሮቹ የእግር ብረቶችን እየሰባበሩ መፍታት ጀመሩ:: በሙሉ ልብ ምስጋና፣ የታሰሩት ወደ ውጭ ወደ ፀሀይ መውጣት ጀመሩ፤ እንደገና ነፃነት!

ብዙዎቹ በጣም ደካማ ስለነበሩ መቆም አልቻሉም:: ለብዙ ቀናቶች በዚህ ቀፋፊ እስር ቤት በሚያስፈራ ሁኔታ ተሸማቀው፣ በአጉል ተስፋ ያ ቀን እንዲያልፍ በናፍቆት ይጠባበቁ ነበር፤ ነፃ የሚሆኑበት ትልቅ ቀን ይመጣል ብለው ጠብቀዋል:: እስር ቤት ጠባቂዎች እርስ በርስ ሲያወሩ ስለተሰማ ጠቀም ተደርገዋል:: የእስር ቤት ዘበኞቹ ስለ እንግሊዘ ሀይል ምንም ዕውቀቱ የላቸውም ስለዚህ ስለውጤቱ እርግጠኛ አልነበሩም፤ ያም ሆነ ይህ የማይረቡ ሀሜታዎች እንደሚወሩት ሁሉ እነሱም ስለጦርነቱ ያወሩ ነበር:: ደረጃ ሳይመርጡ፣ ሁሉም እስረኞች እየቀረቡ የወታደሮቹን እጆች ሳሙ::

ግን፣ ምስጋናን በደንብ መግለፅ ይቻላል ወይ? ከእነዚህ፣ ፀጥ ብሎ፣ ግን እጅ መሳም የመሰለን ነገር ጋር፣ እንዴት ያለ ቃል ነው የሚስተካከለው? ደስተኞቹ ሰዎች በተቻላቸው መጠን በየራሳቸውን መንገድ ሄዱ፤ ንፁህ አየር በተነፈሱም ቁጥር ጉልበታቸው እየበረታ ነበር የሚሄደው:: እንደ ባህላቸው፣ ደስታ በሚሆንበት ጊዜ እንደሚደረገው፣ አጨበጨቡ፤ እንኳን ደህና ወጣችሁ በሚል እንደበትም ተናገሩ፤ ከዚያም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነፃ ላወጧቸው ፈረንጆች እልልታ እሰሙ::

በመካዝኑ ተገኝቶ የነበረ ምግብ ለሰዎቹ ከተከፋፈለ በኋላ ከግቢው እንዲወጡ ተደረገ::

ይህ ትዕይንት የተከናወነው በቤተመንግስቱ ነው:: በአምባው በሌላ ቦታ ግን፣ ሌሎች ድርጊቶች ታይተዋል:: እንደዚህኛው ቀና ባይሆኑም፣ ስሜት የሚቀሰቅሱ ነበሩ:: የተለያዩ ማለቂያ የሌላቸው የመኖሪያ ሰፍራዎች ይታያሉ፤ ከሀር የተሰሩ፣ ከሸራም የተሰሩ ድንኳኖች፣ የኩርዶች የመሰሉ መኖሪያ ቦታዎች፣ መጠለያዎችና የመሳሰሉት ነበሩ:: በነዚህ ቦታዎች፣ በያንዳንዳቸው፣ ወንዶች ሰብሰብ ብለው አስተያዩት ይሰጣሉ፤ ሀሜታም፣ ትንተናዎች፣ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ወይም ደግሞ ያለቅሳሉ፤ ብቻ ማንኛውም የታያቸውን ነገር ያደርጋሉ:: እየተጠጋሁ ስሄድም፣ ያየሁት ነገር ቁጥጥር ያጣ መደናገርና

---

[146] እንደ ፕላውደን አገላለፅ፣ (በተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ ይመልከቱ)

ጩኸት ሳይሆን ያልታሰብ ውካታና ግርግር ነበር፤ ይህም የሆነው የኩርድ ድንኳኖች አካባቢ ነበር፤ በኋላ እንደተረዳሁት እና እንዳሰደነቀኝም እነዚህ ድንኳኖች ለካ የንብረት መጠበቂያ ነበሩ፡፡ መሬቱ በሙሉ፣ በየቦታው በወደቁ ውድ በሆኑ ዕቃዎች ተሞልቷል፡፡ ከነዚህ ንብረቶች የሚንፀባረቅ የሚብረቀረቅ ብርሃን ይታያል፡፡

በዊንድሶር ቤተ መንግስት ያሉ ውድ ንብረቶች ተሰብስበው፣ ከፋይ ላይ፣ አንድ ላይ ቢደረደሩ እንኳን እዚህ ቦታ የታየውን የውድ ንብረቶች ነፀብራቅ አይበልጡም፡፡ እነዚህ ብልጭልጭ ያሉ በቶን የሚቆጠሩ ንብረቶች ወርቅ ከሆኑ፣ የእንግሊዝ መንግስት ለዘመቻው ስላወጣው ወጭም ያን ያህል ባልተጨነቀ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ አንድ የሚያብረቀርቅ ከበድ ያለ የሻማ ማብሪያ እንስቼ በእትኩሮት ሰመለከት፣ ዕቃው ዋጋ የሌለው መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ምንም እንኳን ብዙዎቹ ውድ ከሆነ ብረት ቢሰሩም፣ አብዛኛዎቹ ወርቅ ቅብ ብቻ ነው የነበሩት፡፡

በነዚህ ዋጋ በሌላቸው ንብረቶች ላይ ሰዎች ይጨቃጨቁና ይጋጩም ነበር፡፡ ከነዚህ መካከል ደግሞ፣ ጎላ ብለው፣ እስከፊ በሆነ ከፍ ባለ ድምፅ የሚጮሁና የለበሱት ኮት እንደጅራት የወረደው ከፍል በነፋሱ የሚግለበለበው ጥቁር ኮት የለበሱ ሰዎች ነበሩ፡፡ እነሱም በሀር የተሰሩ ድንኳኖችን ለመጠቅለል እየታገሉ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች፣ ወራዳ የሆነ ባህሪ ባያሳዩና በሚሰቀጥጥ ድምፃቸው የጉብጋባነት ስሜት ባያንፀባርቁ ኖሮ፣ ለእድሜ ልክ ሰማቸውንም ባልጠቀሰኩ ነበር፡፡ እነዚህ ጥቁር ኮት የለበሱ እዋቂ ሰዎች፣ ለሰሙ እሃ፣ ፊላንትሮፒስት ተብየዎች፣ ሁሉም ባይሆኑ እብዛኞቹ እሰረኞቹ ነበሩ፡፡ ጥቂቶቹ የብሪታኒያ ዜጎች ሲሆኑ፣ ሶስት ሚሲዮናውያን፣ ፕራሻን፣ ጀርመን እና የሩሲያ መካኒኮች ነበሩ፡፡ እብዛኞቹ እነዚህ ሰዎች ወታደሮቹ ከመድረሳቸው በፊት ብዛት ያለውን የተዘረፈ ንብረት በእጃቸው አድርገው ነበር፡፡ ከእግራቸው ሰር ተከምሮ ይታይም ነበር፤ ሌላው ሰወር ያለው ደግሞ በጥቁር ኮታቸው ተሸፍኖ ነበር፡፡ እንደተባለው ከሆነ፣ ከእነዚህ የተረገሙ ሰዎች አንደኛው፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ቀርቶ የዲያብሎስ ሰይጣናዊ እይን እንኳን ፍርሃት የሌለበት፣ የተቀደሱትን የእቡነ ሰላማን የሪሳ ሳጥን በድፍረት በመክፈት፣ የእስከሬኑ እንገት ላይ የነበረውን ብዙ ሺ ዶላር የሚያወጣ የአልማዝ መስቀል ከአንገታቸው በጥሶ ወሰዷል፡፡

የነዚህ ውድ ንብረቶች ዜና በመቶዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ሰዎችን ወደቦታው እንዲመጡ አድርጓል፡፡ ጀኔራል ናፒየር፣ ስታቨሊ፣ ስናይደር፣ ዊልቢ ሳይቀር ከረዳቶቻቸው ጋር ለማየት መጡ፤ እነዚህ ሰዎችና የጋዜጠኞች ቡድን አባሎች፣ ለጋዜጠኞች ቡድን ከብርም ሲባል፣ ሌሎቹን ጀግኖች

ካባለጋቸው ባህሪ ተለይተው፣ አንድ ዕቃ እንኳን እንሰተው ወደ ኪሳቸው አልጨመሩም፡፡


በአሃዝ ለመግለፅ ያህል፣ በየቦታው ተብትነው ከነበሩት ንብረቶች፣ አንድ አሰረኛው እንኳ ለመሰብሰብ ሊደከምባቸው የሚገባ ንብረቶችም አልነበሩም፡፡ ከድንኳኖች በአንደኛው፣ በተለያዩ ቀለሞች የነገደ ይሁዳ አንበሳ ምሰል የተጠለፈበት የንጉሰ ነገሥቱ አርማ ተገኘ፡፡ በሌላው ድንኳን፣ የንጉሰ ነገሥቱ ተመሳሳይ የይሁዳ አንበሳ ምስል የተቀረፀበት ማህተም ተገኘ፡፡



*የአፄ ቴዎድሮሰ ማህተም*


ከንፁህ ወርቅ የተሠራ ጽዋ በሚሰተር ሆልምስ እጅ ገብቷል፡፡ ላዩ ላይ በጥንታዊ ኢትዮጲክ ቋንቋ የሚከተለው ፅሁፍ ነበረበት፡፡

*የንግስት ብርሃን ሞገስ ልጅ*
*የንጉሰ አድያም ሰገድ ኢያሱ ጽዋ*
*ጎንደር ለቁስቋም ገዳም የተሠጠ*
*ነብስና ስጋዬ ንፁህ ይሁን*
*15ኛው ክፍለ ዘመን*




*በመቅደላ የንጉሡ ቤት ዕይታ*

የ300 መቶ አመት እድሜ ያለው የአቡኑ ቆብ፣ ከንፁህ ወርቅ የተሰራ ሲሆን፣ ምናልባትም ክብደቱ ከስድስት እስከ ሰባት ፓውንድ ይሆናል፤ ከዚህ በተጨማሪ አራት ዘውዶች፣ ከነዚህ ሁለቱ በዕውቅ በጥራት የተሰሩ ግምታቸው ብዙ ገንዘብ የሚሆን ከፍተኛ ዋጋ ስላላቸው በብሪታንያ ሙዚየም



የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ



ከወርቅ የተሠራው የአቡኑ ዘውድ
(ምንጭ ዋቢ መፅሐፍት ተ.ቁ. 16)

መቀመጥ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዕንቁ ያጌጠ ትንሽ የመፃፊያ ጠረጴዛም ተገኘ፤ በውስጡም ከአውሮፓውያን መንግሰታትና ሰዎች ምስጋና ያለባቸው ደብደቤዎች ሞልተውት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የተለያዩ የሚያማምሩ ጋሻዎች ነበሩ፡፡

ቁጥር የሌላቸው፣ ከወርቅ፣ ከብርና ከነሓስ የተሰሩ መስቀሎች፣ በጣም ተውበው የተሠሩ የዕጣን ማጨሻዎች፣ ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ምንቸቶች፣ ጀበናዎች፣ ሰሀኖች፣ የተለያዩ ኩባያዎች፣ ውድ ከሆነ ብረት ተቀርጸው የተሠሩ መጠጫዎች፣ የቦሄሚያ ጠርሙሶች (ብርጭቆዎች)፣ ከሰቨረስ የመጡ ሸክላ ሰሀኖች፣ የስታፈርድሻየር የሸክላ ሰራዎች፣ ሻምፓኝ፣ በርገንዲ ወይን፣ የግሪክ፣ የስፔይንና የኢየሩሳሌም ወይን፣ የዮርዳኖስ ውሀ የያዙ ጠርሙሶች፣ አረቂና ጠጅ የያዙ ማለሮዎች፣ ጌጣጌጦች የሞሉባቸው ሳጥኖች፣ የወይን ጠጅ፣ ሮዝ፣ ነጭ ሌላም ቀለሞች ያላቸው ከሀር የተሰሩ ድንኳኖች፤ የፔርሺያ፣ የኡሻክ፣ በሩሳ ኪደርሚኒሰተር እና የሊዮን ምንጣፎች፤ ከአንበሳ ፀጉር የተሰሩ ካባዎች፤ ከአንበሳ፣ ከአነርና ከተኩላ ቆዳ የተሰሩ ቆቦች፤ በሚያስደንቅ ሁኔታ በወርቅና[147] በብር አጊጠው የተሠሩ ኮርቻዎች፤ ብዛት ያላቸው በብር የተሰሩ ጋሻዎች፤ ውበትና ብሩህ ቀለም ያላቸው በበጌምድርና በጎንደር ባለሙያተኞች ተውበው የተሠሩ ድባቦች፤ ሰይፎችና ጎራዴዎች፣ የተለያዩ ባለሰለት መሣሪያዎች፣ የፐርሺያ፣ የደማሰቆ እና የህንድ ጨቤዎች ከወይን ጠጅ ከፋይ ከተሰሩና በላያቸው ላይ የወርቅ ቁልፍ ያለባቸው አፎቶች ጋር፣ የንጉሣዊ የብራና ፅሁፎች ከምር፣ የተደረደሩ በአማርኛ የተፃፉ መፅሐፍ ቅዱሶች፣ የፀሎት መፃህፍቶች፣ ቁጥር ሰፍር የሌላቸው የፎቶ አልበሞች፣ በጠርሙስ ላይ የተሳሉ ምስሎችና የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና የጣልያን የአካባቢ እይታ ፎቶግራፎች፣ በጥበብ የተሠሩ ዴስኮችና ጠረጴዛዎች ነበሩ፡፡ ሰፋቱ እየጨመረ በሚሄድ ቦታ፣ በሺ የሚቆጠሩ እነዚህ ዕቃዎች በየቦታው ግራ በሚያጋባ ሁኔታ፣ በአለታማው አምባ፣ በዳገቱና በኮረብታዎች ወደ ካምፕ በሚወሰደው የሁለት ማይሎች ርቀት ባለው ቦታ ሁሉ ተንጠባጥበው እስኪገኙ ድረስ ተብተነዋል፡፡

ከዚህ ትዕይንት በኋላ፣ የቅርቡ የመቅደላ ጌታ እሰከሬን[148] በሸራ ቃሪዛ ላይ ወደተጋደሙበት ቦታ ወደ ሰሜን በር አመራሁ፡፡ በዚህም ደግሞ፣ ሌላ፣ መኮንኖችና ሲቪሊያኖች እርስ በርስ እየተጋፉ ያሉበት ግርግር ቡደን ነው

---

[147] አፄ ቴዎድሮስ ለራሳም ከሠጡት አንዱ ሥጦታ በወርቅ የተሠራ ኮርቻ ነበር፡፡

[148] ምርመራውን ያደረጉት (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

ያየሁት፡፡ እነሱም ደም የነካውን የቴዎድሮስ ቀሚሽ ቁራጭ ለማግኘት ያለማሰለስ እየታገሉ ነበር[149]፡፡

እስከሬኑን የሚጠብቅ ምንም ዘበኛ አልተመደበም፡፡ ትንሽ እንኳን ቢሆን ከብር ሳይሰጡ አስከሬኑ እርቃኑን ቀርቶ ነበር፡፡ በቃሬዛው ላይ እንደተጋደመ፣ ጨካኝ አእምሮ ላላቸው ሰዎች ሰድብና ሹፈት ተጋልጦ ነበር፡፡ ይህን ያዬ መኮንን፣ ለሰር ሮበርት ናፒየር ተናግሮ፣ ጄኔራሉም አስከሬኑ እንዲለብስና በነጋታው ለቀብር እንዲዘጋጅ ትዛዝ ሰጠ፡፡ [150]

ከዚህ ተነሰቼ በተመደቡበት ቦታ ሆነው እስከመጨረሻው ሰአት ድረሰ ለአለቃቸው ሲዋጉ የሞቱ የቴዎድሮሰ ታማኝ ተከታዮችን አስከሬን ለመርመር ሄድኩኝ፡፡ አለቃቸው፣ በደህናው ጊዜ ዙሪያቸውን ባሉ ሰዎች የመወደድ፣ የመከበር የመፈራትና ገናናት ባህሪ ነበራቸው፡፡ የሞቱት እዛገሮች፣ በየቦታው በተለያዬ እወዳደቅ ነበር የሚታዩት፤ ነገር ግን የተለየ ረጋ ያለ ገፅታ ይታይባቸው ነበር፡፡ ቁሰላቸው ብዛት ያለውና አሰቃቂም ነበር፡፡ ዋና እዛገሮች በቁጥር ሰባት ነበሩ[151]፤ እነሱም እስከመጨረሻው ድረሰ በቆራጥነት ከተከላከሉት ከምሽጉ ማማ አጠገብ አንድ ላይ ነበር የወደቁት፡፡ የለበሱት የሀር ልብሰና የደረቡት ያጌጠ ለምድ በደማቸው ርሷል፤ ዙሪያውን ያለው ድንጋይ እንኳን ሳይቀር ላደረጉት ግብግብ ምሰክርነት በተመሳሳይ ሁኔታ በደም ተረጭቷል፡፡

ከታች ማማውን ከበብ አድርጎ በተሠራው የካብ መከላከያ ደርዘን የሚሆኑ ተዋጊዎች ወድቀዋል፤ እንጎላቸው ተከፍቶ፣ እግርና እጃቸው ተገንጥሎ ሌሎችም እሰፈሪ የሆነ ቁሰል ይታይባቸዋል፡፡ ከፍ ብሎ ባለው መከላከያ፣ እሰራ ሶሰት የሚሆኑ የወደቁ ተወላጆች እሉ፣ መቅደላ ውሰጡም፣ ተንጠባጥበው ምናልባትም ቁጥራቸው ወደ ደርዘን የሚሆኑ አሉ፡፡

ወደ ምሽጉ መግቢያ መከላከያ ሆኖ የተሰራው አጥር እንደነገሩ የተገነባ ቢመሰልም፣ በደንብ እንደ አውሮፓና አሜሪካ ወታደራዊ መሀንዲሶች ሊሰሩት በሚችሉት ሁኔታ በደንብ ዕቅድ ያለው ነበር፡፡ ያም እንግዲህ ቴዎድሮስ በነበራቸው የግንባታ መሳሪያዎች ነው ሊሰራ የሚችለው፡፡ ወደ መከላከያው ቦታ ማለፊያው በሁለት እለቶች ስር ነው የሚያልፈው፤ እነዚህ እለቶች ደግሞ ከመግቢያው በኩል 15 ጫማዎችና ከመከላከያው በላይ 30 ጫማዎች ከፍታ ነበራቸው፡፡

---

149 (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

150 የአፄ ቴዎድሮስ ቀብር ትዛዝ የተሠጠው (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

151 ቴዎድሮሰ በመጨረሻዎቹ ሰአታት፣ (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

መግቢያው ሰድስት ጫማዎች ከፍታ ሲኖረው በሁለት እንጨቶች ነበር የተሠራው፣ በላዩም ላይ፣ ከላይ ወደ ታች የሚወርዱ ሁለት ብረቶች፣ ሁለት በአግድሞሽና ወደ ጎን የሚሄዱ ማጠናከሪያዎች አሉበት:: ወደ ውስጥ የሚከፈት ሆኖ፣ ዳር እስከ ዳር በሚቀመጥ በአግዳሚ ጣውላ ነው የሚዘጋው:: ገለጥ ያለው ቦታ ላይ የሰምንት ጫማዎች ስፋት ነበረው:: በማለፊያው በውስጠኛው በኩል፣ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ ከድንጋይ የተሠሩ መሻገሪያዎች አሉ፣ በእያንዳንዱ የአለት ግድግዳ አናት ላይ ደግሞ ምሽጎች ተሠርተውባቸዋል::

በአጠቃላይ ሲታይ፣ በደንብ መከላከል የሚያስችል ቦታ ነበር፤ አንድ ባለ 12 ፓውንደር መድፍ ብቻ የማይታለፍ ሊያደርገው ይችል ነበር:: ነገር ግን ቴዎድሮስ መድፎቻቸውን ፋላና ሰላሴ ላይ ጠምደው አሮጌ ላይ ተሸነፉ:: መድፎችን ወደ መቅደላ ለማስመጣት ዘግይተው ነበር፤ ምክንያቱም ለሁለት ቀናት በውድ ወዳጃቸው በእርመናዊ ራሳም አማካኝነት የሰላም ድርድር እየተካሄደ ነበር:: መጨረሻ ሰላም የማይፈጠር መሆኑን ሲገነዘቡ በሶስተኛው ቀን መድፎችን ለማስወሰድ ጀምረው ነበር፣ ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት፣ ስፒዲና ሎች 3ኛው ፈረሰኛን እየመሩ ድንገት ሳያስቡ ደርሰውባቸዋል::

የሞቱት ሰዎች ቁጥር ከላይ በተለየዩ ሁኔታ እንደተገለፀው ወደ ሰልሳ ይደርሳል፤ የቆሰሉት ቁጥር ግን የዛን እጥፍ ያህል ነበር:: የብሪታኒያዎቹ ጉዳት ደግሞ አስራ ሰባት ቁስለኛ ሲሆን የሞተ የለም:: ምሽጉ ላይ፣ የከባድ መሳሪያ ድበደባው ከሁለት ሰአታት በላይ ነበር የተደረገው:: የሚገርመው በሰፍራው ከነበሩ ከ4ሺ ሰዎች መሀከል የንፁህ ሲቪሊያኖች ህይወት በከንቱ አልጠፋም::

በአሮጌ ውጊያ ከቆሰሉት መሀል ወደ መቶ የሚሆኑት በሰላምጌ ጎጆዎች ተጠልለው ነበር:: ከአንድ ወይም ከሁለት ቁስለኛ በላይ በማስጠለል ከሁለት አንዱ ቤት እንደሆስፒታል ነበር ያገለገሉት::

ወደምስራቅ በኩል፣ ከሰላምጌ በታች በነበሩት መንደሮች ሮኬቶች ጠቅላላ ጥፋት ነበር ያደረሱት:: አንድ አላማውን የሳተ ሮኬት በአንዱ በቀላሉ በአሳት በሚያያዝ ጎጆ አልፎ እሳት በማስነሳቱ ከዚያም ነፋሱ እያቀባበለ ሌሎቹን ጎጆዎች እንዲቃጠሉ በማድረጉ በአጭር ጊዜ መንደሩ እንዳለ አመድ ነው የሆነው::

የፈረንሳዩ ፕሮፌሰር ባርደል[152]፣ ከሌሎቹ አውሮፓውያን ተነጥሎ ወደ ካምፕ አልወረደም ነበር:: በትኩሳት ህመም ይሰቃይ ስለነበር አንደ ቅዠትም

152 ቴዎድሮስ ራሳምን የተቀበሉት (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

ጀምሮታል፡፡ ወደ ስላሴ ጠጋ ብሎ በሚገኝ ሰላምኄ ስፍራ፣ በአንድ ጎጆ ውስጥ በቀፋፊ ሽታና የምግብ ትርፍራፊ ተከቦ፣ በተባይ በተወረረ ምንጣፍ ተሸፍኖ ነው የተገኘው፡፡ ወዲያውኑ ወደወታደራዊ ሆስፒታል ተወስዶ ህክምና ከተደረገለት በኋላ ከአንድ ሳምንት የጠና ህመም ሊያገግም ችሏል፡፡

ይህ የገለጥኩት ነገር ሁሉ ሶስት ስአታት ነው የወሰደብኝ፡፡ ለሲቪሊያኖቹ አማራጭ ነበረን፤ መቅደላ ቆይቶ በአንድ ጎጆ ማታውን ማሳለፍ፣ አለዚያ ሁለት ማይሎች ርቀት፣ ከፋላ ግርጌ ወዳለው ካምፕ ማምራት ነበር፡፡ ብዙ ጎጆዎችን ከተመለከትን በኋላ፣ ወደ ካምፑ ለመሄድ ወሰን፡፡

ሰላምኄ ስንደርስ የካምፕ አጃቢዎች ጋረ ተገናኘን፡፡ ካምፕ ተከታዮችና የዚህ ገናና ጦርነት ዳዝ በዝግታ ወደ ላይ ወታደሮቹ ወደ ሰፈሩበት የመቅደላ አምባ ይጓዛል፡፡ በቅሎዎችና ፈረሶች፣ ቃሬዛና የሰው መሸከሚያውች የሚያባራ በማይመስል ሁኔታ ይጓዛሉ፡፡ ከሰላምኄ  በታች ዝሆኖችን ጀርባቸው ላይ ካለው ከከባድ ሸከማቸው ጋር አገኛናቸው፤ በጨለማው፣ ምትሀታዊ ምስል ይመስላሉ፡፡ በዚህ ሰላም ባለበት ምሽት ደግሞ፣ ለደተኞቹ ለኢንግላንድና ለህንድ ወታራዊ ማዕበል ደንታ ሳያሳዩ ወደ አሮጌ ሸለቆ ያመራሉ፡፡

ፋላን እንዳለፍን፣ ቁልቁለቱን በምን ግዴ ህይል መንደርደር ጀመርን፤ ያም ፋላና ሰላሴን በጥዋቱ ጥለው የወጡ የአቢሲኒያኖችን ካምፕ እስከምናይ ድረስ ነበር፡፡ ካምፑ በእሳት ደምቋል፡፡ ራቅ ብሎ በምስራቁ አድማስ በኩል ደግሞ ረዥም የእሳት መቀነት ይታያል፡፡ ያም ለተወላጆቹ ማስጠንቀቂያ ችቦ ነበር፡፡ በዚያ ሆነው አይናቸውን ያፈጠጡ አሮሞዎች በካምፓችን ውስጥ ስለሚታየው ሰፋ ያለ የእሳት ባህር በመገረም ሁኔታ ይመለከታሉ፡፡

የመጀመሪያው ውጊያ በተካሄደበት በአሮጌ ሜዳ ላይ የተተከለውን የአቢሲኒያኖች ካምፕ አልፈን ሄድን፡፡ ካምፑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻቸው ከተቀበሩበት ቦታ አጠገብ ነበር፡፡ የኛ ካምፕ፣ ከዚህ ግማሽ ማይል ርቀት ላይ ነበር፡፡ ካምፑን ስንቃረብ ሙሾና ለሞቱ ሰዎች የሚደረግ ለቅሶ ሰማን፡፡ በፈረሶቻችን ኮቴ ሰው ረግጠን የምንገድልበት አደጋ ባለበት ሁኔታ በውስጡ እያለፍን አያለ፣ ድንገት በረዶ የመሰሉ ነጫጭ ድንኳኖች በብዛት አየን፡፡ ብዛት ያላቸው ድንኳኖቹ ረጭ ባለ ፀጥታ ምድሩ ላይ ተተክለው ይታያሉ፡፡ በዚህ ባገኙት መጠለያ ተስንራፍተው፣ ድብን ያለ እንቅልፍ ውስጥ ሆነው፣ በህልማቸው፣ ያለምንም ጥርጥር፣ መቅደላ ሲወድቅ መህሪ እንግሊዞቹ ያሳዩትን ባህሪ በፀጋ እያመሰገኑ ነበር፡፡

# የምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች

***ቁጥር 143፣*** *(ምን ይልክ) ምኒልክ መቅደላ በነበሩበት ጊዜ በጣም ተወዳጅ ወጣት ሰው እንደነበሩ ነው የሚታወቀው:: ከአቡነ ሰላማ ጋርም የተለየ ወዳጅነት ነበራቸው:: ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ልጃቸውን አልጣሽን ድረውላቸው ነበር:: ከአሁኑ ሁኔታ ከሁለት አመት በፊት፣ በኦሮሞዋ ንግስት ወርቂት እርዳታ ከመቅደላ አምልጠው ነው የወጡት፤ አልጣሽንን ግን ይዘው አልሄዱም:: የምኒልክ ከመቅደላ ማምለጥ ዋነኛው ምክንያት፣ በቴዎድሮስ፣ ሸዋ ላይ ተሹመው የነበሩት ደጃች በዛብህ፣ ቴዎድሮስን ከድተው የሸዋ ንጉሥ ሲሆኑ ነው የሚባል ወሬ ሲሰሙ ነው:: ምናልባትም ምኒልክ ከመቅደላ ይልቅ አቡኑን የፈሩ ይመስላሉ:: በመቅደላ ሲያድጉም በአፄ ቴዎድሮስ እንደ ልጅ ነበር የተያዙት፤ ከራሳቸው ልጅ ከመሸሻ ቴዎድሮስ ጋር እኩል ነው ያደጉት:: ልጃቸውን ሲድሩላቸውም ወደፊት የምኒልክን ሁኔታ አስበው ይሆን? ምኒልክ መቅደላን ቢሞክሩም፣ የአፄ ቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ ሀዘን ተቀምጠዋል:: እንደ ጳውሎስ ኞኞ መፅሐፍ፣ የምኒልክ የመጨረሻ መሀላ፣ "ቴዎድሮስ ይሙት" ነበር::*

*ምኒልክ 30ሺ ጦር ይዘው ነበር መቅደላን ለመውሰድ ያሰቡት:: ሳያጠቁ ለምን ወደሸዋ እንደተመለሱ ግልፅ አይደለም:: የዚህን ዜና፣ ናፒየር በምርጫ ወርቄ በኩል አግኝቶ ነበር:: ምኒልክ ወደ መቅደላ ሲዘልቁ፣ ከመቅደላ ባላባት ከወርቂት ጋር ግንባርም ፈጥረው ነበር:: መቅደላ የነበሩ ባለሥልጣናት ቴዎድሮስ ቶሎ እንዲደርሱ ሲመኙ ሌሎቹ ደግሞ የምኒልክን መምጣት እንደተመኙ ተዘግቧል:: ከምኒልክ ጋር ሲመሳጠሩ ከነበሩት የቴዎድሮስ ባለሥልጣኖች ቢትወደድ ሀይሉ የሚባል ነበር፤ እሱም ቴዎድሮስ ሲመለሱ፣ መቅደላ ከመድረሳቸው በፊት አምልጦ ለናፒየር ስለመቅደላ መረጃ አቀብሏል:: ዋግሹም ጎበዜም ቢሆኑ ለአቡነ ሰላማ በላኩት ሚስጥራዊ ደብዳቤ፣ አቡኑ መቅደላ ላይ አመፅ ቢያስነሱ ጎበዜ መቅደላን ለማጥቃት ዝግጁ እንደነበሩ ነው::*

***ቁጥር 144፣*** *እቴጌዋ ለባሏ ሰትል ታማኝ ወታደሮችን ሰብስባ ጥሩ ቁርስ አብልታ፣ ጠጅ አጠጥታ፣ መቅደላ እንዲጠበቅ አድርጋለች:: ወጣቷ እቴጌ ጥሩ ወርቅ የእንግሊዞችን መምጣት ሰምታለች:: መቅደላ ላይ የነበሩ የተወሰኑ የቴዎድሮስ ሰዎች መቅደላን ለማስረከብ መደለታቸው እንደታወቀ፣ ልዑል አለማየሁን የቤተመንግስት አልባሳ፣ ፀጉሩንም በብዙ ፎቶዎች እንዳየነው አስላጭታ:: ደጋጎቹ ወደተሰበሰቡት ቦታ ወሰዳ፣ የአባትህ ተወካይ መሆንክን አሳያቸው፤ በመሀከላቸው ገብተህ ከተደለደለው ቦታ ላይ ኮርተህ ቁጭ በል በማለት መከራ፣ እሷ ግን፣ ሰብሰባ መግባት ለሴቶች ክልክል ስለሆነ፣ ከድንኳን ጀርባ አሾልካ ትመለከት ነበር:: የልጁን በተደላደለው የአባቱ ቦታ መቀመጥ ያዩ ሽማግሌዎች ተደናገጡ:: በጣም የገረማቸው ደግሞ፣ ጎበዙ የሚባለው የቴዎድሮስ አንበሳ ገባ ብሎ ከልጁ አጠገብ መቀመጡና፣ ከዚያም፣ ልዑሉ፣ አንበሳውን፣ ከአባቱ እንዳየው እጁን ጣል ሲያደርግበት ሲያዩ*

ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ በስብሰባው የነበሩት በሙሉ ለቴዎድሮስ ታማኝነታቸውን አረጋገጡ፡፡ ስብሰባው እንዳለቀ ግን፣ ለስብሰባው ያልመጡት ሰዎች፣ የሆነውን ሰለሰሙ፣ በፍርሃት እቴጌዋ ያለችበት ድረስ በመሄድ ለቴዎድሮስ ታማኝነታቸውን ሲምሉ ሲገዘቱ ነበር፡፡ እቴጌዋ በዚህ መልክም ይሆናል ኢድማውን የበተነችው፡፡ ከባሏ ጋር ብዙም ፍቅር እንዳልነበራቸው፣ በተለይም ቴዎድሮስን ትንቅ እንደነበር በተለያዩ ፅሁፎች ተገልጧል፡፡ ቴዎድሮስ በወታደራዊ ባህሪያቸው የንጉሳዊ ልብስ መልበስ የማይፈቅዱ ሆነው ሳለ፣ እቴጌዋ ግን ይህንን ትቃወም እንደነበረ ነው፡፡ ይባስ ብሎ፣ ቴዎድሮስ፣ ቁባታቸውን ወይዘሮ የተመኙን ከእቴጌዋ ጋር አንድትቆይ መቅደላ መላካቸው ነው፡፡

አቴጌ ጥሩወርቅ፣ የዘውድ ተሰፈኛው የደጃዝማች ውቤ ልጅ፣ መሆኗ መዘንጋት የለበትም፡፡ ከሌሎች መሳፍንቶች በላይ፣ አቡንን አባ ሰላማን በእጃቸው አድርገው ስለነበር፣ ለዙፋኑ የበለጠ ዕድል ነበራቸው፡፡ በአቡን ካልተቀቡ መንገሥም አይቻልም፡፡ የሆኖ ሆኖ ለባንልበተኛው ለቴዎድሮስ ማስረከብ ነበረባቸው፡፡ ቴዎድሮስ ውቤን ሲያሸንፉ፣ በውቤ ስር የነበረው የትግራይ ግዛት በሳቸው ስር ነው የሆነው፡፡ ደጃች ካሳ፣ ውቤን እንዲገብሩ ቢልኩባቸው፣ ውቤ አልገብርም በማለታቸው፣ ራሳቸውን አንደ ንጉሥ ዳዊት የሚቆጥሩት ቴዎድሮስ፣ ውቤን፣ "ጎልያድ" ጦርነት ላይ አንገናኛለን ማለታቸውም ይጠቀሳል፡፡ አንግዲህ እባቷንና ወንድሞቿን ያሸነፉና ያሰሩ ሰው ነው ያገባችው፡፡ ፍቅር ባይኖራትም፣ ለታማኝነቷ ጥርጣሬ አልነበረም፡፡ አሳዛኝ ሆኖ፣ እቴጌዋ፣ መቅደላ ከመያዙ በፊት የሳል ህመም ነበራት፡፡

ቴዎድሮስ ለልዑል አለማየሁ ያላቸው ፍቅር ይህ ነው አይባልም፡፡ ለአውሮፓውያኑ፣ መሸሻና አለማየሁን ወደ አውሮፓ ወስዳችሁ አስተምሩልኝ ብለው መናገራቸው ተዘግቧል፡፡ ይህም፣ አፄ ቴዎድሮስ መጨረሻቸውን በደንብ የተገነዘቡ ሰው እንደነበሩ ይጠቁማል፡፡

**ቁጥር 146፣** አንደ ፕላውደን አገላለፅ፣ ቴዎድሮስ ባላባቶቹን ለጊዜው አስረው ሥልጣናቸው ሲጠናከር ለመፍታት አስበው ነበር ይላል፡፡ ምናልባትም ይህ ሀሳባቸው ሊሆን ይችላል ለነዚህ ሰዎች በእስር ቤት በሕይወት ሊቆዩ ያስቻላቸው፡፡ ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው፣ ብዙዎቹ ባላባቶች ሲዋጉ በምርኮ የተያዙ፣ ወይንም ንጉሡን ሊከዱ ወይም አሴራችሁ ተብለው ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ገና በፍራቻ ሊከዱ ይችላሉ ተብለው ነው፡፡ ቴዎድሮስ፣ እነዚህን ሰዎች መግደልም ይችሉ ነበር፡፡ ከታዋቂ እስረኞች መካከል አንዱ ምኒልክ ነበሩ፡፡ አሳቸው ግን ከቴዎድሮስ የመጀመሪያ ልጅ፣ ከመሸሻ ካሳ ጋር እኩል ነው ያደጉት፡፡ ምኒልክን የሸዋ ባላባቶች ናቸው አሳልፈው የሰጡ፣ ከውጊያ በኋላ ቢሆንም፡፡ እንደሚባለው ከሆነ፣ ምኒልክ በተያዙ በማግሥቱ፣ ቴዎድሮስ፣ ያ ልጅ እንዴት አደረ ብለው ሲጠይቁ፣ በአግር ብረቱ ምክንያት ሲያለቅስ አደረ ተብሎ ሲነገራቸው፣ ከዚያን ቀን ጀምሮ በአግር ብረት እንዳይታሠሩ ሆነ፡፡ ቴዎድሮስ፣ እስረኞቻቸው እንዴት እንደሆኑ መጠየቅ ባህሪያቸው መሆኑን በተለይም ከአውሮፓውያን እስረኞች ጋር የተለዋወጧቸው መልክቶችና ደብዳቤዎች ያስረዳሉ፡፡

ንጉሡ ሰዎችን በእሥራት ብቻ ማቆየታቸው ከደግነት ጋር የተያየዘ ይመስላል፤ በርግጥ ለእስረኞቹ ግን የከፋ ነገር ነበር። ሆኖም እስረኞቹ ሌላውን አማራጭ ደግሞ ያስተዋሉ አይመስልም።

**ቁጥር 149፤** ቀደመው የቴዎድሮስ አስከሬን አጠገብ ከደረሱ ሰዎች አንዱ፤ ካፒቴን ፍራንክ ጀምስ ይባላል። ካፒቴኑ ለናቱ በፃፈው ደብዳቤ፤ "ራሴ የቆረጥኩትን የቴዎድሮስን ፀጉር ሹሩባ ለሴቶቹ ልጆቼና ላንቺ ለውድ እናቴ ልኬያለሁ" ብሏል። የቴዎድሮስ አስከሬን ምስል ላይ ሙሉ ፀጉራቸው የማይታየው ለዚሀ ነው።


**ቁጥር 150፤** የአስከሬን ምርመራውን ያደረጉት ዶክተር ብላንክና ዶክተር ሉምስዴን ነበሩ። በምርመራውም፤ በሽጉጥ ጥይት ራሳቸውን እንዳጠፉ ተረጋግጧል። ጥይቱ ባፋቸው በኩል ገብቶ በጭንቅላታቸው በጀርባ በኩል ለመውጣቱ ተረጋግጧል። የሚገርመው ነገር፤ ዶክተር ብላንክ ፊታቸውን እያገላበጠ ሲመለከት፤ ፊታቸው ላይ፤ በቅርብ ጊዜ ብዙም ያላሳዩት፤ ደብዘዝ ያለ የደስታ የፈገግታ ምልክት ማየቱን ገልጧል። ሌሎቹ ግን የንቀት ምልክት ነው ብለውታል። ሆኖም ከአዲስ መጭዎች ይልቅ፤ ብላንክ ቴዎድሮስን የበለጠ ያውቃቸዋል።

**ቁጥር 151፤** የአፄ ቴዎድሮስ አስከሬን እንዲቀብር ትዛዝ የተሠጠው ለመልከተኛው ራሳም ነበር። በሚገርም ሁኔታ፤ ቴዎድሮስ ከሁለት ሳምንታት በፊት ከራሳም ጋር ሲያወሩ፤ ራሳምን፤ "እኔ ስሞት፤ ሰላደረስኩብህ በደል ሬሳዬ ላይ ቆመህ ትሰደበኝና ታዋርደኛለህ፤ ከፉ ሰው ስለሆን እንዳይቀበር ትላለህ።" ብለው ተናግረው ነበር። ይህንንም ሁኔታ አብሮ የሰማው ቫልድማየር፤ ራሳምን፤ ንጉሡ ምን እንዳሉት አስታውሶታል። ራሳም በተቻለው መጠን ንጉሡ በሥርአት እንዲቀበሩ ሞክሯል። ቴዎድሮስ ራሳምን ወዳጄ ብለው ስለሚጠሩት፤ ለኢትዮጵያውያኑ፤ ወዳጅ የሚለው ቃል ከንቱ እንዳልሆነ ለማሳየትም ነበር።

**ቁጥር 152፤** ቴዎድሮስ በመጨረሻዎቹ ሰአታት፤ ወታደሮችን፤ የገበችሁልኝን መሀላ እንስቼአለሁ፤ ሂዱ ብለው ሲያሰናብቱ፤ ሰባት አለቆቻቸው ግን እስመጨረሻው እስከቴዎድሮስ ጋር እንዋጋለን ብለው ወስነዋል። ከእነዚህም መካከል፤ ራስ እንግዳ (ጠቅላይ ሚኒስትር)፤ እንግዳወርቅ (የቴዎድሮስ የመድፍ ሀላፊ)፤ የቋራው ራስ ባራኪ፤ ደጃዝማች አብዬ፤ አጋፋሪ መሸሻ፤ የቴዎድሮስ ጠመንጃ ያዥ አማረ፤ የቴዎድሮስ አልፍኝ አስከልካይ ወልደገብሬል ነበሩበት። ደጃማች አብዬ፤ ፈረንጆቹን እንግደላቸው የሚል ሀሳብ ስለሠጡ፤ ቴዎድሮስ ሲሮበዋቸው ነበር። ተሰደቡም አልተሰደቡም በታማኝነት ከጌታቸው ጋር ወድቀዋል። ስለ ራስ እንግዳ ታማኝነት፤ ራሳም ሲገልጥ፤ እንግዳ ለቴዎድሮስ ሲል መርዝ ይጠጣል ብሏቸዋል።

**ቁጥር 153፤** ቴዎድሮስ ራሳምን ሲቀበሉ፤ በጣና ሀይቅ አጠገብ ቆራጣ በሚባል ቦታ ነበር። እንደ ራሳም ንጉሣዊ አቀባበል የተደረገለት የውጭ ሰው የለም። እስረኞቹን እፈታለሁ ብለው ቃል ገብተው፤ ሁሉም እስረኞች፤ ችሎት ተከፍቶ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲጠይቁ ተደርገ። ቴዎድሮስ ራሳቸው፤

*እንገታቸውን ደፍተው ስለበደልኳችሁ፣ ይቅር በሉኝ ብለዋል፡፡ እስረኞቹም፣ እንደ ባህሉ ይቅር ብለናል ብለዋል፡፡ በኋላ ግን፣ ቴዎድሮስ፣ ሃሳባቸውን ቀይረው፣ እስረኞቹ እንደገና እንዲታሰሩ አስደረጉ፡፡ ከውጭ ፀሀፊዎች፣ ሄንሪ ዱፍተን የተለየ መልስ ሲኖረው፣ ሌሎች ግን የቴዎድሮስ ተለዋዋጭ ባህሪ ነው በማለት ስውየውን መውቀስ ይመርጣሉ፡፡ ሆኖም፣ እንደ ዱፍተን ገለፃ፣ ለቴዎድሮስ ሃሳብ መቀየር ምክንያት፣ የፈረንሳዩ ባርደልና፣ አስተርጓሚው አቶ ሳሙኤል ናቸው፡፡ ሁለቱም፣ ንጉሡን፣ አሁን ቢለቋቸው፣ እንግሊዞቹ ተመልሰው ጦር ይዘው መውጋታቸው አይቀርም የሚል ሃሳብ ስለተናገሩ ነው፡፡ ቴዎድሮስ ይህን ሀሳብ ሳያሳዩ ሌላ ሰበብ በመፍጠር ሰዎቹን ወደ መቅደላ መለሱ፡፡ ራሳም ደግሞ ባርደል አላደረገም ባይ ነው፡፡ ነገር ግን ባርደልና የቴዎድሮስ እማች እንግዳወርቅ የተለየ ግንኙነት ስለነበራቸው ፈርተው ነበር፡፡ የአውሮፓውያኑ ደብዳቤና ወረቀቶች በቴዎድሮስ ኢጅ ነበሩ፣ አላስነበቧቸውም፡፡ እንግሊዞቹ፣ ባርደልን በቅፅል(በሚስጥር) ስም "ሽሪምፕ ብለው ነበር የሚጠሩት፡፡ ንጉሡን ደግሞ "ቦብ" አንላቸው ነበር ይላል ራሳም፡፡ ታዲያ ባርደልን አስጠርተን እንዳያጋልጠን ለምነነው ነበርና፣ እሱም፣ ደብደቤው ላይ የሚያስወነጅል ቦታ ካየሁ በትክክል አልተረጉመውም ብሎ ቃል ገብቶ ነበር ይላል፡፡ አውሮፓውያኑ፣ በእጃቸው የነበሩ ደብዳቤዎችና ወረቀቶችን፣ ንጉሡ ሳይደርሱባቸው በተገኘው መንገድ፣ በውሀ፣ በማኘክ በኋላም በእሳት ያቃጥሉ ነበር፡፡ ካሜሮን ለየሽፍታው ሁሉ እንደማለፊያ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ፓስፖርት ለሁሉም አሠርቶ ነበር፣ ሆኖም ከንጉሡ ኢጅ ሳይወድቅ ድራሹን አጥፍተውታል፡፡*



የአፄ ቴዎድሮስ መስቀል

# ምዕራፍ አስራ ሶስት

የቴዎድሮስ ቀብር፣ ባላንጣ ንግሥቶች፣ የመቅደላ ስንብት፣ የጄኔራል ናፒየር ትዛዝ፣ የተዘረፉ ዕቃዎች ጨረታ፣ኦፊሻል ሪፖርት

መቅደላንና አካባቢውን ለቀን ከመሄዳችን በፊት መከናወን የሚገባቸው የተለያዩ ነገሮች ነበሩ:: የአፄ ቴዎድሮስ አስከሬን መቀበር ነበረበት፤ ንግስቲቱን ማፅናናት ያስፈልጋል፤ የወጣቱ ልዑል ዕጣ መወሰን ነበረበት:: ኦሮሞዎቹ፣ አሁን የማይሆኑ ነገሮች እያደረጉና ሰው ለመግደል ጨኸት እያሰሙ ስለሆነ፣ እነሱን የሚያስቆማቸው ነገር መደረግም ነበረበት:: የመቅደላ ስደተኞችም በሽሎን እስኪሻገሩ ድረስ መታጀብ ነበረባቸው:: ምሽጎች፣ መከለያ አጥሮች፣ ማማዎች፣ ወህኒቤቱ፣ ቤተመንግሥቱና የገበሬዎቹ ቤቶች ሳይቀሩ መውደም ነበረባቸው፤ በመጨረሻም ሰስቱን የተራራ ምሽጎች ሃላፊነት ላለበት የአቢሲኒያ ባለሥልጣን ማስረከብ ነበር::

የመጀመሪያው ቀን፣ አሽናፊ ወታደሮችን ወደ ካምፕ በመመለስ ነበር ጊዜው የተያዘው:: ከነዚህ መሀል ግን አንድ ሬጅመንት ምሽጉን እንዲጠብቅ ወደኋላ ቀረ:: በተጨማሪም መቅደላ የወደቁትን የቴዎድሮስ ጦር አለቆችን መቅበር፣ ወደ ሰላሳ ሺ የሚሆኑ ከኛ ካምፕ የጥይት ርቀት የሚሆን ለስፈሩ መጠጊያ ለሌላቸው አቢሲኒያውያን ምግብ ማከፋፈል ነበር::

ናፒየር የቴዎድሮስን ቀብር ትዛዝ ከማስተላለፉ በፊት፣ ቀሪዋ እቴጌ፣ ባልዬው እንዴት እንደሚቀበሩ ፍላጎታቸው ተረጋገጠ:: እቴጌዋ ስትመልስ፣ ዋናው የጦር አዛዥ ያሻውን ማድረግ ይችላል፤ ነገር ግን፣ ፍታቱ፣ ንጉሡ በሚወዷቸው ቄስ እንዲደረግ ምኞቷ መሆኑን ገለፀች:: ይህንን እንኳ ጄኔራሉ ምንም አልተቃወመም::

ከዚያም ለተወሰኑ ሰዎች፣ አስከሬኑ በሀር ጨርቅ በክብር ተከፍኖ ለቀብር እንዲዘጋጅ ትዛዝ ሰጠ[153]:: ከዚህ በኃላ፣ አስከሬኑ እንደነገሩ በተሰራ ሳጥን ውስጥ ተቀምጦ፣ ናፒየር ይቀበርበት ብሎ ወደጠቆመው ቦታ፣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር ተወሰደ:: ጥልቀት የሌለው የመቃብር ጉደጓድ በመሀል ቅጥር ግቢው ተቆፍሮ ነበር:: በጣም ደከም ያለው መነኩሴ ካህን ተጠርቶ ፀሎት እንዲያደርስ ተጠየቀ:: በግልፅ እንደታየው፣ ሁኔታው በጣም አሳዛኝ

---

[153] (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

ስለነበር፣ ሥርአቱን በጥድፊያ ነበር ያደረገው:: በሁለት ጠንካራ ወታደሮች፣ እስከሬኑ ወደ ጉድጓዱ ወረደ፤ መነኩሴው አፍር ዘግኖ በሳጥኑ ላይ ረጨ፤ ከዚያም በአካፋዎች የሚዛቀው አፈር ሳጥኑ ላይ እየተንኳኳ ወርዶ ለአይን እስኪሰወር ድረስ ሸፈነው::

በዚያን ቀን፣ ለዋግሹም ጎበዜ መልከተኛ ተልኮ መቅደላን እንዲረከብ ተጠየቀ:: በሶስተኛው ቀን ጠዋት፣ ለጄኔራሉ መልስ መጣ:: ብልጡ መስፍን በመልሱ፣ መቅደላን እንደማይፈልግ ነው:: ቴዎድሮስ በሕይወት እያሉ በብልጠት ከመቅደላ ርቆ ነበር፤ አሁን ቴዎድሮስ ሰለሞቱ፣ እንደሱ ሀሳብም፣ የበሸሎ ሸለቆ በኦሮሞዎች የተከበበ ሰለሆነ በፈቃዱ እሰረኛ ለመሆን ፍላጎትም የለውም:: ይልቁንስ፣ ሰር ሮበርት በደግነት ምሽጉንም ጨምሮ የቴዎድሮስን መድፎች ቢሰጠው የተሸለ ስጦታ አድርጎ በወሰደው ነበር:: ለምሽጉም መከላከያ አድርጎ ይጠቀምበት ነበር::

ከእንግሊዙ ጄኔራል ጋር ባደረገው የደብዳቤ ልውውጥ ዋግሹም ምክንያቱን አስረዳ:: ጎበዜ የሚታወቅበት ነገር ሌላ ሳይሆን ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ መሸሽ ነው፤ ወይም ከርቀት፣ ለደህንነቱ በማያሰጋ ቦታ ሆኖ ጉዳዮችን ማጤን ነው:: በሁሰቱ ወራት ውስጥ፣ የቴዎድሮስን ካምፕ የተከታተለው፣ ሊደረስበት ከማይችል ከፍታ ወዲያና ወዲህ እያለ ነበር:: የመጨረሻው የአፄ ቴዎድሮስ እንቅስቃሴ፣ ጉረኛውን ዋግሹም በጥድፊያ ወደ ርቀት ቦታ እንዲሸሽ ነው ያደረገው:: ናፒየር፣ ለራሱ ሆነ ለሀገሩ፣ አለቃ በመቀየር ለጎበዜ መወገኑ ጥቅሙ አልታየውም:: ጎበዜ የቴዎድሮስን ያህል ግብ ያለው ሰው አልነበረም፤ ነገር ግን ብዙም ጨካኝ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ መቅደላም ሆነ መድፎች አልተሠጠውም::

በሚቀጥለው ቀን ሁለቱ ባላንጣ ገዥዎች (ንግሥቶች)፣ ወርቂትና[154] መስታወት መቅደላን ለመውሰድ ተወዳዳሪ ሆነው ቀረቡ:: ይህም፣ ርዳታቸውን ለማግኘት ታስቦ፣ እነሱን እነሳስቶ ቴዎድሮስን እንዲከቡ ለማድረግ በመጣው በሚር አከበር አሊ አማካኝነት ነው:: ከሁለቱ መሀከል፣ ወጣትና ወፈር ብላ መልከመልካም የሆነችው የእርባ እመቷ መስታውት በናፒየር ተመረጠች:: በእንግሊዝ ካምፕ ውስጥ በሰነበተችበት ጊዜ የሚገባው ከብር ተሠጧት ከሀር የተሠራ ድንኳን መኖሪያዋ እንዲሆን ተደረገ:: እሷና፣ የሰፔይን ተወላጅ የሚመስለው በጣም መልከኛው የስድስት እመት ልጇ፣ በጣም ድንቅ በሆኑ፣ የሀገሩ ጎበዝ የተባለ ባለሙያ የሠራቸው ልብሶችና ጌጦች አድርገው ነበር የሚታዩት::

---

154 (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

የጀኔራሉ ወጥቤቶች፣ ባላቸው ችሎታ ሁሉ ለንጉሣውያን ቤተሰቡ ምርጥና ጣፋጭ ምግቦች እንዲያቀርቡ ታዘዋል፡፡ ንግሥቷ፣ በወጥቤቱ የተዘጋጀውን ምግብ አሠራር ችሎታ ማድነቋን ለማሳየት ስትል፣ የቀረበላትን ምግብ ሳታማርጥና ሳታስተውል ትበላ ነበር፡፡ በድንጋጤ ለሚመለከታት የፖለቲካ ፀሐፊው ምንም ደንታ ሳታሳይ፣ ገንፎውንም፣ ሥጋውንም፣ ድንቹንም፣ ብቻ በፊቷ የቀረበውን እየበላች፣ ከዛም የቀረበውን ምግብ ሳትጨርስ ቡና ትጠጣና፤ በጣም የጣፈጣት ምግብ ከበላችም፣ የሽጉጥ ድምፅ እስኪመስል ድረስ ከንፈሯን በማላቀቅ ታጣጥማለች፡፡

ንግሥቷ፣ መርካቷን ለመግለፅ ጮክ ብላ ከልቧ ከት ብላ ትለቃለች፡፡ ከዚያም በሥነ ሥርአት ከለበሰችው ልብስ ወደጫፍ፣ ለዚሁ ብላ ባሰረችው ጨርቅ ደኅስ ያለውን ከንፈሯን ትጠርጋለች፡፡ ብርቱካንማ ቀለም ያላት ሔብን[155] የመሰለች ግን ደግሞ የቪነስ ጭንቅላትና ቅርፅ ያላት ሰው፣ ጠጅና አረቄ ተደባልቆ፣ በቀንድ ዋንጫ ይዛላት ቀረበች፡፡ የቀረበላትን መጠጥም በደስታ ከተጎነጨች በኋላ፣ ኮራና ኮስተር ብላ መታየት ጀመረች፤ ይህም ከመጠጣቷ በፊት ከነበረው ሁኔታዋ በለጥ ብሎ ነው፡፡ እንደ ኢያጎ ብልጣ ብልጥ የሆነ መኮንን፣ ዲያብሎስን እንኳን ማባበል በሚችል ምላሱ ንግስቲቷን ለምስል እንደትቀመጥ አግባባት፡፡ ተረጋግታ ባለመቀመጧ፣ ከሶስትና ከአራት ሙከራዎች በኋላ ጥሩ ነው የተባለው ስዕል ተወለደ፤ የዚህ ቅጅ ደግሞ ለመላው አውሮፓ መንግሥቶችና ለአሜሪካ መንግሥት ተላከ፡፡

ሶስተኛው ቀን፣ ጠቅላላ ቁጥራቸው 33 የሆኑ የቴዎድሮስ መድፎችን በማውደም ነበር ያለፈው፡፡

በዚህ ሁሉ ጊዜ ግን በውሃ ጥምና በቀለብ ማነስ ምክንያት ተሰቃይተን ነበር፡፡ ሆኖም በአራተኛው ቀን፣ ጦሩ የበሽሎ ሸለቆን ለቆ ወደ ደላንታ አፋፍ ይሄዳል የሚል የጥሩ ወሬ ጭምጭምታ ስለተሰማ በሁሉም ሰው ልብ የደስታ ስሜት ፈጠረ፡፡

መቅደላ በወደቀ በአራተኛው ቀን ጠዋት፣ ቁጥራቸው 30 ሺ የሚሆኑ አቢሲኒያኖች ወደ ደላንታ ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ ይህንን ሁኔታ ደግሞ ኦሮሞዎቹ አውቀው ስለነበር፣ እንደ ጆፌ አሞራ ከጎንና ከኋላ፣ አንዳንዴም በድፍረት መሀል ድረስ እየገቡ ብዙ ሰዎችን እንደ አስረኛ ወሰዱ፡፡

---

155 ሔብ በግሪኮች ቀደምት ታሪክ የወጣቶቸ አምላክ የሆነች ስትሆን፣ የዙስና የሄራ ልጅ ነች፡፡



*ንግሥት መስታውት ከልጇ ጋር*

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን፣ ከሌሎች ጋር አንድ ላይ ሆኜ እየጋለብኩ የተረፈውን ምሽግ ለማየት ሄድኩ፡፡ ከሁለት ሰአታት በኋላ፣ በሮያል ኢንጂነርስ እማካኝነት ነፍስ ያለው ማንኛውም ሰው እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ፣ ምሽጉን ለመደምሰስ የተመደቡት ሰዎች ለራቸውን ጀመሩ፡፡ የደቡብ መግቢያው ወይም የቃፊር በር ነበር መጀመሪያ የተደረመሰው፤ ከዛ ወደ መካዝኖች የሚወስደው የምስራቁ በር ተደገመ፤ ነፋሱ ከምስራቅ አቅጣጫ ይነፍስ ስለነበር፣ በአምባው ላይ፣ በምስራቅ ጠርዙ ላይ ያሉ ቤቶች በእሳት ተለኮሱ፡፡

ከዚያ እየተነሱ፣ መሀንዲሶቹ በቅልጥፍና እያንዳንዱን ቤት በያዙት የእሳት ችቦ መለኮስ ጀመሩ:: ተመልካቾቹ ተጣድፈው የማያሰጋ ቦታ ሄዱ፤ ከዚያም ሆነው የሚነሳውን የእሳት ማዕበል ለማየትም ነበር:: ለዚህ ሁኔታ አመቺ ሆኖ የተገኘው የስላሴ ደቡባዊ ጠርዝ ነበር:: እንግዲህ ከዚህ ቦታ ሆኖ መቅደላን በአንድ ሺ ያርዶች ርቀት ማየት ያስችላል::

የምስራቁ ነፋስ አዝግሞ እየጠነከረ እንደ ምላስ ቦግ ቦግ የሚሉት የእሳት ነበልባሎቹ በቤቶቹ ጣሪያ ላይ አስኪታዩ ድረስ ካስፋፋ በኋላ፣ እሳቱ እየደመቀና እየሰፋ ሄዶ፣ ከነፋሱ ጋር እየተጫወተ፤ ከመሀል ወደላይ እየጎነ መውለብለቡን ቀጠለ:: የማያቋርጥ የነፋሱ ትንፋሽ ነበልባሎቹን ወደ ቀይ ማዕበል ቀየራቸው፣ ነበልባሎቹም አንድ ላይ ተነባብረው የእሳት ሀይቅ ፈጠሩ::

ሙቀቱም እየጨመረና እየጠነከረ መጣ፤ ያልተተኮሱ ሽጉጦች፣ ጠመንጃዎችና ጥይቶች በብሪታናያ መሀንዲሶች ወደእሳቱ ሲወረወሩ ስለነበር ጆሮ በሚያደነቁር ድምፅ ይፈነዱ ነበር[156]፤ ፍንጣሪዎቹም በአስፈሪ ሁኔታ አጠገባችን ድረስ ያፏጩ ነበር:: ሶስት ሺ ቤቶችና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሚነዱ ነገሮች እየጋዩ ነበር:: በዚህ፣ ግዙፍ፣ በሚውረገረግ እሳት አንድ ቤት እንኳን መትረፍ አይችልም::

---

ጥሩምባዎች የደስታ ድምፅ አሰሙ፤ ከበሮዎችም እንዲሁ፣ የሚነፉት የሙዚቃ መሳሪያዎች ኀላ ብለው ተሰሙ፤ ወፎችም ቢሆን በደስታ ዘመሩ፤ ብሩህ የሆነ ንጋት የሚያዝያ 18፣ 1868 ቀን መምጣቱን አበሰረ::

ሁላችንም ቢሆን የአቢሲኒያ ዘመቻ ተውኔት ውጤትን አይተናል:: በዚህ ቀን፣ ፊታችን ወደ ቤታቻን መመለሻ ጉዞ ወደ ሰሜን አዞርን::

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን ቀዳሚው ጦር የፋላን ቁልቁለት ወርዶ ወደ አሮጌ ሸለቆና ወደ በሽሎ አመራ:: የጓዝ መስመሮችም ተንቀሳቀሱና፣ እራት ሰአት ላይ መንገዱ ለጦሩ ክፍት ሆነ::

ሬጅመንቶቹ ልክ እንደ ሰልፍ፣ ተዘጋጅተው፣ አግረኛው፣ ፈረሰኛው፣ መድፈኛው፣ መሀንዲሶቹ፣ ቆፋሪና ግንበኞች በሥርአት፣ በረድፍ ነበሩ:: ዋናው አዛዥ ፈረሱ ላይ እንደወጣ፣ "ወደፊት!"፣ የሚለው ትዛዝ ተሰማ፤

[156] (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

በባንዱ እየተመራ፣ የ45ኛው ሬጅመንት ጠመንጃውን እንግቦ ከሙዚቃው ጋር በተሰማማ ርምጃ በኩራት ቁልቁለቱን መውረድ ጀመረ:: የተወላጆቹ የህንዶች ሬጅመንት አግረኛና ፈረሰኛ፣ መድፈኛው፣ የባህር ሀይል ብርጌድ በመጨረሻም "የቄልንግተን መስፍን" የሚባለው ሄደ:: የሬጅመንቱ ወደኋላ ያለው የመጨረሻው ክፍል፣ መንገድ ጀምሮ ሲንቀሳቀስ፣ ሰድስት ሺ ከሚሆኑ ሰዎች የሚወጣ "ቺርስ" የሚል ተደጋጋሚ ድምፅ ሲያሰማ፣ የሚቀባበለው ድምፅ፣ በበረሀውና ባደኀቸውን በቀሩት ጉብታዎች ላይ እየነጠረ ነበር:: ይህም በአሰር ማይል ርቀቶች በተጠንቀቅ ለሚጠባበቁት አሮሞዎች፣ ወታደሮቹ የስንብት ድምፅ እያሰሙ መሆኑን እንዲገነዘቡ አደርጓቸዋል::

ግርማ ሞገስ ያላቸው፣ ጨለም ብለው ግትር ያሉት ሶሰቱ ምሽጎች፣ ከተራሮች በላይ ራሳቸውን ቀና አድርገው የደቡቡን አድማስ ፈጥረዋል:: ከጠዋቱ ሰማይ ጋራ በመደባለቅ፣ በብሩህ የጮራ ቀለሞች ደምቀው ሲታዩ፣ ብርቅዬ ለሆነ፣ የዕይታ የጀርባ ምሰል መጠቀም ያስችሉ ነበር:: የሩቅ ባለዝናው መቅደላ፣ እናቱ ጭጋግ በሚመስል ጭስ ተሸፍኗል፤ ከሚቃጠለው ንብረት፣ የእማልከትን ቁጣ ለማርገብ የሚቀርብ ገፀ በረከት እስኪመስል ድረሰ ጭሱ ወደላይ ይወጣል::

የመጓጓዣ ከብቶቹ ጉልበት እንዲያገኑ፣ መቅደላ በነበርንበት ጊዜ በገፍ ከተሰበሰበው ቀለብ እንዲመገቡ ተወሰኗል:: ለዚህም ሲባል፣ ከደልዳለው ቦታ ትንሽ ጎድጎድ ያለ ቦታ ተመርጦ ለካምፕ ሆኗል::

በጣም አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ደግሞ አትኩሮት መሰጠት ነበረበት:: በጦር ግንባሩ ሲጋፈጡ የነበሩ ወታደሮችን ለመጥቀም ሲባል ብዛት ያላቸው ከመቅደላ የተዘረፉ ንብረቶች መሸጥ ነበረባቸው፤ ይህም፣ ገንዘብ ላላቸው ሰዎች ወይም ጥንታዊ ዕቃዎችን ለሚወዱ ሰዎች ነበር:: አዛዥ መኮንኖች ለሬጅመንታቸው ወይም ለወታደሮቻቸው ይጠቅማሉ የሚሏቸውን ቅርሶች እንዲመርጡ ተጠይቀው ነበር:: እነዚህ ንብረቶች ወይም ቅርሶቹ በአስራ እምስት ዝሆኖችና በ200 በቅሎዎች ተጭነዋል::

ከጠዋቱ ሶሰት ሰአት ተኩል ሲሆን፣ ታምቡር ሲመታ፣ የተለያዩ ሬጅመንቶች ከየካምፓቸው በመውጣት 200 ያርዶች ርቀት ላይ የሚገኝ ትንሽ ከፍ ያለ ደልዳላ ቦታ ላይ፣ በመሀል፣ እሰረኞች፣ መኮንኖችና ጄኔራሎችን በማድረግ እራት ማዕዘን በሆነ ዙሪያ ቆሙ::

የጦሩ ካህን ሰለ እሰረኞቹ ሁኔታና እና ሰለመጣንበት ድል ሲገልፅ፣ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሀል እንባ ያላረጠበው አይን ማግኘት ይከብዳል:: ይህን በሰሙ፣ በሁሉም ሰዎች ላይ ጥልቅ ሰሜት ነው የፈጠረው፤ የሰውየው ድምፅ ቃና፣ የሚያስደስተው የፀሀይ ብርሃን፣ በርቀት የከበቡት የተራራዎቹ ጠቆር ያለ



የመቅደላ ቃጠሎ

ጥላ፣ በላያችንና በዙሪያችን የሚዘምሩት ወፎች፣ የሚንሳፈፉት ደመናዎች፣ ያ አሁድ ቀን በካላንደር ላይ ካሉ ቀናት በበለጠ ሁኔታ፣ በቦታው በነበሩ ሰዎች ይታወሳል።

በሚቀጥለው ቀን፣ ወደ አቢሲኒያ በዘመተው ጦር በጣም የሚደነቅና ስልት ያለው ሰልፍ ተደረገ።

ዲቪዢኑም ስድስት ረድፍ ያለው የአራት ማዕዘን ቅርፅ በመስራት ተሰለፈ፤ መሀሉ ክፍት ነበር። አሰረኞቹ፣ ሲቪል ሠራተኞች፣ የውጭ ወይም የሌላ ሀገር መኮንኖች ውስጥ እንዲሆኑ ተጋበዙ። የጄኔራሉ ረዳት፣ ኮሎኔል ፍሬድ ቲሰገር፣ የጄኔራሉን መግለጫ ከፍ ባለ ድምፅ አነበበ። በዘመቻው ያጋጠሙ ሁኔታዎችንና ግቦችን በሚያዳምቅ አነጋገር ነበር።

*"የአቢሲኒያ ጦር ወታደሮች! የኢንግላንድ ንግሥትና ህዝቡ፣ ያገራችን ሰዎች ከረዥምና አሰቃቂ ከሆነ አሰራት እንድታስለቅቁ፤ በአቢሲኒያው ንጉስ፣ በቴዎድሮስ የተደፈረውን የአገራችን ክብር እንድታስጠብቁ፣ በጣም አስቸጋሪና ፈታኝ የሆነ ዘመቻ ግዳጅ ሰጥተዋችኋል።*

*የሀገራችን ትዛዝ ክብር በሚገባው ሁኔታ ስለተወጣችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ።*

*አብዛኛውን ጊዜ በትሮፒካል ፀሀይ፣ ወጀብ ባለው ዝናብ መሀልና በሚያዳልጥ መሬት፣ 400 ማይሎች ርቀት ተራራማና አስቸጋሪ የሆነ አገር አቋርጣችኋል።*

*ቀጥ ያለ ዳገትና ገደላማ የሆኑ ከ10ሺ ጫማ ከፍታ በላይ ያላቸው ተራራዎችን፣ ስንቃችሁ ከናንተ ጋር እኩል ባልደረሰበት ሁኔታ ተጉዛችኋል።*

*ከጠላት አጠገብ ስትደርሱም፣ ምንም እንኳ በጣም አነስተኛ ምግብ ብትይዙም፣ እንዳንዶቻችሁ ለብዙ ሰአታት ምግብ ሆነ ውሀ ሳትቀምሱ፣ በአራት ቀናት ውስጥ ፈታኝ የሆነውን በሽሎን ተሻግራችሁ፣ ከተመቸው ምሽጋቸው ሆነው እንደሚያሸንፉ በርግጠኛነት ቁልቁል የወረዱትን የቴዎድሮስን ወታደሮች አሸንፋችኋል።*

*በሺ የሚቆጠሩ መሳሪያዎቻቸውን እግራችሁ ስር አስቀምጠዋል።*

*ከሰላሳ በላይ የሚሆኑ፣ አብዛኞቹ ከብደት የነበራቸውና በቂ እርሳሶች የነበሯቸውን መድፎችን ማርካችሁ ሰባብራችኋል።*

*በእልምት ባይ ተጋዳይነት፣ ቴዎድሮስ ቀሪ አለቆቹና ተከታዮች ሲከላከሉት የነበረውን የማይደፈር ምሽግ ጥሳችሁ ገብታችኋል።*

*መግቢያውን ጥሳችሁ እንደገባችሁ፣ ምህረት የማያውቀው ቴዎድሮስ፣ የተሠጠውን ምህረት ስላላመነ በገዛ እጁ ራሱን አጥፍቷል።*

*የብሪታንያ አስረኞችን ብቻ ሳይሆን፣ የሌሎች የወዳጅ አገር እስረኞችንም አስለቅቃችኋል፡፡ ከዘጠና በላይ የሚሆኑ የአቢሲኒያ ባላበቶችና ገዥዎችን ሰንሰለት ፈታችኋል፡፡*

*የብዙ ሰዎች ሕይወት የጠፋበት መቅደላ በአሳት ነዶ የተለበለበ አለት ሆኖ ይቀራል፡፡*

*የኛ፣ ፈጣንን ሙሉ በሙሉ የሆነ ውጤት፣ በመጀመሪያ፣ ለትክክለኛ ምክንያት ሰለመጣን፣ አጁ በኛ ላይ እንደነበረ በሚሰማኝ በፈጣሪ በረከት ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ እናንተ በሳያችሁት ከፍተኛ ስሜት ነው፡፡*

*የህንድ ወታደሮች ከአውሮፓዊ ጓዶቻቸው ጋር ለመሰለፍ በዘርና በእምነት የነበረውን ልዩነት ረስተዋል፡፡ ከዚህ በፊት፣ ማንም ሌላ ሠራዊት እንደናንተ በከብር ስሜት ጦርነት የተቀላቀለ የለም፤ ይህ ደግሞ ብዙ ድካምና ችግር አልፋችሁ እንድትሄዱ አድርጓችኋል፤ ጠላትን ለማጥቃት ስትቃረቡ ብቻ ነው የችኮላ መንፈስም ያሳያችሁት፡፡*

*በየግላችሁ የደረሰው ሁኔታ ማስታወሻ ቶሎ ያልፋል፤ ነገር ግን በድፍረት ያሳያችሁት ወኔ በታሪክ ውስጥ ይኖራል፡፡*

*ንግሥቷና የኢንግላንድ ህዝብ አገልግሎታችሁን ያመሰግናል፡፡*

*እንደ ጦር አዛዥነቴ፣ በኔ በኩል ግዳጃችሁን ለመወጣት ላሳያችሁት ሙሉ ስሜት፣ እናም ለጠበቃችሁት ጥሩ ሥነ ሥርአት አመሰግናችኋለሁ፡፡ መንደርተኞቹ ተዘረፉ ወይም ተበደሉ፣ ጉዳት አደረሱ ተብሎ አንድም ወታደር ላይ አቤቱታ አልቀረበም፡፡ በሞቃታሙ የዙላ አየር ጠባይና በቁማይሌ ማለፊያ፣ በተጨማሪም በየቦታው ባሉ ጣቢያዎች፣ ለኛ ሲሉ የሚደክሙትና ግንኙነታችን እንዳይቋረጥ ያደረጉ ጓዶቻችንም የሚገባውን ዕውቅና ለመስጠት መርሳት የለብንም፡፡ እያንዳንዳቸው እናም ሁሉም፣ ከኛ ጋር ለመሆን ያላቸውን በሙሉ ይሰጡ ነበር፡፡ ስለዚህ የኛን ምስጋና ማግኘት ይገባቸዋል፡፡*

*ተመልሳችሁ እስከትሳፈሩ ድረስ ደህንነታችሁን አጠብቃለሁ፤ እስከ ህይወቴ መጨረሻ የናንተ አዛዥ መሆኔን በኩራት አስታውሳለሁ፡፡"*

*ሮ. ናፒየር፣ ሉተናንት ጄኔራል*

*ጠቅላይ አዛዥ*

*የደላንታ ካምፕ፣ ሚያዝያ 20፣ 1868*

(ከላይ የተጠቀሰው ወታደራዊ መግለጫ እያንዳንዱ ዝርዝር እውነት ነው፡፡ ጄኔራሉ ከሚገባው በላይ ራሱን ከፍ አድርጎ በፅሁፉ አላስቀመጠም፡፡ ግልፅና እንደ ራሉ ትሁት ነበር፡፡)

በዳውንትና ደላንታ አፋፍ ጊዜያዊ ካምፕ በቆየንበት በሶስተኛው ቀን፣ ለሽያጭ የሚቀርቡት ዕቃዎች በሙሉ ለአጫራቹ ተዘጋጁ፡፡

በሥነ ሥርአት በሚተዳደር የወታደር ካምፕ ውስጥ ለአዲስ አይነት እንቅስቃሴ ጥሪ የሚደረግበት ታምቡር መመታት ተጀመረ:: ሁሉም መኮንኖች፣ ተመልካቾችም ከመቅደላ የተዘረፈውን ንብረት በተከመረበት የግማሽ ኤከር ዙሪያ ተሰበሰቡ::

ለአጫራችነት የተመረጠው ሰው ሎተናንት ኤስ ነበር፤ ደከመኝ የማይል ሰው ሆኖ በተፈጥሮው ቀዳማዊ ናፖሊዮንን የመሠለ ገፅታ ያለው ነበር:: ከየሀገሩ የተሰበሰቡ ምርጥ ምንጣፎች ተዘረጉ፤ በሺዎች ከሚቆጠሩ አብያተክርስቲያናት የተሰበሰቡ ዕቃዎች በጠዋቱ ፀሀይ ያብረቀርቃሉ:: በግርግር፣ ግራ በሚያጋባ ሁኔታ እርስ በርስ የሚጋፉት ሰዎች እቃ ገዥዎች ነበሩ:: (በአለም ውስጥ በጣም ጠብ አጫሪ የግርግር ቡድን ቢኖር፣ የእንግለዞች ነው::) እቃ ገዥዎቹ ደግሞ፣ በጊዜው ስለ ጥንታዊ ቁሳቁሶች እውቀት ያላቸው ሰዎች ሆኑ፤ በሚገርም ሁኔታ እውነተኛውን ዕቃ መስሎ ከተሠራው፣ ወርቁን ከብልጭልጩ ለይቶ የማወቅ ችሎታ አላቸው::

የተጫራቾች ቁጥር ትንሽ አልነበረም:: እያንዳንዱ መኮንንና የሲቪል ሠራተኛ የመቅደላ ማስታወሻ መያዝ ይፈልጋል:: አንዱ ከብር የተሠራ መስቀል ወይም ከብሮንዝ የተሠራ ይገዛል፤ ሌላው የዕጣን ማጨሻ፣ ሌላው ደግሞ ጎራዴ:: ከብር የተሠሩ ዋንጫዎች፣ መጠጫዎች፣ በብዛት ነበሩ:: ከሀር የተሠሩ ጃንጥላዎች፣ በወርቅ ያጌጡና የውድ ቀለም ባላቸው ድንጋዮች የተሽቆጠቆጡ ኮርቻዎች፣ ድንኳኖች፣ ምንጣፎች፣ ብሩህ በሆነ ቀለም የተፃፉ መፅሐፍ ቅዱሶችና ሌሎችም ፅሁፎች፣ ብዙ ዋጋ የሌላቸው ጌጦችና፣ ሀብሎች፣ ቀለበቶች፣ አምባሮችን በሙሉ ገዥዎች አግኝተዋል::

ሚስተር ሆልምስ፣ እንደ ብሪቲሽ ሙዚየም ተወካይነቱ በጣም ተደስቷል:: ብዙ ገንዘብ ስለነበረውም ብዙ ነገሮችን በጨረታ አሸንፏል:: ነገር ግን ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ሃብታም ለሆነ ሬጅመንት፣ ፀኛው ሁሳር፣ ይገዛ ስለነበር እየተፎካከረ አስቸግሮታል:: የቴዎድሮስ የግል የሆነ ማንኛውም ነገር ሲቀርብ ግን፣ ሌሎች ሰዎች በግላቸው ሁለቱንም በጨረታ ያሸንፏቸው ነበር::

ቴዎድሮስ በልጅነታቸው ይይዙት የነበረው ጋሻ ምንም እንኳን በመጠነኛ ብር ቢለበድም፣ ጨረታው በጣም የተጋጋለ ነው የሆነው፤ ከአሰር ዶላር ጀምሮ በፍጥነት ወደ ሁለት መቶ ዶላር ከፍ ብሎ በመጨረሻ በኮሎኔል ፍሬዝር ተገዛ::

ሚስተር ሆልመስ፣ ብዙ የሚያዳኑ ንብረቶችን ማስቀረት ችሏል::

ጨረታው ሁለት ቀን ፈጀ:: ጠቅላላ ገቢው ወደ 5ሺ ፓውንድ ይጠጋል:: ይህ ገቢ፣ ለተመለመሉ መኮንኖችና ከበሽሎ ደቡብ ለሚገኙ ሰዎች ተከፋፈለ፤ እያንዳንዱ ሰው ከአራት ዶላሮች በላይ ሊያገኝ ችሏል::

ደላንታ በመጣን በአራተኛው ቀን ጥዋት፣ አስረኞቹ፣ በዛ "በአለም ምርጥ ሰው"፣ በኮሚሳሪያቱ በካፒቴን ኤሰ ሀላፊነት ወደ ቤታቸው መንገድ ጀምረዋል፡፡

ከደላንታ ካምፕ፣ ሌፍተናንት ጄኔራል ናፒየር፣ አንፀባራቂ የሆነውን የወታደራዊ መልከቱን ፃፈ፡፡ ይህ ሪፖረት፣ በመቅደላ ፊት ለፊት በፍጥነትና በሚገባ የተጠቃለለውን ሁኔታ ለመላው አለም እንዲታወቅ ያደረገበት ነው፡፡

## የሰር ሮበርት ናፒየር ወታደራዊ ሪፖርት
## የጠቅላይ ዕዝ ጽ/ቤት፣ ዋና ቢሮ፣ የእንጣሎ ካምፕ
## ግንቦት 12፣ 1868

ከቡር ፣ ሰር! ሚያዝያ 3፣ ዋድላ አፋፍ ላይ ካምፕ ባደረግሁበት ጊዜ፣ ከደላንታ አለቆች መልከት ደረሰኝ፤ በዚህ መልከትም፣ ቴዎድሮስ ከመቅደላ ተነስተው አሮጌ ሜዳ ላይ ካምፕ እንዳደረጉና ዘመቻ ለማድረግ እንዳሰቡ ነበር፡፡ ከእስረኞች የመጣው ደብዳቤም ራሴን እንድጠብቅ የሚያስጥንቅቅ ነበር፡፡ በብሪትሽ ሠራዊትና በደላንታ ሜዳ መሀል የ3400 ጫማ ጥልቀት ያለው የጀዳ ሸለቆ ይገኛል፡፡ የዚህ ማለፊያ ደግሞ ምቹ ስለሆነና በቀላሉም መመከት የሚቻል ስለሆነ፣ በጠላት ፊት ቦታውን ለመቆጣጠር፣ ያለ ከፍተኛ ጉዳት መደረግ የሚችል አልነበረም፡፡ ፈጣን የሆነ እንቅስቃሴ በማድረግም፣ አስራ ሰምንት ማይሎች በመጓዝ ጀዳን ተሻግሬ ደላንታ ሜዳ ላይ ካምፕ መሰረትኩ፡፡ በማይሎች የተጓዝነውን ርቀት መቁጠር፣ ብቻውን፣ በመንገዱ ላይ የተደረገውን ልፋትና ድከመት መግለፅ አይችልም፡፡ ከፍተኛ የሆኑ ዳገቶችና ቁልቁለቶች፣ ከመጠን በላይ የነበረው ሙቀት፣ ከባድ ሸከም ለተሸከሙት ወታደሮች ከፍተኛ ፈተና ነው የነበረው፡፡ ያም ሆኖ፣ ቴዎድሮስ በሸሎን አልተሻገሩም፤ ነገር ግን በበሸሎ ወንዝና በመቅደላ መሀከል የሚገኙ መንደሮችን ዘርፈውና አቃጥለው ነበር፤ እነዚህ መንደሮች ደግሞ በሌላ ጊዜ ለሳቸው ታማኞች ነበሩ[157]፡፡ ከደላንታ ሜዳ ሆኜ፣ ሩቅ ቢሆንም፣ ግልፅ በሆነ መንገድ መቅደላንና ወደመቅደላ የሚያደርሰውን አካባቢውን ማየት ቻልኩኝ፡፡ በጥሩ የሩቅ መነፅር (ቴሌስኮፕ)፣ የአካባቢውን አደገኛነት፣ የቦታውን ጠቅላላ አቀማመጥ ስለተረዳሁ፣ ጥቃቱን የተዋጣ ለማድረግ ማግኘት የምችለውን እግረኛ ጦር በሙሉ ማምጣት እንዳለብኝና፤ ጥቃቱ ውጤት እንዲኖረው ሁሉንም የፈረሰኛ ጦር ማሰለፍ እንዳለብኝ ተገነዘብኩ፡፡ ያም ሆኖ መሰብሰብ የምችለውን ጦር ባገኝም፣ ወደ መቅደላ ደቡብ በኩል ወዳለው ቃፊር በር ጥግ ድረስ ወታደሮች በረድፍ በመላከ ጥቃቱን መፈፀም እንደማልችል ተስምቶኛል፡፡ የመረጃ ከፍል መኮንን የነበረውን ሚር አከባር አሊን፣ ለወሎ

---

157 (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

አሮሞዎች ንግሥት፣ ለመስታውት መልከት እንዲወሰድ አዘዝኩት፡፡ በዚህ መንገድ፣ መስታውት ያለ የሌለ ሰዎቿን አስባስባ፣ ባለ ሀይሏ፣ በዚያ በኩል ያሉትን ማምለጫ ቦታዎች እንድትዘጋ ነበር፡፡ የሚር አከበር አሊ ሪፓርት አብሮ ይላካል፤ ሪፓርቱም እንዴት አድርጎ ተልኮውን በደንብ እንደተወጣ ያሳያል፡፡ መቅደላ አካባቢ ምንም አይነት መዘግየት እንዲፈጠር ፈቃደኛ ሰላልነበርኩ፣ ምሽጉን ለማጥቃት በሚደረገው ዘመቻ የሚያስፈልገኝን በቂ ቀለብ እስከምይዝ ድረስ ለብዙ ቀናት በሽሎን ሳልሻገር ለመቆየት ወሰንኩ፡፡ ያልተረጋገጉት የአቢሲኒያን ስዎች፣  በትንሹ የሚላኩ ወታደሮች ላይና ሰላማዊ ሁኔታ የሚያሳዩትን የኛን ወታደሮች ጥላቻ ሊያሳዩ እንደሚችሉም አልዘነጋሁም፡፡ ነገር ግን፣ የማጓጓዣው ክፍል የነበረበትን የተለያዩ ችግሮችና፣ በቂ የሆነ ቀለብም አለመኖሩ በበቂ የወታደሮች ቁጥር ቦታዎችን ለመያዝና በሚፈለገው መጠን ማጠናከር እንደማልችል አድርጎኛል፡፡ ያም ሆኖ፣ እያንዳንዱ ቀን ተጨማሪ ጥንካሬ እያመጣ ነበር፤ በመሀሉም፣ በተቻለኝ መጠን ነፃ በሆነ መንገድና በመደለልም ከተከዜ እስከ አንጣሎ ያሉት ትንንሽ ገዥዎች ወዳጅነታቸውን ጠብቀው የሀገሩን ተወላጆች ሰርዳታ እንዲልኩ አደርግ ነበር፡፡ ሁኔታው የተቃና እንዲሆን ያደረገውና የነበረው አማራጭ ይህ ነበር፡፡ ያለዕድል ሆኖ፣ ቢሰካም ሙሉ በሙሉ አልበረም፡፡ የኛ ዋናው ጦር በቦታው ስላልነበረና የነበረውም ጫና ስለቀነሰላቸው፣ በየቦታው ያሉ አለቆች፣ የኛን ጓዝ የሚጓጓዙ አቢሲኒያውያን ላይ ችግር መፍጠር ጀመሩ፡፡ በዚህም የኛ ጓዝና በየቦታው የተመደቡ ወታደሮች ላይ ጥቃት ጀመሩ፡፡ ሰለዚህ፣ በሀገሩ ተወላጆች፣ ከአንጣሎ ተነስቶ የሚመጣው ጓዝ በጣም በሚያስፈልግበት ወቅት እንዲቋረጥ ተደረገ፡፡ በዚህም የተነሳ፣ በሚያዝያ 4፣ መተማመን የምችልበት የነበረኝ ስንቅ ለጥቂት ቀናት ብቻ የሚሆን ነው የነበረው፡፡ ጦሩ ያለውን ጓዝ፣ ላት በሚባል ቦታ፣ ወደ ኋላ 100 ማይሎች ርቀት ላይ ጥሎ፣ ለዘመቻው የለበሰውን ብቻ ይዞ ነው የመጣው፤ ብርድልብሶች፣ ከባድ ኮትና ውሀ የማያስገባ እንሶላዎች የያዘው፡፡  ሌላ አማራጭም ሰላልነበረ፣ አንድ ድንኳን ለአስራ ሁለት መኮንኖች ወይም ለሀያ ወታደሮች እንዲጋሩ ተደረገ፤ በየቀኑ ያጋጠመን የዝናብ ወጀብ እነዚህን ድንኳኖች በጣም አስፈላጊ ሆነው እንዲገኙ አድርጓቸዋል፡፡ የማጓጓዣው ክፍልም፣ የማያስተማምኑ የሀገሩ ተወላጆች ጓዝ በሚይዙባቸው ቦታዎች ተልኮ ቀለብ እንዲያመጣ ታዘዘ፡፡ ይህ ደግሞ፣ በስንቅና ትጥቁ ክፍል ለነበረኝ ችግር መፍትሄ ተስፋ ሰጥቶኛል፤ ሆኖም አጣዳፊው የወቅቱ ሁኔታ ደግሞ ግፊት እየፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪ ሁለተኛ ሁኔታ፣ ብርጋዴር ጄኔራል መርዌዘር፣ ወደ ተከዜ ሄዶ፣ ከአለቆች ጋር በመነጋገር የዶቄት ቀለብ እንዲያቀርቡ እንዲያደርግ ወከልኩት፡፡ ሜጀር ግራንት ወደ ላት እንዲመለስ መመሪያ ተሠጠው፤ ካፒቴን ሞር፣ ወደ አሸንጌ ሀይቅ ሄዶ፣ በዚህ ቦታ የተፈጠሩ መሰናከሎችን እንዲያሰወግድ ታዘዘ፡፡ ካፒቴን ሰርዲና ሚስተር መንዚንጀርም፣ ካፒቴን ወደ ዳውንት፣ መንዚንጀር ቴዎድሮስ ወደ ሰበለቡት ወደ ደላንታ ደንበር ተላኩ፤ በነዚህ መኮንኖች ሥራ ምክንያት፣ ከብቶቹን መቀለብና፣ ለወታደሮች፣ ለእያንዳንዱ ወታደር 8 አውንስ ዶቄት፣ ለአስራ አንድ ቀን የሚሆን ቀለብ ማግኘት ቻልኩ፡፡ ያገሩ ተወላጅ የሆኑ ተከታዮች ግን በዶቄት ፋንታ ስንዴ እህሉን ተቀበሉ፡፡

የሚደነቅ ስሜት ባላቸው በኔ ሠራዊት በመተማመን፣ ይህን ያለኝን ቀለብ ወይም ሥንቅ በመያዝ መቅደላን ለማጥቃት ተዘጋጀሁ፡፡ እኔ ራሴ ካየሁት የመቅደላና የአካባቢው ዕይታ በተጨማሪ፣ በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ በቅርቡ ከመቅደላ ከድቶ የመጣ ቢትወደድ ሀይሉ[158] ከሚባል ሰው አገኘሁ፡፡ ቢትወደድ ሀይሉ፣ ከሸዋው ንጉሥ ከምኒልክ ጋር በመመሳጠሩ፣ ቴዎድሮስ ሲመለሱ ወዲያውኑ የሞት ቅጣት እንደሚያጋጥመው በደንብ አውቋል፡፡ ለማጥቃት የምናስበውን ይህን ሀይለኛ ቦታ በቂ ሀሳብ እንዲኖር በፅሁፍ ብቻ ለመግለፅ ይከብዳል፡፡

የመቅደላ ምሽግ፣ ከበሽሎ ወንዝ ዳርቻ በቀኝ በኩል አስራ ሁለት ማይሎች የሚሆን ይርቃል፡፡ ነገር ግን ያለው ትልቅ ከፍታና ጥርት ያለው አካባቢው ምሽጉን በደንብ ተለይቶ እንዲታይ አድርጎታል፡፡ የቦታው መሀል ቦታ ከባህር ወለል በላይ 9ሺ ጫማ ከፍታ ያለው የሰላሴ አለት ነው፡፡ ሰላሴ፣ ሰላምጌ የሚባል አምባ ሜዳ ላይ ነው የቆመው፡፡ ሰላሴ እንደገና፣ ከአለት በተፈጠሩ ቀጥ ያለ ግድግዳ ባላቸው ብዙ እርከኖች ይከፋፈላል፡፡ እነዚህ እርከኖች፣ ከፋላ ጋር የሚያገናኛቸው ጎድጎድ ያለ ቦታ አለ፡፡ ፋላ ግዙፍ የሆነ የተፈጥሮ መከላከያ ነው፣ እናቱ ጠፍጣፋ ሲሆን፣ ጠቅላላ ከፍት ሆኖ ከሰላምጌ በኩል መቆጣጠር ይቻላል፡፡ ወደ ሰላምጌ የሚወስዱ ማናቸውንም መንገዶች በ1200 ጫማዎች ከፍታ ያስፈራራል ወይም ይቆጣጠራል፡፡ ጎኖቹ ገደላማ ይመስላሉ፤ እናቱ ደግሞ በተፍጥሮ የአለት ስብርባሪዎች ተከቦ ከ18 እስከ ሀያ ጫማዎች ከፍታ ባላቸው ጥቂት ቦታዎች ብቻ ነበር መደፈር የሚቻለው፡፡ በፋላና በሰላሴ እንደምንም ተሸፍኖ፣ የመቅደላ እናት በአጋማሹ ነበር የሚታየው፡፡ ወደ መቅደላ የሚወስደው መንገድ፣ በገደላማው ፋላ ጎን ላይ ነው እየተጠማዘዘ የሚወጣው፤ ከፋላ ለሚተኮስ ተኩስ ክፍት ሆኖ ከዛም ለሚወርድ ድንጋይ ናዳ የተጋለጠ ነበር፡፡ የመንገዱ አንዱ በኩል በጣም ቀጥ ያለ ዳገት ስለሆነ፣ ጥቂት ፈረሶች ያውም የሀገሬው ርቢ የሆኑት ብቻ ናቸው የሚጋልቧቸውን ሰዎች ወደላይ ወደታች ማመላለስ የሚችሉት፡፡ ጠቅላላው መንገዱ እንዳለ በጎኑ በሰላሴ ጠርዝና ሰፋ ባለው በሰላምጌ ከፍል የታቀፈ ነው፡፡ በጠቅላላው፣ መቅደላን ሳይጨምር፣ ለመከላከያነት ያለው ባህሪ፣ የውጭ ሥራው ካሰበነውና ጠለቅ ያላለ ስለቦታው በደረስን ገለፃ ምክንያት ከጠበቅነው በላይ ነበር፡፡ የከዳው አለቃ፣ ቢትወደድ ሀይሉ፣ ትግስት አጥሮት፣ ከመቅደላ በደቡብ በኩል፣ በቃፊር በር፣ ላንታ ከሚባል ከፍታ ትይዩ እንድሞክር እንዲህ አለ፤ "ሰላሴን መያዝ ከፈለግህ በዚህ በኩል ሂድ፣ ነገር ግን መቅደላ መያዝ ከፈለግህ በላንታ በኩል መሄድ አለብህ፡" ነገር ግን፣ ይህ መሆንም የሚችል አልነበረም፡፡ ለማከፋፈል በቂ የጦር ሀይልም አልነበረኝም፡፡ እንደዚህ ያለውን ሰፊ የተፈጥሮ ምሽጎች ስብስብ፣ በኔና በጦሩ ግንኙነት መስመር መሀል እንዲሆን አልፈለግሁም፡፡ ያሰብኩት ደግሞ፣ እውነተኛው አላማ መቅደላን መያዝ ሳይሆን፣ ቴዎድሮስ ሁሉንም መድፎቻቸውን የደረደሩበት ቦታ ስለሆነ ሰላምጌን ነው፡፡ ስለዚህ ፋላ ለሁሉም ቁልፍ ነው፡፡

---

158 (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

በሚያዝያ 7፣ ወደ በሽሎ ወንዝ ወለል ወርጄ መሻገሪያውን ቃኘሁ፡፡ ወደ መቅደላ መሄጃ መደበኛው መንገድ በአሮጌ ሸለቆ በኩል ነው፤ ይህ ደግሞ ከሰላምጌ ግርጌ በቀኝ በኩል ባለ ወጣ ያለ ክፍል ጋር ይገናኝና ከሰላምጌ ተነስቶ በሸሎ ድረስ በሚወርድ ጎርባጣ ኮረብታ ይራዘማል፡፡ ተመሳሳይ ኮረብታ፣ ከፋላ ተነስቶ እስከ ወንዙ ድረስ ይወረድና ሸለቆውን በግራ በኩል ይዋሰነዋል፡፡ የዚህ ኮረብታ ከፍተኛ ቦታው ከአሮጌ ሸለቆ ወለል ወደላይ 2ሺ ጫማ ይሆናል፡፡ የቦታው ትልቅነት፣ የሸለቆውን ሁለት ጎን በጥቂት አግረኞች ለመያዝ የማይሆን ነው ያደረገብኝ፡፡ የዚህ ሁሉ ቁልፍ ፋላ ነው ብዬ ስለወሰንኩ ኮረብታውን ለመያዝ ወሰንኩኝ፤ ይህም፣ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች፣ ወደዚህ እስቸጋሪ ተፈጥሮ በሚመሩ በጊመቦርጊና እፍጃ በሚባሉ በኩል ነበር፡፡ እዚህ ኮረብታ ላይ ከሆንኩ፣ በፋላ በሁለቱም በኩል መንቀሳቀስ እችላለሁ፤ ቀረብ ብሎ በማስተዋል፣ ይህ አስፈላጊ ሆኖ ነው የተገኘው፡፡

በአራተኛውና በዘጠነኛው እንቅስቃሴ መሀከል፣ የኔ ጦር፣ ሌተናንት ኮሎኔል ፓሪሽ ከሚመራው 45ኛው ሬጀመንት በመጡ በስድስት ኮምፓኒዎች ጨምሯል፡፡ ይህ ሬጅመንት ለማጓጓዝ ሲባል ወደ ኋላ ተንትቶ ስለነበር፣ ከዙላ ተነስቶ የሀያ እምስት ቀን ጉዞ አድርጓል፡፡ የ3ኛው የቦምቤይ ክንፍ፣ ቁጥር 1፣ በኮሎኔል ካምቤል የሚመራ ለአጣዳፊው የማጓጓዝ ተግባር ሲባል የሰባት ቀን ጉዞ ያክል መንገድ ወደ ኋላ ቀርቷል፤ ስለዚህ ጥቃቱን ለመፈፀም ዕቅድ ውስጥ ያስገባኋቸው የተዋጣለት መኮንንና በጣም ጎበዝ የሆኑ ወታደሮች አገልግሎት እጥቼያለሁ፡፡

በሚያዝያ 9፣ ሁሉም ሠራዊት ከስሩ የሚወርደውን በሸሎ ወንዝን ቁልቁል ማየት ከሚቻልበት፣ በ3900 ጫማዎች ከፍታ ላይ ከሚገኘው ደልዳላ ቦታ ጠርዝ ላይ ሠፈረ፡፡ ሜጀር ቻምበርሲን ከ23ኛው የፑንጃብ ቃኝ ጦር ጋር፣ ከበሎቺ ክንፍ ድጋፍ በማግኘት የበሸሎን ወለል በመቆጣጠር የቴዎድሮስን መንገድ ጠገ፡፡ 10ኛው ሮያል ኢንጂነርስ ኮምፓኒ ሬዲዮ ክፍል ደግሞ ግንኙነቱ እንዲቀጥል አደረገ፡፡ በካፒቴን ጉድፌሎው የሚመራው የሮያል ኢንጅነርስና የማደራስና በምቤይ ምሽግ ሠሪዎች፣ የሚያስፈልገውን የእሸዋ ከረጢት፣ መሰላል፣ መግቢያ በሮችን ለመደርመስ በባሩድ የተሞሉ ከረጢቶችንና ሌሎቹንም ነገር አዘጋጀ፡፡ በመቅደላና በበሸሎ መሀከል የነበረው ብቸኛ ውሀ ማመላለሻ መስመር በጠላት ተኩስ ከልል ስር ስለሆነ፣ ሁሉም የሠራዊቱ ውሀ ተሸካሚ ከፍሎች በትራንስፖርቱ ክፍል በካፒቴን ቤይንብሪጅ መሪነት ከሁለት ረዳት መኮንኖችና ከትራንስፖርት ክፍሉ ሉተናንት ራመስበተም ጋር በመሆን ተደራጅቶ፣ ሥራው፣ ከበሸሎ ወደላይ ውሃ እንዲመላለስ ማድረግ ነበር፡፡ ከፑንጃብ ጋማ ከብት መሪዎች የተወሰነ ቡድን በካፒቴን ግሪፍት መሪነት፣ ከትራንስፖርት ከፍሉ ሉተናንት ጋሰሊ ረዳትነት ተደራጅተው በጦር ሜዳው የቆሰሉ ሰዎችን ማመላለሻ ቃሬዛዎች ተሠጣቸው፡፡ ይህ ሁሉ ዝግጅት ከጠናቀቀ በኋላ፣ በኮሎኔል ግሬቭስ የሚመራ ፈረሰኛ በሸሎን እንዲይዝ አደረግሁ፤ ነገር ግን አስፈላጊ ሲሆን ወደፊት ለመንቀሳቀስ እንደሚችል ሆኖ ነው፤ የቀረው ሀይል፣ በሰር ቻርልስ ስታቭሊ ቀጥታ ትዛዝ በሸሎን እንዲያቋርጥ አደረግሁኝ፡፡ ሁለተኛው ብርጌድ፣ በብርጋዴር ጄኔራል ዊልቢይ እዛዥነት፣ ለርዳታ በሸሎ ወንዝ ወለል እንዲቆይ ተደረገ፡፡ 1ኛው ብርጌድ፣ በጄኔራል ስናይደር መሪነት፣ የጊምቦርጊን ኮረብታ እንዲይዝና ለካምፕ የሚመች ቦታ

ለመምረጥ ወደፊት እንዲገሰግስ፤ በተጨማሪም በምክትሉ የሰንቅና ትጥቅ ክፍሉ ሀላፊ የሚመራውን የጠላትን ቦታ ለሚቃኘው ክፍል ሽፋን እንዲሠጥ ተደረገ:: የሰንቅና ትጥቅ ክፍሉ ምክትል ባቀረበው ሪፖርት፣ ወደጊምቦርጊ መውጫው በጣም ቀጥ ያለ ሰለሆነ አስቸጋሪ ነው፤ ስለዚህ ንጉሡ የሠሩት፣ በአሮጌ ሸለቆ የሚያልፈው መንገድ ቀለል ያለና፣ የተራራ መድፎችንም ሆነ ዓዝ ለማመላለስ አያሰጋም አለ:: በዚህም ምክንያት የንጉሡን መንገድ ተከትለው እንዲሄዱ ታዘዙ::

የተጓዡ ቀዳሚው ረድፍ አፍጀ ሲደርስ፣ እኔም ከፊት ደረስኩ:: የንጉሡ መንገድ፣ ከአሮጌ ማለፊያ የሚጀመረው ከአፊጆ 1200 ያርዶች ርቀትና 700 ጫማዎች ዝቅ ብሎ ነው:: የሜጀር ቻምበርሌን የፑንጃብ ቃኝ ክፍሎች ወዲያውኑ ተልከው የማለፊያውን አናት እንዲጠብቁ አዘዝኩ፤ ቀሪው የብርጌዱ ክፍል ደግሞ በተቻለ ፍጥነት እንዲሰባሰብ ተደረገ:: ሜጀር ቻምበርሌን ቦታውን እንደያዘ ወዲያውኑ፣ በካፒቴን ፊሎውስ የሚመራው የባህር ሀይሉ የሮኬት ብርጌድ፣ ማለፊያውን ተሻግሮ ብቅ አለ:: እነሱን ተከትሎ፣ የኮሎኔል ፔን ከባድ መሳሪያ ክፍል በአግረኛ ጦር ታጅቦ መጣ:: በዚህ ወቅት፣ ጠላት፣ ከፋላና ከሰላምጌ በኩል ተኩስ ከፈተ፣ ያነጣጠረውም ፑንጃቦችና አፊጆ ላይ ነበር:: ያለው ርቀት 3ሺ ያርዶች ቢሆንም፣ የጠላት ተኩስ በትክክለ አላማው ላይ መድረስ ችሏል:: ይህም በትክክል በመተኮሱና ምናልባትም ከመጠን በላይ ባሩድ ስለተጠቀሙ ይሆናል፤ ነገር ግን አሩሩ ዝምብሎ የሚወድቅ አይነት ብቻ ስለሆነ ማንም ሰው አልተጎዳም:: ከጠላት መድፍ ተኩስ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ፣ ብዛት ያለው ሠራዊት ከሰላምጌ ተነስቶ በፋላ ጎን ሲወርድ ታየ፤ በቁልቁለቱና በተራራው በፍጥነት ወርደው አሮጌን አጥለቀለቁት:: ብዙዎቹ የጠላት ወታደሮች ቀይ ለብሰዋል፣ እናም ከሩቅ ሲታይ ከኛ ወታደሮች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ፈጥረዋል:: አምስት መቶ የሚሆኑት አለቆች ፈረስ ላይ ናቸው:: የባህር ሀይሉ ብርጌድ ተጣድፎ አፊጆ ላይ ከወጣ በኋላ፣ እያንዳንዱ የሮኬት ቱቦ እንደተዘጋጀ፣ የሚገሰግሰው የጠላት ጦር ላይ ተተኮሰ፤ የጠላት ጦርም በመደናገጥ አንደመቆም አለና አንዳንድ ቦታም ወደኋላ አፈገፈገ፤ ነገር ግን፣ በሌላ አቅጣጫ ባሉት ወደሌሎቹ፣ ወደፊት መገስገሰ ቀጠለ:: ሰር ቻርለሰ ስታቭሊን፣ በዚህ ጊዜ፣ ተጠግቶ የነበረውን ቀሪውን እግረኛ ክፍል ወደፊት እንዲያመጣና ጥቃቱን እንዲመክት መመሪያ ሠጠሁ:: 4ኛው ሬጅመንት (የንጉሡ) በኮሎኔል ካሜሩን ስር፣ እነሱን ተከትሎ ደግሞ የበቪሊ ቤሉቺዎችና በሜጀር ፕሪቻርድ የሚመሩት ሮያል ኢንጂነርስ፣ በካፒቴን መዶነል የሚመሩት የቦምቤይ ምሽግ ሠሪዎች፣ በፍጥነት የቁልቁለቱን መንገድ ይዘው ወደ አሮጌ ሜዳ ወረዱ:: በመጨረሻም ጠላትን ከፊትለፊታቸው ማየት በመቻላቸው ያልተገደበ የደስታ ስሜት ነው የፈጠረባቸው:: ለማጥቃት በዝግጁ ሁኔታ ከአሮጌ የሚለያቸው ትንሽ ዳገት ላይ ወጡ፤ ወዲያውኑም ከጠላት ጋር ተገናኙ፤ የአለቆቻቸው ከፍተኛ ጥረት ቢኖርም፣ የጠላት ወታደሮችን እንዳለ ወደ ኋላ መግፋት ቻሉ:: ይህም የሆነው የሰናየደር ጠምንጃዎች ተኩስ ባሳየው አስከፊ ውጤት ነው:: ጀግንነት የተሞላበት ብዙ ሙከራ በአቢሲኒያውያን ተደርጎ ነበር፣ ነገር ግን ብዙዎቹ አለቆቻቸው ወደቁ፤ እናም ከኛ በግራ በኩል ወደሚገኘው ወደ አሮጌ ሸለቆ ቁልቁለቱን ለመውረድ ተገደዱ:: የተወሰኑት ደግሞ ወደላይ ወደፋላ ጎን አፈገፈግው

በቁልቋል ቁጥቋጦች ጀርባ ተከለሉ፤ ከዚያም ሆነው፣ በስታሽሊ ቀኝ በኩል በሚተኩሱት ተኩስ ጉዳት አደረሱ:: ካፒቴን ፌሎውስ ቀድሞ በሚደርሰው እግረኛ እስኪሸፈን ድረስ ሮኬቶቹን ሲተኩስ ነበር:: ከዛም ለሰር ቻርለስ ስታቨሊ ርዳታ እንዲያደርግ ተላከ:: የሮኬቶቹ ተኩስ፣ የበሺሊ ቤሎቺዎች ከሚተኩሱት ተኩስ ጋራ የሮያል ኢንጂነርስ በሉተናንት ቴይለር ስር ባሉ ሁለት ከባድ መሳሪያዎች እገዛ ተደርጎላቸው፣ በስታሽሊ ጎን የነበረውን ጠላት በማጥራት የተፈጠረውን ችግር አስወገዱት:: ከዚህ በኋላ ሮኬቶቹ ፋላ ላይ እንዲያነጣጥሩ ተደረጉ፤ በኋላ እንደተረዳሁት፣ በጣም ጥሩ ውጤት ነበር ያስገኙት:: የጠላት የተወሰኑ ወታደሮች ቡድን በአፊጆ በኩል ለማለፍና፣ በኛ በቀኛችን በኩል ለመዞር ሞከሮ ነበር፤ ነገር ግን በጥቂት ሮኬቶች ተገድቦ፣ በ ኬ ኮምፓኒ፣ በማዳራስ ምሽግ ሠሪዎች በሜጀር ፕረንደርጋሰት መሪነት፣ ሌፍተናንት ኮሎኔል ሎች ከ3ኛው በምቤ ፈረሰኛ ከፍል ጋር በመሆን እናም የእግረኛ ርዳታ ተጨምሮበት ሰዎቹ ተበተኑ:: ወደ ግራ በኩል፣ ኮሎኔል ሚልዋርድ፣ ከፔን ከባድ መሳሪያ ጋር በመሆን በ4ኛው (የንጉሡ) ሬጅመንት ከፍል በካፒቴን ኪቶ መሪነት ታጅቦ፣ የ23ኛው ቃኝ ጦር በካፒቴን ፒተርሰን መሪነት ተደምሮ፣ መድፎች ከፋላና ከሰላምጌ ተኩስ በጀመሩበት ሰአት፣ ከአሮጌ ማለፊያ ተነሱቶ ወደላይ እየወጣ ነበር::

የቴዎድሮስ ወታደሮች ከሰላምጌ እየወረዱ መምጣታቸውን ሲመለከት፣ ኮሎኔል ሚልዋርድ፣ ጠንካራ ቦታ ላይ በመሆን በፔን ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ ከፈተ:: ማለፊያውን ለመሸፈን ቃኝ ጦሩን ይዞ የነበረው ሜጀር ቻምበርሌን ወደግራው በመንቀሳቀስ ኮሌኔል ሚልዋርድን ተቀላቀለ:: ብዛት ያላቸው አቢሲኒያውያን ሚልዋርድ ወዳለበት ቦታ እየገሰገሱ ነበር:: በፔን ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ ይደርስ በነበረው ጉዳት ሳይበገሩ፣ በቆራጥነትና በሥርአት ወደፊት ይገሰግሉ ነበር:: ቻምበርሌን ከቃኝ ጦሩ ጋር በመሆን ይህንን ጥቃት በፍጥነትና በወኔ ነበር የተጋፈጠው፤ ብዙ እልቂት በማድረሰም፣ ሰዎቹን በግራ በኩል ፊት ለፊት ወዳለው ሸለቆ ገፋቸው:: ያም ሆኖ ግን ከአቢሲኒያኖች በኩል ጀግንነት የተሞላበት መከላከል በማድረግ ያለምንም ፍርሀት ከፑንጃቢዎች ጋር ጨበጣ ውጊያ አደርገው ነው:: በጦር መወጋት ምክንያት የታዩት ቁስሎች ምን ያህል ተጠጋግተው እንደተዋጉ ምስከርነት ይሰጣሉ:: ራቅ ባለው በግራ በኩል፣ ጠላት፣ ብዛት ባለው ሀይል ወደ አሮጌ ሸለቆ መግቢያ በኩል እየገፋ ነበር:: በዚያ በኩል ደግሞ ጓዝ እየደረሰ ነበር:: የጓዙ ኃላፊ፣ የ4ኛው (የንጉሡ) ሬጅመንት ሉተናንት ሰዊኒ፣ በከፍተኛ ዝግጅት ጓዙን በማያሰጋ ቦታ ከመረ:: ጓዙን ጠባቂዎች፣ ሁለት ኮምፓኒዎች ከ4ኛው፣ አንድ ከ10ኛው ሬጅመንት የተውጣጡ፣ በካፒተን ሮበርት ስር በመጀመሪያ፣ ከዛም ሲጎዳ ከ11ኛው (ሁሳርስ) ሉተናንት አባዲ መሪነትና ስዊኒ ጋር በመሆን ወደፊት በመምጣት፣ ጠላት ወደ አሮጌ ሸለቆ እንዳይወርድ በሚገባ ተከላከለው ጠበቁ:: በአሮጌ ሸለቆ መግቢያ ላይ እንዲቆሙ ተደርገው፣ ከዛም በጓዝ ጠባቂዎች ወደኋላ ተገፍተው፣ በቻምበርሌን ቃኝ ጦርና ከ4ኛው ከመጡት ሰታቨሊ በጎናቸው በኩል ባዞረባቸው በሁለቱ ካምፓኒዎች ተከበው፣ የጠላት ተዋጊዎች ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባቸው:: ቁጥራቸው በርከት ያሉት፣ በቀጥታ በሚተኮስባቸው የተራራ መድፎች ተመተው ሲወድቁ ይታያሉ:: የቴዎድሮስ

ወታደሮች ማሸነፍ የለመዱ ስለሆነ በሙሉ ልብ ነበር ወደፊት የገሰገሱት፡፡ ከነበሩበት ጥሩ መከላከያ ቦታቸው፣ ራሳቸውን አውርደው መመለሻ ወደሌለበት ቦታ ገብተዋል፡፡ በቴዎድሮስ ቃል የተገባላቸው፣ ከእንግሊዞቹ የማረኩት ነገር የራሳቸው እንደሚሆን ነበር፤ በመጨረሻም ከሜዳው ተገፍተው ቢሄዱም ጠንካራ ፍትጊያ ሳያደርጉ ቀርተው አልነበረም፡፡

በዚህ ውጊያ፣ በአብዛኛው ወቅት ከባድ ዝናብ እየወረደ ነበር፡፡ ወታደሮቹ በዝናብ ርሰውና ደክመው ነበር፤ ሆኖም ባገኙት ድል ስሜታቸው በጣም ከፍ ብሎ ስለነበር ለእዳሩ ካምፕ መፈለግ ጀመሩ፡፡ ወደ አሮጌ ማለፊያ የሚወስደውን መንገድ ተቆጣጥረው፣ ሳይመሽ፣ የአቢሲኒያን ወታደሮች ለመግጠም ወርደው የመጡበትን የአፍጀ ከፍታን መልሰው ያዙ፡፡ የቆሰሉት፣ በሆስፒታሉ ሀላፊ በዶክተር ቸሪ መሪነት እርዳታ ተሰጣቸው፡፡ ብዙ የቆሰሉ አቢሲኒያውያንም ቢሆን፣ በኛ ወታደሮች ከጦር ሜዳው ወደ ሆስፒታሉ ተወስደው እርዳታ እንዲሠጣቸው ተደረገ፡፡ ማምሻውን የደረሰው 2ኛው ብርጌድ፣ በ1ኛው ብርጌድ በውጊያ የተያዘውን ቦታ ተረከበ፡፡ በነበረን የተቻለ መረጃ፣ የአቢሲኒያ ተዋጊዎች ቁጥር ግምት ከአምስት ሺ ያላነሰ ነበር፤ ሶስት ሺ የሚሆኑት ጠመንጃ የያዙ ሲሆን፣ ሌሎቹ ግን ከዛ ባነሰ ሁኔታ ነው የታጠቁት፡፡ ከውጊያው አንድ ቀን ቀደም ብሎ፣ ቴዎድሮስ አዲስ ጠመንጃዎችን ለወታደሮቹ አድለው ነበር፡፡ በጠላት በኩል የደረሰው ጉዳት በትክክል ሊገመት አይችልም፤ 349 የሞቱ ሰዎች ከፊት ለፊታችን በግራ በኩል ባለው ቦታ ተቀበሩ፡፡ እነዚህ፣ ሁሉም የወደቁት በስታሸሊ የመጀመሪያው ጥቃት ነበር፡፡ በጣም የቆሰሉ ሰላሳ አቢሲኒያውያን ወደ ሆስፒታሉ ተወስደዋል፡፡ የቴዎድሮስ የጦር አበጋዝ፣ ፊታውራሪ ገብርዬና ሌሎችም የሚታወቁ አለቆች ከወደቁት መሀል ነበሩ፡፡ ሌሊቱን፣ የወደቁ ጓደኞቻቸውን የሚጠሩ የአቢሲኒያውያን ጩኸት ይሰማ ነበር፤ ብዛት ያላቸው የቆሰሉ ሰዎችም ከውጊያ ሜዳው ተወስደዋል፡፡ የቴዎድሮስ ወታደሮች እጃቸውን በሠጡበት ወቅት ብዛት ያላቸው የቆሰሉ ሰዎች አይተናል፡፡ የብሪታንያ ጉዳት ደግሞ ሀያ ብቻ የቆሰሉ ሲሆን ሁለቱ ሞተዋል፡፡ የዚህ የጉዳት ልዩነት የመጣው፣ አቢሲኒያኖቹ ባደረጉት ቆራጥ የሆነ ያልተቋረጠ፣ በደንብ በስነ ሥርአት ከተደራጀና በበለጠ ሁኔታ ከታጠቀ ወታደር ላይ ባደረጉት ጥቃት ነው፡፡ የ23ኛው ቃኝ ወታደሮች ከታጠቁት መሳሪያ ጋር ሲወዳደር እንኳን የበለጠ ታጠቁ ማለት አይቻልም፡፡ 23ኛው የታጠቀው ጠመንጃ አቢሲኒያኖች ከያዙት ባለሁለት አፈሙዝ ጠምንጃ ጋር አይወዳደርም ነበር፡፡ ያልተጣደፈ ውጊያ ነበር፤ የጠላት ወታደሮች በየትኛው ባገኙት የተመቸ ቦታ ለማጥቃት ይመለሱ ነበር፡፡ እኔም የጠላት ወታደሮችን ወደላይ ወደከፍታው ማሳደድ እንዲቆም ትዛዝ ሠጠሁ፤ ምክንያቱም የመጨረሻው ውጤት የኛ ወታደሮች ወደ ቦታቸው መመለስ ስለሆነ፣ ይህ ደግሞ አዲስ የጉልበት ስሜት በጠላት ወታደሮች እንዳይፈጥር ነበር፡፡

በ11፣ በጠዋት፣ ሉተናንት ፕሪዶና ሚስተር ፍላድ በደጃች አለሜ ታጅበው ወደኔ ካምፕ መጡ፡፡ ደጃች አለሜ የአፄ ቴዎድሮስ ታማኝና አማችም ናቸው፤ ሁሉም የመጡት የሰላም ጥያቄ ይዘው ነው፡፡ እኔ ስመልስም፣ ቴዎድሮስ፣ ሁሉንም እስረኞች የሚለቁ ከሆነና፣ ራሳቸውም ለእንግሊዝ ንግሥት እጃቸውን የሚሠጡ ከሆነ፣

ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚገባውን ክብር ለመሥጠት ቃል እንደምገባ ነው፡፡ ሉተናንት ፕሩዶ፣ የዚህን ቃል የያዘውን ደብዳቤ ይዞ ወደ መቅደላ ተመለሰ፡፡ እኩለ ቀን ሲሆን ግን፣ ደጃች አለሜ ቀርተው፣ ከሚስተር ፍላድ ጋር በመሆን ወደ እንግሊዝ ካምፕ ተመለሱ፡፡ ያመጣው ደብዳቤ፣ የቴዎድሮስ ፊርማ ወይም ማህተም የሌለበት ሲሆን እኔ ያቀረብኩትን ጥያቄ የማይቀበል ነው፡፡ እኔም ደብዳቤዬን መልሼ ላኩኝ፡፡ ሉተናንት ፕሪዶና ሚስትር ፍላድን፣ ከዚህ ውጭ ሌላ ድርድር እንደሌለ እንዲያስታውቁ መልሼ ላኳቸው፡፡ እኔ የወሰንኩት፣ እስረኞችን መረከብ ብቻ ሳይሆን፣ ሙሉ ቅጣት፣ በተለይም እስረኞች ከቁጥጥር ነፃ ከሆኑ በኋላ፣ በፍፁም አስፈላጊና መፈፀምም ያለበት ነገር ነው፡፡ ቴዎድሮስ ተበሳጭተው በእስረኞች ላይ ሊፈፅሙ የሚችሉትን ማሰብ በጣም የሚያም ነገር ነው፤ የነሱን ደህንነት ለማስጠበቅ የተማመንኩበት ነገር፣ የቴዎድሮስ ወታደሮች ድል የተመቱበተንና ሞራላቸውን የገደለውን ግጭት ሁኔታ እንደ አዲስ መቀሰቀስ ነው፤ በዚህም ቴዎድሮስ ራሳቸው ነፃ አይሆኑም፤ ያሰፍላጎታቸው ደጃች አለሜ ቴዎድሮስን መከዳታቸውን ማስታወስ ነበረብኝ፡፡ በሌላ ወገን፣ ደጃች አለሜን ማሳመን በቻልኩበት በማስፈራሪዬ ተማምንኩኝ፤ በዚህም፣ ማንም እውሮፓውያኑ ላይ የሚጎዳ ነገር ያደረገው ሰው ላይ የማይታከት ማሳደድ አንደማደርግና አንደምቀጣ ገልጫለሁ፡፡ የእንግሊዘ ሀይል መቅደላ መድረሉንም በመጠቆም፣ ልንቀጣው የፈለግነው ሰው የቱንም ያህል ሩቅ ቢሆንም በማንኛውም የአቢሲኒያ ማዕዘን ተደብቆ ሊያመልጥ እንደማይችል ገለጥኩ፡፡

ሉተናንት ፕሪዶ ወደ መቅደላ ሲመለስ፣ በመንገድ ላይ፣ ከራሳምና ከቀሪዎቹ የእንግሊዝ እስረኞችና ከሌሎች ከተለያዩ ሀገራት አስረኞች ጋር ተገናኙ፡፡ ማምሻውኑ ሁሉም እስረኞች የኔ ካምፕ ደረሱ፡፡ በደጃች አለሜ ጥያቄ መሠረትና በገባሁት ቃል ለሀያ እራት ሰአታት ምንም አይነት የማጥቃት አንቅስቃሴ ከማድረግ ተቆጠብኩ፡፡ እርባ ስምንት ሰአታት እንዳለፉ፣ ቴዎድሮስ እጃቸውን አልሠጡም፡፡ በደረሰኝ አስተማማኝ መረጃ፣ የቴዎድሮስ ወታደሮች ከደረሰባቸው ሽንፈት እያገገሙ ነው፡፡ በ10፣ በማታ፣ መቅደላ መድረስ ያልቻሉ ወታደሮች ተመልሰው ከጦሩ ጋር ተቀላቅለዋል፤ አዲስ የመከላከያ እደረጃጀቶች እየተደረጉ ነው፡፡ ከዚያም ጋር፣ ቴዎድሮሰና የጦር እለቆቻቸው፣ ከታች ከደልዳለው ቦታ በሰፈረው በ2ኛው ብርጌድ ላይ ሌሊት ጥቃት ለማድረስ እያሰቡ አንደሆን ነው፡፡ ስለዚህ እኔም የጠላትን ቦታ ለማጥቃት መዘጋጀት ጀመርኩኝ፡፡ መጀመሪያ ያሰብኩት፣ በካምፓችን ፊት ለፊት ያለውን ፋላን ከሰላምጌና ከስላሴ የሚመጣውን ተኩሰ በሚከልል ሁኔታ ከጎን በኩል ለማጥቃት ነበር፡፡ ሆኖም ጠላት ላይ በደረሰው ለውጥ ምክንያት፣ ቴዎድሮስ፣ በመቁሰል፣ በሞትና በመከዳት ከነበራቸው ጦርና ጀግኖች እለቆቻቸውን ግማሹን ሰላጡ፣ ሰላምጌን በንጉሡ መንገድ በኩል ለማጥቃት ወሰንኩ፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገው ዝግጅትም ተጠናቆ፣ ለከባድ መሳሪያዎችም ቦታ ተቀይሮና ከተጠመዱ በኋላ፣ የመጣልኝ ዜና፣ ቴዎድሮስ መቅደላን ለቀው ሄደዋል እናም ብዙ እለቆቻቸው

ከነተከታዮቻቸው እጃቸውን መስጠት ይፈልጋሉ ነበር[159]:: እጅ መስጠቱን ተስማምቼበት፣ ሰር ቻርለስ ስታቨሊን ጥንቃቄ ሳይጎድል ከዚህ ቀደም የታቀደው ዕቅድ እንዳለ ወደ ሰላምጌ እንዲገፋ አዘዝኩ::

የነበረው የውሀ እጥረት፣ መቅደላ ፊት ለፊት የሚበቃ የፈረሰኛ ሀይል ሊያስቆም አልቻለም:: በህንድ መኮንን ስር የነበረው የራሴ የግል አጃቢ ቡድን ብቻ ነው የቀረው:: የተወሰኑ የሌላ ክፍሎች በሉተናንት ስኮት እየተመሩ የመቅደላን የምዕራብ ጎን እንዲጠብቁ ተላኩ፤ እነሱም፣ የቃፊር በር ግዳጁን ፊፅሞ የሚመለሰውን በኮሎኔል ግሪቭስ የሚመራው ፈረሰኛ እስኪመለስ ድረስ ጥሩ ቦታ ሆነው ነበር:: ቃፊር በር በኦሮሞዎቹ እየተጠበቀ ነበር:: ከጠቅላይ ጽ/ቤቱ ፈረሰኛ ስንዲ ሆርስ በሜጀር ብሪግስ፣ ከ3ኛው ድራጎን ዘቦች አንድ ክፍል፣ ከ3ኛውና 12ኛው ፈረሰኛ በሜጀር ሚለር ስር በሸሎ ላይ ቁልፍ ቦታ ይዞ ይጠበቅ ነበር፤ በምንጀራ ሸለቆ በኩል ጠላት እንዳይሸሽ ለመዝጋት ነው:: በሉተናንት ቡቨሊ የሚመራ የበሉችዎች አንድ ክፍል፣ በፋላ ኮረብታ በኩል፣ ወደላይ ወጥቶ በጣም ወሳኝ የሆነ ቦታ ያዘ፤ በኮሎኔል ፊልድ ስር ከዕዝ ጽ/ቤቱ የ10ኛው ከንፍ ተጨማሪ ማጠናከሪያ ድጋፍ ተጨመረላቸው:: መድፎቹ በቦታ ከተጠመዱ በኋላ፣ እግረኛው ወደፊት ቀጠለ፤ ይህም ክፍል፣ በመረጃ ክፍሉ በካፒቴን ስፒዲ፣ ከ3ኛው ቀላል ፈረሰኛ በኮሎኔል ሎች መሪነት ታጅቦ ቀደም ብሎ እየመራ ነበር:: እነዚህ የተላኩት፣ እጃችን እንሰጣለን ካሉት አለቆች ጋር ግራ መጋባት እንዳይፈጠር ለመነጋገር ነበር:: ምንም አይነት የመከላከል ሁኔታ አልታየም:: ሰር ቻርልስ ስታቨሊ፣ በአስቸጋሪ የአለት ክፍተት በኩል ወደ ሰላሴና ሰላምጌ መግቢያ መድረስ ችሏል:: በሰላምጌ ፣ መሳሪያቸውን አውርደው እጃቸውን የሠጡ የታጠቁ ተዋጊዎችን ቁጥርና በሰፍራው የተገኘውን ህዝብ፣ ማለትም፣ ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት ቁጥር በትክክል መገመት ያስቸግራል:: የተማረኩ ጠመንጃዎችን መሰብሰብና መጠበቅ አስፈላጊ ነበር:: ወደ መቅደላ እንቅስቃሴ ከመጀመሬ በፊት፣ እጃቸውን የሠጡትን ወታደሮችና የተከተሏቸውን ሰዎች ወደታች ወደሜዳው መውሰድ አስፈላጊ ነበር:: ቴዎድሮስ ራሳቸው፣ ለማምለጥ ምንም ሙከራ ሳያደርጉ፣ ለመከላከል በመዘጋጀት በመቅደላ ፊት ለፊት በአልበገር ባይነት እየተፈታተኑን ነበር:: ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን፣ ሁሉም ሰው ሰላምጌን ከለቀቀ በኋላ፣ መቅደላ ላይ ወዲያውኑ ጥቃት እንዲጀመር ትዛዝ ሰጠሁ:: ወደ መቅደላ መግቢያው፣ ከሰላምጌ ወለል በ300 ጫማዎች ከፍ ይላል:: ዳገቱም በጣም ቀጥ ያለና መንገዱም የማይመች ነበር:: የመግቢያውን አስቸጋሪነት ካየሁ በኋላ ጥቃቱ በተቻለ መጠን ከፍተኛና ጠንካራ እንዲሆን አደረግሁ:: ያለኝን ከባድ መሳሪያ በሙሉ በቦታው ላይ እንዲያነጣጥርና እንዲሸፍን በማድረግ የጠላትን የመከላከል ችሎታ ለማዳከም ነበር፤ በዚህም ሊደረስ ይችል የነበረውን የሰው ጉዳት ለመቀነስ ነበር:: የአጥቂው ሀይል የተውጣጣው፣ 2ኛው ብርጌድ በ33ኛው (የመስፍኑ) ሬጅመንት በመመራት፣ ከሮያል ኢንጂነርስ፣ ከማዳራስና በምቤይ ግንበኛና ምሽግ ቆፋሪዎች ጋር ነበር:: የኃለኞቹ፣

---

159 ቴዎድሮስ ለጦር አለቆቻቸውንና ተከታዮቻቸውን መሀላችሁን እንስቻለሁና ሂዱ በማለት ለቀዋቸዋል::

የነበረውን መለናከል እንዲያስወግዱ ነበር፤ የ1ኛው ብርጌድ ደግሞ በቅርብ ርዳታ እንዲያደርግ ሆኖ ነው። የመድፍ ወይም ከባድ መሳሪያው ተኩስ በመግቢያውና በምሽጉ በለሜን በኩል እንዲያተኩር አደረግኩኝ፤ የለሜኑ ክፍል በወታደሮች ጎጆዎች የተጣበበ ስለነበር ነው፤ በተቻለ መጠን የአቢሲኒያ እስረኞችና ሲቪሎች ያሉበትን መሀል ላይ ከፍ ያለውን ቦታ እንዳይነካ ለማድረግ ሞከርኩ። ጢሳት በጥንቃቄ ራሱን ደብቆ ስለነበር፣ ቦታው ጭር ያለ ሰው የሌለበት ይመስል ነበር። ነገር ግን ወታደሮቻችን መግባት ሲጀምሩ፣ ቦታው፣ ጠመንጃቸውን በወረወሩ ወታደሮች፣ የተፈቱ እስረኞች፣ ብዛት ያላቸው ቴዎድሮስን ወደው ወይም ሳይወዱ ይከተሉ በነበሩ ሰዎች ተሞልቷል። በለው እጅ የተሠራው መከላከያ ደግሞ፣ የካብ እጥር ሲኖረው፣ በላዩ ላይ፣ ሾህ ባለው የእንጨት መስናከል ተሸፍኗል፤ በመሀሉም ጠባብ በደንጋይ የታቀፉ መግቢያዎች አሉት። ዝቅ ያለው መከላከያ ከውስጥ በኩል ነው የተሠራው፤ ከፍያለው ደግሞ ዝቅ ብሎ ከተሠራው መከላከያ በለባ ጫማ ከፍ ይላል። ከወታደሮቹ ጎጆዎች፣ ጠባብ፣ ቀጥ ያለ ዳገት ያለበት የተጠማዘዘ መንገድ ወደዚህ መከላከያ ይወስዳል። የዚህ መከላከያ ጥቃት የተካሄደው በሰር ቻርለስ ስታቨሊ ሲሆን፣ ወታደሮቹ በጀግንነት የፈፀሙት ተግባር ነበር። የዚህ ሪፓርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዟል። እንደ ዕድል ሆኖ መከላከያዎቹ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አልተሠሩም፤ ምንም እንኳን ጥቃቱ ከጠላት በኩል ጀግንነት በተሞላበት ሁኔታ በተኩስ ቢፋጠጥም፣ ተኳሾቹ ወደነሱ እየገሰገሰ የሚሄደው ጥሶ የሚገባው ወታደር ላይ ማነጣጠር አልቻሉም፤ እንደሱ ካደረጉ ደግሞ ራሳቸውን ከለናይደር ጠመንጃዎች ከሚተኮሰው ፈጣንና ገዳይ ለሆነ ጥይት ያጋልጣሉ። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ከኛ በኩል የሚደርሰው አደጋ ቀለል ያለና ብዙም ውጤት የማይኖረው ይሆናል። የሮያል ኢንጂነርስና መንገድ ሠሪዎቹ ከ33ኛው ሬጅመንት ቀዳሚ ክፍል ጋር ሆነው መግቢያውን ከመጣሳቸው በፊት ቀደም ብለው ሄደው ስለነበር፣ ዘጠኝ መኮንንኖችና ወታደሮች የመቁሰልና ቀላል የሰውነት አደጋ ደርሷባቸዋል።

ከረጅም ጊዜ በኋላ መግቢያ መንገድ ሲከፈት ተቻለ። ይህም በመግቢያው አካባቢ ተዘጋጅቶ በነበረው መሰላል እማካኝነት የ33ኛው ቀዳሚ ግንባር ሰዎች በእለቱ በኩል ወጥተው የመከላከያ ቦታ ማለፊያዎችን ስለከፈቱ ነበር። ጠላትም ወደ ሁለተኛው መከላከያ እንዲያፈግፍግ ተገደደ፤ ከዚያ በኋላ ግን መከላከሉ ቆመ። በውጭ በኩል በነበረው መግቢያው በር አካባቢ፣ ቁጥር ያላቸው የቴዎድሮስ ታማኝ አለቆች ሞተው ተገኙ፤ ከነዚህ መሀል አንዱ ደጃች እንግዳ ነበር። ደጃዝማቹ ሁሉንም እስረኞች እንግደላቸው ብሎ ቴዎድሮስን ተማጥኖ ነበር፤ ነገር ግን ጉዳዩ በሌሎቹም ግፊት ሳይደረግ ቀርቷል። በሁለተኛው ማለፊያ በር አጠገብ ቴዎድሮስ ወድቀዋል። የ33ኛው ሰዎች ማለፊያውን ጥሰው ሲገቡ፣ ቴዎድሮስ ወደቁ፤ በኋላ እንደለማሁት ከሆነ በራሳቸው እጅ ነው። ወታደሮችም ወዲያውኑ ሽሽት ጀመሩ፤ አንዳንዶቹ በቃፊር በር በኩል ነበር፤ በሩም ወታደሮቹ ሲሸሹ በወረወሯቸው ጠመንጃዎች ተጨናንቆ ነበር። ከነዚህ ከሸሹት ወታደሮች አብዛኞቹ በኦሮሞዎች እጅ ወደቁ፤ የቀሩት ደግሞ፣ በጓደኞቻቸው ላይ የደረሰውን ዕጣ ካዩ በኋላና ከኦሮሞዎች በኩል የሚመጣውን የዛቻ ጥሪ ሲሰሙ ወደ መቅደላ ተመልሰው እጃቸውን ሠጡ።

የመቅደላ ሀላፊነት ለብርጋዴር ጄኔራል ዊልቢ ነው የተሠጠው፤ እሱም ከ33ኛውና ከ45ኛው ሬጅመንት ከንፍ ጦር ጋር በታውን ተቆጣጠረ፡፡ በጣም ብዛት ያላቸው ሰዎች ስለሚኖሩበትና የሰዎቹ ቁጥርም ከመጠን በላይ ስለነበር፣ ሥርአት ማስያዝ ቀላል አልነበረም፡፡ በየመግቢያው ላይ ዘቦች ተመደቡ፤ ይህም ለደህንነት ወይም ጥበቃ አስፈላጊ ስለነበር ነው፡፡ የቴዎድሮስ ቤተሰቦች በሚስተር ራሳም ሃላፊነት ስር ተመድበው፣ በተቻለው መጠን የሚያስፈልጋቸው ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያደርግላቸው ተጠየቀ፡፡ አቢሲኒያውያን እስረኞች ከእግር ብረትና ሰንሰለታቸው ተፈቱ፡፡ ብዛት ያላቸው አቢሲኒያውን፣ በዚያን ጊዜ ጉዳያቸውን ለመመርመር ጊዜም ስላልነበር፣ ለመጠበቅ እንዲቻል ወደመሀል ቦታ እንዲሰበሰቡ ተደረጉ፡፡ እነሱም ወዲያውኑ ጎጆዎችን ቀልሰው መጨረሻ መቅደላ ለቀን እስከንወጣ ድረስ በቦታው ቆዩ፡፡ በ15፣ 4ኛው(የንጉሡ) ሬጅመንት፣ መቅደላን ከ33ኛው ተረከበ፤ 45ኛው ደግሞ ወደ ሰላምጌ ተዛውሮ፣ በኮሎኔል ፊልድ የሚመራውን 10ኛውን ድጋፍ እንዲሠጥ ተደረገ፡፡ ይህም የተማረኩትን መሳሪያዎችና መድፎቹን ለመጠበቅና፣ እነዚህን መሣሪያዎች ለማውደም ለሚዘጋጁ ሰዎች ተጨማሪ የሰው ሀይል ለመስጠት ነበር፡፡ የመቅደላ ነዋሪዎች ደግሞ አሮጌ ላይ እንዲሰበሰቡ ተደረገ፤ ይህም የሆነው ቀንና ሌሊት ሰዎቹን ለመዝረፍና ለመግደል አድፍጠው ከሚጠብቋቸው ኦሮሞዎች ለመጠበቅ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ስለነበረ ነው፡፡

ምንም እንኳን ከኦሮሞዎቹ ንግሥቶች ጋራ መልካም ወዳጅነት ቢኖረንም፣ ሰዎቻቸው ግን በመጠኑ እንኳን ራሳቸውን ስለማይቆጣጠሩ የመጠጥ ውሃችን እንዳይወስዱና የጋማ ከብቶቻችን እንዳይነዱብን፣ በመተኮስ፣ በተደጋጋሚ ማባረር ነበረብን፡፡ የተወሰኑት የነሱ ሰዎች ለዘረፋ መቅደላ ድረስ ደፍረው ገብተው በ33ኛው ዘብ ወታደሮች ተያዙ፡፡ በ15ና በ16፣ ጥትቃቸውን የፈቱ ወታደሮችና ህዝቡ ከአሮጌ መውጣት ጀመሩ፡፡ ሁሉም አይነት እስተያየት ተደርጎላቸው፣ የነበራቸውን ንብረት ይዘው እንዲሄዱ ተፈቀደላቸው፡፡ ከአሮጌ ሲወርዱ በእግረኛ ወታደሮች እንዲጠበቁ ሲደረግ፣ በሸሎን ተሸግረው ዋድላ እስኪደረሱ ድረስ ደግሞ መንገደኞቹ በፈረሰኞች እንዲጠበቁ ተደረገ፡፡ አብዛኞቹ እነዚህ ሰዎች፣ በቴዎድሮስ ብዙ መከራ በደረሰባቸው በደላንታ ገበሬዎች ያለምንም ጥርጣሬ ትንሽም ምህረት አይሠጣቸውም ነበር፤ ሆኖም ለእንግሊዝ ሠራዊት እጃቸውን ስለሠጡ፣ ደህና ቦታ ደርሰው ወደ የቤታቸው እስኪሄዱ ድረስ የነሱን ደህንነት መጠበቅ የኛ ሀላፊነት ነበር፡፡

በ17ኛው ጠዋት፣ እስከ ቀኑ አስር ሰአት ባለው ጊዜ ውስጥ ማንም ሰው ከመቅደላ እንዲወጣ ትዛዝ ተላለፈ፡፡ በዚያ ሰአት፣ ሁሉም መቅደላ መግቢያ ላይ የተማረከ መሳሪያ እንዲወድም ተደርጎ፣ መግቢያ ማለፊያዎችም እንዲፈርሱ ከተደረገ በኋላ በመቅደላ የሚገኙ ሁሉም ቤቶች በእሳት እንዲጋዩ ተደረገ፡፡ ሊረዷቸው የሚችሉ ጓደኞች የሌላቸው የቆሰሉ አቢሲኒያውያን ወደኛ ሆስፒታል ተወሰዱ፡፡ ዝሆኖቹና ከባድ መሳሪያውች በ15 አስቀድሞ ስለተላኩ፣ በሚያዝያ 18፣ ሠራዊቱ ወደ ባህር ዳርቻ ጉዞው በሸሎን መልሶ ተሻገረ፡፡ የዘመቻውን ፕላንና ፎቶግራፎች በአክብሮት አያይዣለሁ፡፡ የህንን መልክት አስቀድሜ መጨረስ ባለመቻሌ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ ነገር ግን በዚህ አስቸጋሪ ሀገር ጉዞ ማድረግ፣ ቀናቱንና አብዛኛውን ጊዜ

ስለሚወሰድና እና ባለኝ ጊዜም ላይ ጫና ስለሚፈጥር፣ ከአቅሜ በላይ ነው የሆነብኝ። በሚቀጥለው መልክቱ፣ የሪፖርቱን ማጠቃለያ እንደምጨርስ ተስፋ አለኝ፤ ይህም የአብዛኛውን ጦር መመለስ ስለሚጨምር፣ እናም ከዛ በኋላ ለንግስታችን መንግሥት ለእውቅና መቅረብ የሚገባቸውን ሁኔታዎች ማቅረብ ስለምችል ርካታ ይኖረኛል። ይህም፣ በሥሬ ለማዘዝ ክብሩ ያጋጠመኝን የመኮንኖችና የወታደሮችን አገልግሎት በከፍተኛ ሁኔታ ለመፃፍ ስለማልችል እሁን ብፅፍም ደግሞ በበቂ ሁኔታ የሚገባውን ያህል ስለማይሆን ነው።

ታዛዥ አገልጋይዎ በመሆኔ ክብር ይሰማኛል
አር ናፒየር፣ ሉተናንት ጄኔራል
የጦር ጠቅላይ አዛዥ

በሚያዝያ 13፣ በመቅደላ ምሽግ የተማረኩ ከባድ መሳሪያዎች መመለስ

ከብራስ የተሠሩ 3 ባለ አምስት ኢንች አፈሙዝ 56 ፓውንደሮች
አንደ ባለ 18 ፓውንድ ዲቶ
አራት ብራስ 6 ፓውንደር ዲቶ (የቱርክ)
ሁለት ባለ 6 ፓውንደር ዲቶ (የእንግሊዝ፣በካስፒሮ የተሰራ)
አንድ ባለ 6 ፓውንደር (የፈረንሳይ)
አምስት ባላ 24 ፓውንደር ሀውዜር (የፈረንሳይና በሀገሩ የተሰሩ)
ሶስት ባለ 12 ፓውንደሮች ዲቶ
አንደ ባለ 3 ፓወንደር፣ አራት ከብረት የተሰሩ 1 ፓወንደር ሀውዜር

ከሰር ሮበርት ናፒየር መልክት ጋር፣ የሰር ቻርልስ ስታቨሊ ለለ መቅደላ መማረክ የሚገልፅ ለጦር አዛዡ የተፃፈ ሪፖርት ተያይዟል። ሰር ሮበርት በራሱ ደብዳቤ የገለጣቸውን ሁኔታዎች ያትትና በመደምደሚያው ላይ ለአዛዡ የቀረቡ የመኮንኖች ሥም ይዘረዝራል።

*የሚከተሉትን የመኮንኖች ስም ዝርዝር ለአዛዡ ለማቅረብ ምኞቴን አገልጣለሁ፡ ብርጋዴር ጄኔራል ዊልቢ የ2ኛው ብርጌድ አዛዥና ጥቃቱን የመራ። እሱም ውጤታማ የሆነ አገልግሎት ያበረከቱትን መኮንኖች ይጠቅሳል፣ ካፒቴን ሂክስ፣ የብርጌዱ ሜጀር፣ ካፒቴን ጀምስ፣ ምክትል ረዳቱ ሜጀር ጄኔራል፣ እና የ12ኛው የቤንጋል ፈረሰኞቹ ካፒቴን ካገል፣ ሜጀር ፕሪቻረድ (የቆሰለ) ፣ ከሮያል ኢንጂነሮችና ምሽግ ሠሪዎች ከፍተኛ መኮንን ከሚከተሉት መኮንኖች ውጤታማ ርዳታ እንዳገኘ ይጠቅሳል፤ ካፒቴን ኤልየት ከኬ ኮምፓኒ፣ የማዳራስ ምሽግ ሠሪዎችን በመምራት። ካፒቴን ፎርድ፣ ለተናንት በርድ፣ ኮሎኔል ዳልሪምፐል፣ እና ከማዳራስ ምሽግ ሠሪዎች ሰርጀንት ፐርል፣ ሰርጀንት ሃሮልድ አን ዲን፣ ኮርፖራል መዶናግና መንገድ ሰሪ ቤይሊ፣ የ33ኛው ሬጂመንት አዛዥና ሬጅመንቱን ወደ መግቢያውና ከመግቢያው እልፎ የመራ። እዚህ ላይ የተለየ ማስታወሻ ለማቅረብ በልመና እጠይቃለሁ፤ ለቁጥር*

*3691 ታምቡር መችው ሚካኤል መጉዋየር እና ለቆጥር 949 ወታደር ጀምስ በርገን ከ33ኛው ሬጅመንት፤ ሁለቱም ሰዎች ለመጀመሪያ ወደማለፊያ ጥሰው የገቡና መግቢያውን የከፈቱ ናቸው:: ካፒቴን ኤልየት የማዳራስ ምሽግ ሠሪዎች አዛዥ፣ ካፒቴን መዶኔል የቦምቤይ ምሽግ ሠሪዎች አዛዥ፣ ሌተናንት ኮሎኔል ፓሪሽ የ45ኛው አዛዥ፣ የ10ኛው ረጅመንት አዛዥ ኮሎኔል ፊልድ፣ ሌተናንት ኮሎኔል ካሜሮን የ4ኛው(የንጉሡ) አዛዥ፣ ሜጀር በሸሊ የበሉቺ ሬጅመንት ክንፍ አዛዥ፣ ሜጀር ቻምበርሊን የ23ኛው ፑንጃብ ቃኝ ክፍል አዛዥ፣ ብርጋዴር ጄኔራል ፐተሪ የሮያል ከባድ መሳሪያ አዛዥ፣ ሌተናንት ኮሎኔል ዋለስ የሮያል መድፈኛ ዲቪዢን አዛዥ፣ ሌተናንት ኮሎኔል ሚልዋርድ የሮያል መድፈኛ ዲቪዢን አዛዥ፣ ሌተናንት ኮሎኔል ፔን የሮያል ከባድ መሣሪያ (ኤ-21) አዛዥ፣ የባህር ሀይሉ ሮኬት ብርጌድ አዛዥ ኮማንደር ፌሎውስ፣ ካፒቴን ተዊስ የሮያል ከባድ መሣሪያ(ቢ-21) አዛዥ፣ ከ3ኛው ብርጌድ ቀላል ፈረሰኛ ኮሎኔል ግሬቭስ የፈረሰኛው ብርጌድ አዛዥ፣ የ3ኛው ድራጎን አዛዥ ሌተናንት ኮሎኔል ታወር፣ የ12ኛው ቤንጋል ፈረሰኛ አዛዥ ሜጀር ጎሀ፣ ሜጀር ብሪግስ የ ሰንዲ ፈረሰኞች አዛዥ፣ ሌተናንት ኮሎኔል ሎች የፈረሰኛ አዛዥ፣ የ3ኛው ብርጌድ ቀላል ፈረሰኛ ክፍል አዛዥ ካፒቴን ሙር፣ የጠቅላይ አዛዡ አጃቢ አዛዥ ሌተናንት ሰኮት፣ የሮያል ኢንጂነርስ ሌተናንት ኤ ል መሰረር፣ ካፒቴን ለስሊ እና ሌተናንት ሊኮክ ከቦምቤይ ምሽግ ሠሪዎች፤ ካፒቴን ቤይንብሪጅ የመንገድ ትራንስፖርት ኮር አዛዥ፣ ጦሩ በሸሎን ከለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ለወታደሮቹ ውሀ ለማቅረብ ከፍተኛ ግዳጅ የነበረበት፤ ካፒቴን ሮስ፣ ግሪፍት እና ትወንቲማን ከ20ኛው ሁሳር የመንገድ ትራንስፖርር ዲቪዚዮን ኮር አዛዥ፤ ሜጀር ሚኞን የ1ኛው ብርጌድ ረዳት ኮሚሳር ጄኔራል፣ ሜጀር ጎልድስዎርቲ ከ2ኛው ብርጌድ የፈረሰኛ ብርጌድ ሜጀር ተጠባባቂ ኮሚሳር ጄኔራል፤ የ1ኛው ዲቪዚዮን ዋና ሀክምና መኮንን፣ ዶክተር ማሬ ለፊልድ ሆስፒታል ያደረገው ዝግጅት የሚፈለገውን አይነት የነበረ፤ ሰርጀን ሜጀር ዋይሊ ከ2ኛው ብርጌድ የፊልድ ሆስፒታሉ ሀላፊ::*

*ከኔ ረዳቶች ደግሞ የሚከተሉትን መኮንኖች ሥም ለማቅረብ እፈልጋለሁ:: ሌተናንት ኮሎኔል ዉድ ረዳት፣ ሜጀር ቤይገሪ ረዳት ሰንቅና ትጥቅ፣ ሌተናንተ ላውንደርስ ከ20ኛው ሁሳር የካምፕ ረዳት፣ ካፒቴን ጆርጅ አርቡትኖት ተጨማሪ የካምፕ ረዳት::*

*እነዚህ መኮንኖች፣ ከተከበሩት የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ የተሠጡኝን ትዛዞች እንድወጣ፣ ዙላ ከደረስኩበትና የመጀመሪያው ብርጌድ ከመጣ ጀምሮ ትልቅ እርዳታ ያደረጉ ናቸው::*

*ሌተናንት ጄኔራል ሰር አር፣ ናፒየር፣ G.C.8.C.S.I., ለህንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር*

*የጠቅላይ ዕዙ ጽ/ቤት፣ ቀማይሴ ካምፕ*
*ሰኔ 1፣ 1868*

ከቡር ሆይ፣ ስር፣ በግንቦት 20 በተላከው ቁጥር 40 መልከቱ በመቀጠል፣ በዚህ ቀን እኔ ራሴ ወደ አቢሲኒያ ከዘመተው የመጨረሻው ጦር ክፍል፣ የ25ኛው ቦምቤይ

የተወላጆች ቀላል እግረኛ እና የቤሎቹ 27ኛው ባታሊዮን ጋር በመሆን የሶሮ ማለፊያን እንዳለፍኩ በእከብሮት ሪፖርት አደርጋለሁ::

ከደላንታ እስከ አንጣሎ የነበረው ጉዞ ፈታኝ ነበር፤ ይህም አብሮን ይጓዝ ከነበረው በተዳጋጋሚ ከወረደው የዝናብ ማዕበል የተነሳ ነው፣ በከፊልም ቢሆን ወታደሮች እና በተለይም ካምፕ ተከታዮችና የመጓጓዣ ከብቶች ከችግሩ ነፃ ሊሆኑ አልቻሉም::

## የምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች

*__ቁጥር 153፤__ ራሳም፣ አስከሬኑ የቴዎድሮስ መሆኑን እንዳረጋግጥ የተጠየቅሁ እኔ ነኝ፣ ቀብራቸውንም እንዳስፈፅም የታዘዝኩ እኔ ነኝ በማለት ዘግቧል:: አስከሬኑ ሲከፈን፣ ከፋኞች ያሳዩትን ስሜት በማየት፣ ራሳም ሲያትት፣ ምንም ቢሆን፣ በዚህ ሰአትም ለቴዎድሮስ ፍቅርና እከብሮት ያላቸው ሰዎች ነበሩ ይላል:: ቀብሩ ሲፈፀም ግን፣ በሌላ ሥራ ምክንያት በቦታው አልነበረም::*

*__ቁጥር 154፤__ ከንግሥት መስታውት በፊት መቅደላ የደረሰችው ወርቂት ነበረች:: ቴዎድሮስን ባለ እቅማችን ስንታገል ኖረናል፤ ሀይሉን ስላልቻልነው፣ ልጄ አምኖ ገብቶ ነበር፣ አሁን ግን ተገድሏል፤ መቃብሩን ማየት እፈልጋለሁ፤ መቅደላም ይገባኛል ብላ ነበር:: ይህንን ስትል፣ መስታውት እየመጣች ነው ሲባል፣ በችኮላ መቅደላን ለቃ ወረደች:: መስታውት ወንድ ልጅ ስለነበራት ከወርቂት የተሻለች ነበረች:: ሁለቱም እንደ ሌላዋን የምትታመን አይደለችም በማለት ለእንግሊዞቹ ነግረዋል:: አንደኛዋ ሌላዋን፣ ቃሏን አትጠብቅም በማለት የተናገሩት፣ ሁለቱም አንድ ላይ እንዲስማሙ በተጠየቁበት ጊዜ ነበር::*

*__ቁጥር 156፤__ ይህ ፍንዳታ ሲሰማ፣ ከታች የነበሩት እቴጌ ጥሩ ወርቅና፣ የቴዎድሮስ ዕቁባት ወይዘሮ የተመኙ፣ አንድ ላይ ወደ መቅደላ ዞር ብለው ተመለከቱ:: ከዚህ በፊት ከፉ ነገር አምብዛም የማይወጣት፣ በወታደሮቹም ተወዳጅ የነበረችው ወይዘሮ የተመኙ (እንግሊዞቹ እቴጌ ይሏታል)፣ "እንግዲህ ጌታችን ሞተ፤ ከዚህ በኋላ ግን የአቢሲኒያን ሰው እሳት ይፍጀው::" በማለት ተራገመች:: በቁንጅናዋ የታወቀች የየጁ ኦሮሞ ነበረች፤ ከእንግሊዞቹ ጋር አልሄድም በማለት ወደ ትውልድ ቦታዋ ወደ የጁ ሄዳለች:: አፄ ቴዎድሮስ፣ ለወይዘሮ የተመኙ ያደሉ እንደነበር ግልፅ ነበር:: ሌሎች የሚጠቅሱት፣ እቴጌ ጥሩ ወርቅ፣ የደጃች ውቤ ልጅ እንደመሆኗ ቴዎድሮስን ትንቅ ነበረ:: አንድ ጊዜ፣ ቴዎድሮስ ወደ ክፍል ሲገቡ እቴጌዋ ከመቀመጫዋ ሳትነሳ ባይኗ ብቻ ገርመም አድርጋ ማንበቧን ቀጠለች:: ባልየው፣ ራሳቸው ንጉሡ እንደገቡ አውቃለች:: የተናደዱት ቴዎድሮስ፣ "እንቺ ሴት ተመልከቺኝ" በቁጣም "ተነሺ! እኔ አሽከር እመስልሻለሁ?" አሉ:: እቴጌዋ ቀስ ብላ ከመቀመጫዋ ተነስታ የታጠፈውን ልብሷን በመዘርጋት፣ ቀዝቀዝ ባለ አንደበት፣ "ሲገቡ አልሰማሁም፣ ከሰዎ የበለጠ*

*ጌታን፣ ፈጣሪን  እያናገርኩ ነበር፡፡" በማለት ስትመልስ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለባቸው ቴዎድሮስ ንዴታቸው በርዶ፣ ምንም ቃል ሳይተነፍሱ ወጥተው ሄደዋል፡፡ እቴጌዋ የቴዎድሮስን ባህሪ በደንብ ታውቅ ነበር፡፡*

***ቁጥር 157፣*** *የደላንታ ሰዎች ከዋግሹም ጎበዜና ከወሎ ኦሮሞዎች ጋር ሸፍተው ነበር፡፡ ሆኖም ዋግሹሙ፣ የቴዎድሮስን ምመጣት ሲሰማ የ30ማይሎች ርቀት ሸሽቶ በመሄዱ፣ የደላንታ ሰዎች የግድ ለቴዎድሮስ እጅ መስጠት ነበረባቸውና ምህረት ጠይቀው ገቡ፡፡ ቴዎድሮስም፣ እኔ ልጠብቃችሁ ካልቻልኩ እንዴት አደርጌ አማችኋለሁ በማለት ምህረተ ሰጥተው ነበር፡፡ እልፈው ሲሻገሩ ግን፣ የደላንታን ሰዎች፣ ለምን ከዚህ ቀደም ወደኔ አልገባችሁም ብለው ሲጠይቁ፣ ሰዎቹም ዋግሹም ጎበዜና ኦሮሞዎቹ ከልክለውን ነው በማለት ሲመልሱ፣ ቴዎድሮስ ተናደው፣ እናንተም እንደነሱ መጥፎዎች ናችሁ በማለት መንደሮቻቸው እንዲበረበሩ አዘዋል፡፡ በርግጥ፣ የደላንታ ሰዎች ከዋግ ሹም ጎበዜ ጋር ከማበራቸው በፊት፣ ለመቅደላ ምሽግ ቀለብ ይሰፍሩ ነበር፡፡*

***ቁጥር 158፣*** *ከምኒልክ ጋር ተላልከዋል ከተባሉት አንዱ የመቅደላው አዛዥ የበጌምድሩ ራስ ኪዳነ ማርያም ነበሩ፡፡ በቴዎድሮስ ትዛዝ ታስረው ወደ ደብረ ታቦር ስለተወሰዱ የበጌምድር ሰው አኩርፎ ነበር፡፡ በኋላ፣ ራስ ኪዳነ ማርያም፣ ቴዎድሮስን ቀድመው መቅደላ እንዲመለሱ ሆኗል፡፡ በመቅደላ አምባ የነበሩ ሁለት ቢትወደድ ሀይሉ የሚባሉ ነበሩ፣ አንደኛው የጭሊጋው ሲሆን ይህ ሌላው መሆኑ ነው፡፡ ከመቅደላ በሌሊት በመሰላል ነው ያመለጠው፤ ለማምለጡ  ምክንያት፣ የሰውየው የቅርብ ዘመድ የሆነ ባላምባራስ ገብሬ መድህኔአለም የሚባል የወንደጂ ገዥ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍቶ ስለነበር እሱንም ያስጠይቀዋል በሚል ፍራቻ ነበር፡፡*

# ምዕራፍ አስራ አራት

ወደ መጣንበት - ወደ ተከዜ ጉዞ፣ የሉተናንት ሞርጋን ሞትና ቀብር፣ ታቦት፣ የቄሶች የምስጋና ቅዳሴ፣ ከመቅደላ ሰደተኞች ጋር መለያየት፣ የንግሥት ቪክቶርያ ለከሩሴዱ ጦር እንኳን ደስ ያላችሁ መልከት፣ የእቴጌዋ ሞትና ቀብር፣ ልዑል እለማየሁ፣ የካሳ ሽልማትና ከናፒየር ጋር ሰንብት፣ በሶሮ ማለፊያ ትልቅ ጎርፍ

በሚያዝያ 24፣ ሠራዊቱ፣ እምባው ላይ የነበረውን ካምፕ እፍርሶ ወደመጣበት ለመመለስ መንገድ ጀመረ፡፡

የእንግሊዝ ሠራዊት፣ በአራቱ ቀናቶች ውስጥ በነበረው የተትረፈረፈ ሁኔታ፣ ጥሩ ዕረፍት አድርጎ ስለነበር በጣም በተዝናና እና ደስተኛ ሁኔታ ወደ ባህር በሩ ለፍጥነት ጉዞ የተዘጋጀ ነበር፡፡

ሁሉም እደጋዎችና የነበሩ ፍራቻዎች በመወገዳቸው፣ ወደቤት በሚደረገው ጉዞና ከሱም ጋር ተያይዞ በሚታየው እስደሳች ለሜት

*ለማንም ጠላት፣ ለምንም አደገኛ ማለፊያ እንበገረም፣*
*ዳተኛነትን አንቀበልም፣ ወደፊት ያለምንም ልጓም*
*በፍጥነት ወደፊት መሄድን ነው እንጂ፡፡*

እናም የሚያነቃቃው "የጌሪ እውን" ጣዕመ ዜማ በጆሯቸው እየተንቆረቆረ፣ እነዚህ ደፋር የአየርላንድ ወታደሮችና "የዌልንግተኑ መስፍን" ፈጥኖ ከመንቀሳቀስ ውጭ ምን ያደርጉ ነበር፡፡

*በጋራዎች ላይ፣ እንደ ጀግና ተዋጊ*
*እንበታትናለን ሁሉንም*

እነሱንም ተከትሎ የጦር ጓደኞቻቸው፣ "የንጉሡ"፣ 45ኛው፣ የ3ኛው ድራጎን ጋርድ፣ በሺ የሚቆጠሩት የህንድ ሠራዊት አባላት፣ ከነሱም ጋር በሺ የሚቆጠሩ የካምፕ ተከታዮች ነበሩ፡፡

ጦሩ ከደላንታ ሲነሳ በጣም ጥሩ ጤንነት ላይ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመሀከላቸው ለማንያ የሚሆኑ፣ በመቅደላና በአሮጌ የቆሰሉትን ጨምሮ፣ የተጎዱ ሰዎች ነበሩ፡፡ የሆነ ሆኖ በየብርጌዱ ሆኖ በብዛት የሚደረገው ጉዞ፣ ሳይውል ሳያድር በበሽሎ ሸለቆ የደረሰባቸውን የእንስሶቹን ጉዳት ማሳየት ጀመረ፡፡ የጀዳን ሸለቆ እንዳለፍን፣ የሚቀጥለው ቀን እስቃቂ ሁኔታ ነው

የፈጠረው፡፡ መኮንኖቹና ወታደሮች ተዝናንቶ በነበረው የሰውነታቸው ሁኔታ መቸገር ጀመሩ፤ ይህም ለዘመቻው ሲባል ጓዝ እንዳይሸከሙ ተደርጎ ስለነበር ነው፡፡

ምንም ሳናቆም ከሰንዲ ተነስተን እብደቁምን አለፍን፤ ከዛም ጋዞና ሳንታሪ፣ ቁልቁል ወደ ተከዜ ወርደን፣ በሚያዝያ 28 በወንዙ ዳርቻ ካምፕ አደረግን፡፡

በዚህ ቦታ፣ የእንግሊዝ ሠራዊት አንደ ምስጉን መኮንን፣ የ10ኛውን የሮያል ኢንጂነርስ ኮምፓኒ ሉተናንት ሞርጋንን አጣ፡፡ ወጣት፣ ደፋር፣ ታታሪ፣ ከዛም በተጨማሪ እውነተኛ ክርስቲያን ሰው ነበር፡፡ በተከዜ ዳርቻ፣ በቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ዙሪያ ካሉ ዛፎች በአንዱ ጥላ ሥር ተቀበረ፡፡ የ1ኛ ብርጌድ ሲቪልና ወታደሮች በሙሉ አስከሬኑን ተከትለው ወደቀብር ቦታው በመሄድ የሚገባውን ክብር ለመስጠትና የሚያውቁት ሰዎች በሙሉ ሀዘናቸውን ለመግለጥ ነበር፡፡ በቀብሩ ሥነ ሥርአት ላይ የተነበበው በጣም ስሜት የሚነካ ስለነበር፣ በመቃብሩ ዙሪያ የቆሙ ሁሉም፣ በርግጥ ብሩህ ተስፋ የነበረው ወታደር ከዚህ አለም መለየቱን እንዲሰማቸው አድርጎታል፡፡ በሚወዛወዙት ዛፎች ሥር ነበር መቃብሩ የተቆፈረው፤ እንግዲህ ወደፊት ትውልድ በትውልድ ሲተካ፣ ይህ ወደ መቅደላ የዘመተ፣ ታዋቂ ክሩሴደር ያረፈበት ቦታ፣ በአውሮፓውያን መንገደኞች የሚከበር ሥፍራ ይሆናል፡፡

የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ፣ ሉተናንቱ ስለነበረው የላቀ አገልግሎት፣ ለማያወላውል ጉልበቱና ጥረቱ፣ በማለፉ ምክንያት የሚሰማውን ሀዘንና የእንግሊዝ ሠራዊት የደረሰበትን ጉዳት የሚገልፅ የምስጋና መግለጫ አስተላለፈ፡፡ ሉተናንት ሞርጋን በሙሉ ወታደራዊ ሥርአት ተቀበረ፡፡

ማምሻውኑ፣ የሀገሩ ተወላጆች ለአሸናፊዎች የሚያሳዩት ስሜቶች መረጃ የሚሆኑ ምልከቶች ማየት ጀመርን፡፡

ወደ ደቡብ ስንጓዝ፣ ጆሮቻቸውን በጣቶቻቸው ደፍነው ወታደሮቹ ሊያደርጉ ያሰቡትን ነገር ሲነግሯቸው ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፡፡ አሁን ግን ወታደሮቹ ምሽጉን የተለበለበ አለት እስኪሆን ድረስ እቃጥለው የማይበገረውን የቴዎድሮስ ሠራዊት በአራት እቅጣጫ ለነፋስ በትነው መምጣታቸውን ሲያውቁ፣ ለማዳመቅ መምጣት ጀመሩ፡፡

የነበራቸው ትቢትና ኩራት የ "ቴዎድሮስ አሸናፊዎች" ላይ ባደረባቸው አስደናቂ ስሜት መተካት ጀመረ፡፡ በብዛት እየሆኑ ለምስጋና ይመጡ ጀመር፡፡ ከመዝሙረ ዳዊት የምስጋና መዝሙር፣ "በሀይሉ ማዳንና ከበረከቱ ብዛት"፣ የሚጀምረውም፣ "እግዚአብሔር እለቴ አምባዬ ነው መድሀኒቴ ነው፤ እግዚአብሔር ጠባቂዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ፤ ጋሻዬና የረድኤቴ ቀንድ፥

መጠጊያዬና መሸሸጊያዬ፣ መድኃኒቴ ሆይ፥ ከግፍ ሥራ ታድነኛለህ" (2ኛ ሳሙኤል፤ 22)

በተመሠጠ ዳዊታዊ በሆነ ስሜት ነበር የተደገመው:: "ዳዊት በጌታ ፊት በተገኘው የሙዚቃ መሳሪያ ነበር የተጫወተው::" የሳውል ልጅ ሚካስ እንዳየችው የአይሁዳውያንን ሽርጥ አሽርጦ ሲዘልና ሲወዛወዝ ነበር:: ጥሩምባ እየተነፋና በከፍተኛ ድምፅ እየጮሁ የአቢሲኒያ ቄሶች፣ ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎችና የቤተክርስቲያኗ ልጆች የፅላቱን እምሳያ ታቦቱን ይዘው መጡ::

የኢትዮፒክ የታቦቱ እምሳያ ርዝመቱ አምስት ያርድ፣ ጎኑ አንድ ያርድ ሲሆን ከፍታው አንድ ጫማ ይሆናል:: ዳር ዳሩ በወርቅ ባጌጠ ቀይ ልብስ ተሸፍኗል፤ በላዩ የምህረት ወንበር እምሳያ አለው፤ ግን ከወርቅ የተሠራ አይደለም:: ከእንጨት የተሠራ ሆኖ ሀር ለብሷል:: ላዩ ላይ ከፍ ፉ ያጌጠ ሀር እንደ ዘውድ ሸፍኖታል፤ የስንዝር ርዝመት ያለው የተንጠለጠለ ነገር በሁለቱ ጎኖች አሉ::

ፅላቱ ላይ ኪሩቤሉም ሆነ የስርየት መከደኛው አይታዩም:: እነዚህ ሁለት ነገሮች ስለሚጎድለው፣ እንደ ዋናው የሙሴ ፅላት አይሆንም:: ከሚያሸበሽቡት ሰዎች እናት ላይ ከፍ ብሎ የተለያዩ ቅዱስ የተባሉ የቤተክርስቲያን ዕቃዎችን ጨምሮ፣ ሻማዎች፣ ከብርና ከብሮንዝ የተሠሩ መስቀሎች ወዘተርፈ ተይዘዋል::

ዋናው ቄስ፣ ረዥም እጅጌ የሌለው ቀሚስ ለብሷል፤ አናቱም ላይ ጥምጣም አድርጓል:: ደረቱም ላይ በደንብ ያጌጠ የበሬ ቆዳ ይታያል::

ተከታዮችም ከጥጥ የተሠራ እጀ ጠባብ ለብሰው፣ ቀበቶዎችን ይዘው ከቄሱ ጋር ይጓዛሉ:: ይህ በተራው የልጆቹን ከፍተኛ አድናቆትን በመፍጠሩ፣ ጆሮ የሚያደነቁር ዜማ እያሰሙ የያዟቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች እየተጫወቱ ወደ ጠቅላይ ዕዙ ቢሮ ይጓዛሉ::

ከነሱ መሀከልም በከፍተኛ ድምፅ የሚያዜሙ ብዛት ያላቸው ቅጥ ያጡ ባለጌዎች ነበሩ፤ ሀፍረት በሌለው ድፍረት ከፈረንጆቹ ገንዘብ ይለምኑ ነበር::

ከነዚህ ብዛት ካላቸው የተደበላለቁ ጠያይሞች ወንድ፣ ሴትና ህፃናት ባሉበት ቦታ፣ በሚያስገርም ሁኔታ ንፁህ ልቦና ያለው የሰዎች ፊት በጣም ጥቂት ነበር:: ለአመል ያህል አንኳን ኢጋጣሚዊን ሲያገኝ የማይገባውን ንብረት ከማንሳት የሚቆጠብ አንድ ነብስ እለ ብል እንኳን የማጋንን ይመስለኛል::

የራሱ ያልሆነውን ንብረት በከፍተኛ ብልጠት ለመውሰድ ያለው የሰው መሠረታዊ ባህሪ በነዚህ ሰዎች በያንዳንዳቸው ላይ የታተመ ይመስላል::



ቄሶች ለሮበርት ናፒየር ሲያሸበሽቡ
(Roger Acton)

የነበረው ወዳጅነት በሚታየው ተመሳሳይ ባህሪ ከቀዘቀዘ ወዲያ፣ ከሠራዊቱ ውስጥ፣ ማንም ሰው ቢሆን፣ እኔ እንደማምነው ከሆነ፣ አንድም አቢሲኒያዊ ድንኳኑ አጠገብ እንዲገኝ የሚፈቅድ አልነበረም፡፡

ነገር ግን ለፈረንጆቹ ከብር ሲባል ለመዘመር ሲመጡ ማንም ቢሆን ለመቃወም ልቡ የከጀለ አልነበርም፡፡ ያም ግን ሰዎቹ ከድንኳኖቻቸው በር በቂ ርቀት አስከቆዩ ድረስ ነበር፡፡ ሰር ሮበርት ናፒየር በነሱ ላይ በተቀዳጀው አሸናፊነትና በነበረው ትልቅ ልቦና፣ ለጦርነቱ እህልና ሌሎቹንም አስፈላጊ ነገሮች በማቅረብ የጦሩ ረዳቶች ነበሩ ብሎ ስላመነ፣ ወታደሮቹና መኮንኖቹ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚችሉትን ያህል ጥሩ ፊት ለማሳየት ሞከሩ፤ እንዲያውም በልቦናቸው የሚበቃ የመዝናናት ስሜት ስለተሰማቸው ዘፈንና ዜማውን ለመውደድም በቅተው ለታየው ዘፈንና ሽብሸባ ሲያጨበጭቡ ነበር፡፡

በተወላጆቹ መሀል ቄሶቹ ከፍተኛ ከብር ስለነበራቸው ከተሰብሳቢዎቹ ፊት ለፊት የነበሩት እነሱ ነበሩ፡፡ ሁሉም፣ ከጠቅላይ ዕዙ ቢሮ ሃምሳ ርምጃዎች ርቀት በሚገባቸው ቦታ ከቆሙና ከተሰበሰቡ በኋላ፤ ከመሃከላቸው ጠንካራ ድምፅ ያለው ቄስ ንጉሡን ላሸነፉ ፈረንጆች ከብር ሲባል የሚቀደሰውን ዜማ ከፈተ፡፡

ዜማውን እያዜመ መሚሚቅ ሲጀመር ድመፁ እየጎላና እየደመቀ ሄደ፤ የተሰበሰቡትም፣ መስቀል በሚወዛወዙበት ጊዜ፣ ዜማውን ተቀላቀሉ፤ በከፍተኛ ድምፅ ሲዘምሩም የሚያስደነቅ ውጤት ነው የፈጠረው፡፡

ከዚህ ዜማ በኋላ፣ ሰድስት ቄሶች በዋናው ቄስ እየተመሩ ማነብነብ ጀመሩ፡፡ ወዲያውኑ ድምፃቸው ከፍ ብሎ ሳንባቸው የሚቀደድ እስከሚመስል ድረስ ከዚህ ቀደም እንደሆነው አይነት እንደገና በዜማ ተጨረሰ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ዙሪያ ፈጥረው፣ ባጭሩ ሲገለፅ፣ ወረብና ሽብሸባ ጀመሩ፤ ዜማው እየደመቀ ሲሄድ፣ ለምልከት ጭብጨባ ሲጀመር፣ በዙሪያው የነበሩ ሴቶችና ህፃናትም "እልል እልልልል!" በማለት እነሱም ወደ ላይ መዝለል ጀመሩ፡፡

ከዚያም በሶስት ረድፍ ተከፍለው እንደቀደመው ሁሉ በከፍተኛ ድምፅ በማዜምና እንቅስቃሴም በመጨመር ሽብሸባውን ቀጠሉ፡፡ ከመሀከላቸው ስድስት የቄሱ ረዳቶች ነበሩ በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱት፤ ከነዚህ መሀል፣ በጣም ልጅ በነበሩት በሶስቱ የተለየ የሽብሸባ እንቅስቃሴ ተደረገ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ፅላቱ ከቄሶቹ አጠገብ ነበር፡፡ ሁሉም ከተደረገ በኋላ በከፍተኛ ድምፅና ዜማ እንቅስቃሴውና ዜማው ተጠናቀቀ፡፡

ላዳረጉት ውለታ ተብሎ በአገልግሎት ምክንያት የተጎዱ አንድ መቶ ሀያ ሶስት በቅሎዎች ለእነዚህ ሰዎች ተሠጣቸው፡፡ በተጨማሪም በርከት ያለ

የበቆሎና የሳር ክምር፣ እኛ በሌለንበት ጊዜ በማጓጓዣው መስመሩ ተሰብስቦ ነበር፤ የጦር ማጓጓዣው በምንም አይነት ሲወስደውም አይችልም ነበር።

በዚህ ካምፕ ከመቅደላ ከተለቀቁ ሰዎች ከመጨረሻዎቹ ጋር ተለያዩን። እነሱም መንገዳቸውን በላሊበላ በኩል አድርገው ወደ ጣና ሀይቅ አቅጣጫ ሄዱ። እኛም ጉዟችን ወደ ሰሜን ቀጠልን። ከጦሩ ጋር እያሉ በእያንዳንዱ ጣቢያ በበቂ ሁኔታ ተመግበው ነበር።

ስንመለስ የምግብ እጥረት አልነበረም። እኛ በሌለንበት ጊዜ የወታደር ካምፖቹ ከየምግቡ አይነት ክምር በሚሆን ደረጃ ሰብስበው ነበር። የብር ዶላሩ፣ የሀገሩ ተወላጆች እጅ ላይ ካረፈ ምንም አይነት ያላቸው ነገር በሙሉ ለሽያጭ ይቀርባል። መሬቱ በበቂ ሁኔታ ያልታረሰ እንደ መሆኑ፣ በተፈጥሯቸው ድንጉጥና እንግዶችን ተጠራጣሪ እንደመሆናቸው መጠን፣ በተጨማሪም ቀለቡ የተሰበሰበበት አካባቢ ጠበብ ካለ የሀገሩ ክፍል እንደመሆኑ፣ ለምግብ የሚሆነው ቀለብ አሰባሰቡ በጣም የሚያስገርም ነው።

ጦሩ ወደፊት በደስታ ይገሰግሳል፤ ጉዞውም ከተከዜ ወደ ሙጃ፣ ከሙጃ ወደ ወንደች፣ በደመና በታጠረው መኸገር አምባ ላይ የተከዜን ሸሰቆ ተሰናብቶ ነው። ከዛም ቁልቁል ወደ ዲልዲ ወርደን ልብሳችንና የነበረን ንብረት ሰበሰብን። እንደገናም፣ ዕይታው፣ የተጠማ ከንፈር ላይ እንደሚያርፍ ውሃ በሚያረካው በቦሄያ ተደሰተን። ከዲልዲ ወደ ማርዋ የሚያቆሰል ጉዞ ነበር፤ በሙቶዎች የሚሆኑ በቅሎዎች ሞቱ። ከማርዋ፣ ወደ መቅደላ ለጥቃት ሲሄድ የኛው ዲቪዚዮን ያረፈበት ቦታ፣ ወደ ላት፣ ከዚያም መሰጊታ ቀጥሎም የሚያምረው አሸንጌ ሀይቅ ነበር። ከሀይቁ ባሻገር ያለው የሚያምረው ረግርግ በአረንጓዴ ገፅታው ፈገግ ብሎ ይታያል።

አሸንጌ እያለን፣ በሶሮ ማለፊያና በሰናፌ ቁልቁለት የሚወርደው ጎርፍ መጀመሩን ዜና ሰማን። በማለፊያው ውስጥ የተሠራው የወታደሮች መንገድ መፍረሱን፣ በተጨማሪም ዝናቡ በሀይል ለመጀመሩ ምልክቶች መኖራቸውን፣ ስለዚህ፣ መንገዱ ወታደሮችን ወደ ባህር ዳርቻው ለማሳለፍ የሚሆን አለመሆኑን ነው።

የብዙ ማይሎች ርዝመት የነበራቸው የቴሌግራፍ መስመሮች በጎርፉ ተወስደዋል። ብዙ የድርቆሽ ክምርም ከጥቅም ውጭ ሆኗል። በርግጥ፣ ለዚህ የከፋ ሁኔታ መሻሻል የሚበጁ የተለያዩ ሀሳቦች መሰንዘር ተጀምሯል።

በሰናፌ፣ የዝናቡ ወራት እስከሚያልፍ ወታደሮቹ የሚሰነብቱባቸው ጎጆዎች እንዲሠሩ ሀሳብ ተሰጠ። እንደገናም ካምፑ እንዳለ በሰናፌ ቁልቁለት ላይ እንደነበረው እንዲቆይና እያንዳንዱ ጣቢያ ለሚመጡት ወታደሮች ምግብ አዘጋጅቶ እንዲጠብቅ፤ ቴሌግራፎችም ወታደሮቹ የሚደርሱበትን ሰአት

እንዲያስታውቁ ተባሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሀሳቦች በሙሉ ውድቅ ሆኑ፡፡ ያም ውሳኔ ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሆነ በጎርፉ ምክንያት የደረሰው ጉዳት በሙሉ ለሰር ሮበርት ናፒየር በዝርዝር እስኪቀርብ ድረስ ነበር፡፡

ያን ቀን ማታ በአሸንጌ ከባድ ዝናብ ጥሎ ድንኳኖችን ለላበሰበሰ ላያያዝ አስቸጋሪ ሆኗል፤ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን ጥዋት አራት ሰአት ላይ ድንኳኖቹ በደንብ ደረቁ፤ እናም ጦሩ ጎዞውን ቀጠለ፡፡ ብዛት ያለው የተረፈ ጓዝ በእሳት እንዲቃጠል ሆነ፤ ጄኔራሉ ለነዚህ ለተረገሙ ሰዎች መስጠት አልፈለገም፡፡ ደግነት ባደረገላቸው፣ ሰዎቹ ምስጋና ቢስ ነው የሆኑት፤ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ፣ ጓዙ ከዚህ ጣቢያ ጀምሮ ወደ ፊት ከመሄድ እንዲጓተት አደርገዋል፡፡ ያም ኮሎኔል ሚልዋርድ ከቀናት በፊት በሀይቁ አጠገብና በውሀው ላይ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ ነበር፡፡

አሸንጌን ከለቀቅን በሁዋላ፣ በሞሰባ ተራራ ደቡብ በኩል ባለ ዳገት ላይ የሚገኘው የሀያ ጫካ ከሶስት ወይም አራት ሰአት በኋላ ደረሰን፡፡

ስንመለስ፣ በመንገዳችን ላይ፣ የሮያል ኢንጂነርስ ትሪጎኖሜትሪካል ሰርቬይ (አሳሽ) መኮንኖች የሆኑትን ሉተናንት ካርተር፣ ደምለር እና ሆልዲችን አገኘናቸው፡፡ በብዙ ድካምና ጥረት ከባህሩ ዳር ተነስቶ እስከ ደላንታ ድረስ ወደ 6ሺ ስኩዌር ማይል የሆነ ቦታ በማሰስ ተሳክቶላቸዋል፡፡

ሀያ በሚባለው ቦታ ምንም በእርጥበት፣ በጉምና በጭጋግ ብንከበብም፣ ሆዳችን በፖርት ዋይን፣ ብራንዲ እና ንፁህ ጃማይካ ረክቷል፡፡ ይህም አስፈላጊ የሆስፒታል ዕቃዎችን ማከፋፈል የግድ አስፈላጊ ስለነበረ ነው፡፡ ዕቃዎቹን ለማጓጓዝ ብዛት ያላቸው የጭነት እንስሳት ስለሚያስፈልጉና ንብረቶችን በቦታው እንዲጠበቅ ከማድረግም ሰሰሚሻል ነበር፡፡

ከሀያ ወደ ፒላጎ፣ በዝናቡና በጭቃው ምክንያት አጭር ጉዞ ነው የተደረገው፡፡ አምስት የጭነት ዝሆኖች በጥይት ተመቱ፡፡ በጣም ደከመው ስለነበረ ይህን አማራጭ መውሰድ የግድ ነበር፡፡

በሚቀጥለው ቀን፣ ጦሩ ፒላጎን ለቆ ወደ ሙካን ሄደ ከዛም ወደ አፃላ፡፡ በዚህ ቦታ ስንደርስ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር አምባ አላጌ ላይ ትንሽ የመድፍ ተኩስ ወርወር ለማድረግ አስቦ ነበር፡፡ ምክንያቱም፣ የአምባው ጌታ በተቻለው መጠን በጭነት ተሽከርካሪ የሚሄደው ቀሰብና ጓዝ እንዲጓተት አድርጎ ስለነበረ ነው፡፡ ደግነቱ፣ ወልደየሱስ ከቦታው ተሰውሮ ስለነበር፣ አምባው ላይ መተኮሱ የሚፈለገውን ውጤት አያመጣም ነበር፡፡

ከአፃላ፣ ጄኔራል ናፒየር፣ የተሰባጠረውን ጦር ምንም ሳያቆም ወደ ሰሜን፣ ወደ ቤት፣ ጉዞ እንዲቀጥል አደረገ፡፡ የሚያስደስቱት የመሸከ ሜዳዎችንና የሚንቦሰቦሉትን ውሀዎችን አልፈን ሄድን፡፡ የሚያስፈራውና ለየት

ያለው፣ ከመስጊ በፊት የሚገኘውን ቦታ የአላጌን ሸለቆ እንዳለፍን አየነው:: በሚቀጥለው ቀን ለኛ እፎይታ፣ አንጣሎ የሚገኘው የተመሸገውን ካምፕ ማየት ቻልን:: ወደ ባህር በሩ በምናደርገው ጉዞ ግማሹ ላይ ነን:: የመጨረሻው የኋላ ብርጌድ በግንቦት 12 አንጣሎ ደረሰ::

ከመቅደላ እስከ አንጣሎ የነበረው ጉዞ፣ ለብዙ የትራንስፖርት መስመሩ የጭነት ከብቶች መሞት ምክንያት ሆኗል:: መንገዱም በነሱ ጢም ብሎ ነበር:: በማወዳደር፣ ከሞስኮው ሽሽት የነበረው ሁኔታ ለእንስሶቹ የከፋ በመሆን ከዚህኛው የበለጠም አልነበረም:: በመቶዎች የሚቆጠሩ የጋማ ከብቶች በየቀኑ ይሞቱ ነበር:: ግመሎቹ በቀላሉ ነበር የሚሞቱት፤ ዝሆኖችም ቢሆን በጣም ተሰቃይተዋል:: የፈረሰኛው ክፍል ፈረሶች በደርዘን ነበር የሞቱት::

የጀዳን ሸለቆ ማቋረጥና የዲልዲ ተራራ፣ የ700 እንስሳት ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል:: የመንገዱን ካርታ ላንዳፍታ ማየት፣ እነዚህ የተያያዙ ኮረብታዎች፣ ጓዝ ለተጫኑ እንስሶች እንዴት አድካሚ እንደነበሩ መረዳት ይቻላል::

ከአንጣሎ ተነስቶ ወደ ባህሩ ዳርቻ በሚደረገው ጉዞ ግን፣ ከዚህ ቀደም ሥርአት ያልነበረው የተደበላለቀ ጉዞ ሳይደረግ ተከፋፍሎ እንዲሄድ ተደረገ፤ እያንዳንዱ የእግረኛ ወይም የፈረሰኛ ሬጅመንት የተለያዩ የጉዞ ቀናት ተሠጠው::

ጦሩ አንጣሎ እንደ ደረሰ፣ የሚከተለው እጠቃላይ ትዛዝና ቴሌግራም ከኢንግላንድ ንግሥትና ከካምብሪጁ መስፍን ተልኮ ስለነበር በጠቅላይ አዛዡ አማካኝነት ለየሬጅመንቱ መኮንኖች ተነበበ::

የአንጣሎ ካምፕ ግንቦት 12፣ 1868

በዚህ ቀን በቴሌግራፍ የደረሰውን መልክት ጠቅላይ አዛዡ ለአቢሲኒያው ጦር ሲያስተላልፍ በከፍተኛ ርካታ ነው:: ስር ሮበርት ናፒየር፣ በዕዙ ስር ያሉትን ሁሉም ሰዎች፣ ሁላችሁም ላደረጋችሁት አገልግሎት ለጋስ የሆነቸው ንግሥት ቪክቶርያ ዕውቅና በመሥጠቷ እንኳን ደስ ያላችሁ ይላል:: "ንግስታችን ለሰር ሮበርት ናፒየርና ለጀግና ተዋጊዎች፣ ለተቃና ውጤታችሁ ከልብ የመነጨ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልከት ልካለች::"

የአንጣሎ ካምፕ፣ ግንቦት 12፣ 1868

የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ፣ በርሱ ትዛዝ ሥር ላሉ ወታደሮች የሚከተለውን፣ ከግርማዊ ፊልድ ማርሻሉ፣ ጠቅላይ አዛዡና ከተከበሩት የህንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በቴሌግራም የተላከውን መልክት ሲያነብ በታላቅ እርካታ ነው::

"በተጎናፀፋችሁት ታላቅ ስኬትና ቻይና ጀግና በሆኑት ወታደሮች ሁላችንም ተደስተናል።"

"ከቡርነትዎን በሙሉ ልቢ እንኳን ደስ ያለህ እላለሁ። እንደገናም፣ የትም ቦታ መሄድ የሚችልና ሁሉንም ማድረግ የሚችል ጦር ምን ማለት እንደሆነ አስተምረኸናል። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ፣ ሁሉም ነገር በሚገባ ነው የተከናወነው።"

ድፍን ኢንግላድን ያስደሰተው፣ ወደ አቢሲኒያ ውስጥ የዘለቀው የደስታ መልከት የመጀመሪያው ይህ ነበር። ግርማዊነቷ፣ ንግስት ቪክቶርያ በመደሰት ስር ሮበርት ናፒየርንና ከፍሴደሮቹን እንኳን ደስ ያለህ መልከት መላኳ፤ የካምብሪጁ መስፍን፣ ለአቢሲኒያ ዘማች ጦር በቴሌግራም ሰላምታ መላከን ጨምሮ ነው። ትንሽ ጦርነት ቢሆንም፣ ትልቅ ዘመቻ ነበር። በተራራ የተቆለፈች አቢሲኒያ ውስጥ ቢሆንም እንኳን ምንም አይነት የጥላቻ ስሜት አልተንፀባረቀም፤ ዝናው ደግሞ በጉልህ ሁኔታ፣ በመላው ኤስያ እንዲሰማ አድርጎታል። ተራርቀው የሚኖሩ ልዑሎችና፣ ሌሎች ገዥዎች ዝናውን ሰምተው መንቀጥቀጥ ጀመሩ። የሰላም ዘመን ቢሆንም የኢንግላድን ጉልበት እንዳላደከመው ተመለከቱ። ስለዚህ፣ ይህ የመጨረሻው፣ በጣም ጥሩውና፣ ከድሎች ሁሉ ታላቅ የሆነው፣ ምንም እንኳን ትንሽ ቢመስልም የኢንግላንድን ክብር ከዚህ ቀደም ከሆነው በላይ ጠንካራ መሠረት ላይ አስቀመጠው።

ሠራዊቱ ያለምንም ማቋረጥና ያለምንም ድካም ከአንጣሎ ወደ ሰናፌ መንገዱን ቀጠለ። የነበረ አንድ ሞት የእቴጌ ጥሩነሽ ነበር፤ የሞተችውም በሳንባ በሽታ ነበር። ቀብሯ ላይ በእቴጌዋ ዘመዶች ጥልቅ የሆነ ሀዘን ነበር የታየው። በግንቦት 15 ሞታ፣ አይኩለት የሚባል ቦታ ተቀበረች[160]። "የንጉሡ ጦር" የወታደር ባንድ፣ አስከሬኑ ወደ መቃብሩ ሲሄድ ፊት ለፊት እየተራመደ፣ 'Dead March in Saul'፣ የሚባለውን ሙዚቃ ተጫወተ። ከአስከሬኑ ሳጥን አጠገብ፣ የማይተካ ሰው ሕይወት በማለፉ ደንገጡሮችዋ ለቅሶና ከባድ የሀዘን ስሜት ነው ያሳዩት። ከኋላ ከእቴጌዋ ቤተክርስቲያን ወገን የሆነው የቀብሩን ስርአት የሚመራው ቄስ ይከተላል፤ ወጣቱ ልዑል ከሚስተር ራሳም ጋር ሆኖ፣ የጠቅላይ እዛዡ ጽ/ቤት ረዳት፣ ብዛት ያላቸው ረዳቶቹ፣ ብዛት ያላቸው አቢሲኒያውያን ይከተላሉ።

---

160 ኢጋጣሚ ሆኖ የእቴጌዋ አያትም እዚህ ቦታ ነበር የተቀበሩት።



የእቴጌ ጥሩ ወርቅ የቀብር ሥነ ሥርአት
(Roger Acton)

አቴጌዋ ከትንሹ ልጇ[161] ጋር ሆና ወደ ቦምቤይ ለመሄድ ነበር ያሰበችው፤ ሰር ሮበርት የመከራትም ይህንኑ ስለነበር፣ የተሻለ አማራጭ ነው ያለችው መንገድ ነበር።

ወጣቱ ልዑል አለማየሁ አሁን ወላጅ አልባ ሆነ[162]። ነገር ግን እሱን በሚመለከት ተወስኖ የነበረው የጦር አዛዡ ሃሳብ አልተቀየረም እንዲያውም ተጠናከረ።[163]

ወደ አቢሲኒያ የዘመተው ሠራዊት የመጨረሻው ክፍል በግንቦት 24 ሰናፌ ደረሰ። ከአንጣሎ ጀምሮ ወደዚህ ከፍተኛ ቦታ ላይ ወደነበረ ካምፕ መጓዝ ምንም አሰልቺ ቢሆንም፣ በየቀኑ፣ የዘመቻው መጠቃለያ ለመቃረቡ ምልክት ነበር። ባህሩን እየተቃረብን እንደሆነ፣ እናም አንዴ ባህሩ ላይ ከሆን፣ ወደ ቤት፣ ከፊት ለፊታችን ወደ ውድ ቤት የምናደርገው ጉዞ ሩቅም አይሆንም።

ከስድስት ወራቶች በፊት፣ ወታደሮቹ በልባቸው የብረት ያህል ጥንካሬ ይዘው፣ ለሚደረገውም ነገር አእምሯቸውን አዘጋጅተው ነበር ሰናፌን ለቀው የሄዱት። የመጀመሪያው ጣቢያችን ሰናፌን ከለቀቀን በኋላ ሁለት ዙር ሰብል ታጭዷል። አሁን ደግሞ ምርት የደረሰበት ወቅት ስለሆነ የበቆሎ ቅጠልና ፍሬ ለሶስተኛ ጊዜ ደርሷል።

የትግሬውን መሰፍን ካሳን፣ ሆን ብዬ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ሳላነሳው በፀጥታ ያቆየሁት ሰው፣ የኔን ትውስታ እንደገና ማግኘት ይገባዋል። ታማኝ አጋዥና ታማኝ ሰው ነበር። በመጀመሪያ ጊዜ በህውዜን፣ ከወራጅ ውሃ አጠገብ ቃል ከገባ ወዲህ ቃሉን ሳያጥፍ ነው የቆየው። በልዑሉ በኩል የተደረገ ማናቸውም ነገር በራሱ በልዑሉ ነው የተደረገው። ያለማሰለስ፣ የእንግሊዙን ጄኔራል አላማ ለማሳካት ይጥር ነበር። በብልሃት፣ ጥንካሬ በተሞላበት ሁኔታ የሚያስፈልገውን ርዳታና ለሰውም ለእንስሳም የሚሆነውን ቀለብ ሰበሰበ። ቅንጣት ያህል ሥራውን የማጓደል ሁኔታ አልታየበትም። የሚያስፈልገው የምስጋና ቃል የሚገባውም ነበር። ዋግሹም ጎበዜም ቢሆን እንደ መሰፍኑ ሙሉ ቃል ነበር የገባው። ነገር ግን፣ የገባው ቃል ለእንግሊዙ ጄኔራል ፍሬ አልባ ቃላቶች ብቻ ነበሩ። በግዛቱ፣ በላስታና በሰሜን በነበረበት ጊዜ፣ ጄኔራሉ፣ የጎበዜን የውሸት ጓደኝነትና የማይታመን አለመሆኑን ሙሉ በሙሉ ያወቀ መሆኑን መናገር አይቻልም ነበር። ነገር ግን፣ ግልፅ የሆነው፣

---

161 ስለ ልዑል አለማየሁ (በምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች)

162 አያቱ ለልዑል አለማየሁ የፃፉለት ደብዳቤ (በምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች)

163 (በምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች)



ወላጅ አልባ የቀረው ልዑል አለማየሁ
(Roger Acton)

የወንዱና ቃል ጠባቂው የትግሬው ልዑልና ያደረገው ትብብር በእዛዡ እእምሮ ብልጭ ይላል፡፡ ሰለዚህ፣ በርግጥ፣ ልዑል ካሳ ውሊታና ወዳጅነቱ የኔ ይሁን ብሎ መጠየቅም አያሰፈልገውም፡፡

የእንግሊዝ ሠራዊት ሰናፌ እንደ ደረሰ በሁለተኛው ቀን፣ ልዑል ካሳ ከሶሰት መቶ ምርጥ ፈረሰኞች ጋር በመሆን የእንግሊዝን ሠራዊት ለመሰናበት መጣ፡፡ በናፒየር የተሳካ ውጤት በጣም ደሰተኛ ነበር፤ እናም ጄኔራሉን ባለ የእቢሲኒያ መዝገበ ቃላት መያዝ በሚችለው ቃላቶች በሙሉ ምሥጋናውን ደረደረለት፡፡ ለናፒየር ያለውን ምኞት ለመግለፅ እንዲህ እለ፣ "የመንግሥተ ሰማይ ሁሉ ደስታ ይሰጥህ፣ ያገርህን ሰዎች አድናቆት፣ ከፍ ያለ ማዕረግ፣ ብዙ ሚሰቶችና ልጆች ይሰጥህ፤ ዕድሜ ይሰጥህ፤ በፓትርያርኩ፣ በእብርሃም፣ በይሰሐቅና ያዕቆብ በቀኝ ጎን ያሰቀምጥህ፡፡" ፀሐፊውም እሜን! እለ፡፡

ያለምንም ጥርጥር፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ምንም እንኳን የእንግሊዝ ጄኔራል ቢሆንም፣ ቀዝቀዛ የሆነውን ሥነ ሥርአት እርግፍ አድርጎ ትቶ፣ ለደማቅ ምሰጋናው መልስ በመሰጠት ላሳየው ታማኝነትም በፍቅር እቀፈው፡፡

የንግሥቷን ልደት ለማከብር በሰናፌ ሌላ የተካሄደ ሥርአት ነበር፡፡ የወታደሮቹ የሚደነቅ ስልት የተመላበት ትርኢት የልዑሉን የጋሰ አድናቆት ነው የቀሰቀሰው፡፡ እሱም ቢሆን በጄኔራል ናፒየር ፊትና በረዳቶቹ እንዲሁም የሌላ ሀገር መኮንኖች ባሉበት ጥሩ ሰሜት ለማሳየት ባለው ፍላጎት፣ የራሱን ሰዎች በሁለት መሰመር ካሰለፈ በኋላ የውጊያ ትርኢት ማሳየት ጀመረ፡፡

ልዑሉ የራሱን ድርሻ በደንብ ነው የተወጣው፤ በተለይም የፈረስ ግልቢያ ችሎታው ከምንም በላይ በጣም ጥሩ ነበር፡፡ እንዴ ምልከት ከተሠጠ በኋላ የውጊያ ትርኢቱ ተጀመረ፡፡ በዚህ ትርኢትም እያንዳንዱ ሰው ለነበረው እሰላለፍ ደንታ ሳይለጥ ወደ ተቃራኒው ገሰግሶ ይሄድና በጦሩ በድልድሙ በኩል ከፊት ለፊቱ የመጣውን ማንኛውንም ሰው ያጠቃል፡፡ የሚሸሹት ወገኖች ደግሞ ወዲያው እንደታወቁ፣ እየሸሹም ቢሆን አደገኞች መሆናቸውን ለማሳየት ገና መሸሸት ሲጀምሩ፣ እንደ ፓርቲያን፣ ጥይት የሚተኩሱ እየመሰሉ በሜዳው ይሮጣሉ፡፡

ላሳየው ጥሩ እምነት፣ ሰር ሮበርት ናፒየር ለካሳ በጣም ዋጋ ያለው ሽልማት ሰመሰጠት ደሰተኛ ነበር፤ በተለይም እንደሱ በጣም ጠቃሚ ለሆነ ሰው፤ ሰለዚህ 1500 በእፈሙዝ በኩል ባሩድ የሚገባበት ጠመንጃ፣ Brown Besses[164]፣ 400 ሺ ጥይቶች በካርታ፣ ሰድሰት መድፎች ከነእርሳሳቸው ነበሩ፡፡

---

164 የእንግሊዝ ወታደሮች ነፍጥ



የንግሥቷን ልደት በማክበር በሰናፌ የተደረገ ሠልፍ
(Roger Acton)

በዚህ በሚደነቅ ሥጦታ፣ ወራሪ ግብፆች ላይ ብድሩን መመለስ እንደሚችል ምንም ጥራጣሬ አይኖርም፡፡እነዚህ ግብፆች ለረዥም ጊዜ ይህ ነው የማይባል ወንጀል ያለምንም ገደብ አቢሲኒያውያን ላይ ሲያደርሱ ነበር፡፡ ካሳ፣ ከሱ ጋር መመለስ ከፈለጉ በርከት ያሉ አውሮፓውያን ጋር በመሆን እንግዲህ ዋግ ሹም ጎበዜና ግብፆች ላይ፣ ራሱ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችላል፡፡

ጦሩ ለመመለስ ከመነሳቱ ሶስት ወይም አራ ቀናት ቀድሜ፣ አምስት፣ ዳዝና የተወሰዱ ንብረቶች ከተጫኑ ከብቶች ጋር በሰናፌ ቁልቁለት መውረድ ጀመርኩ፡፡ አብረውም ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ነበሩ፡፡ ማለፊያው፣ ያን ጊዜ ወደ ዘመቻው ስመጣ የነበረውን ይመስላል፤ ነገር ግን በሃሳቤ፣ ወፎቹ የእንኳን ደኅና መጣችሁ የሚል የደስታ ፉጨት የሚያሰሙ መሰለኝ፡፡ በጣም ቀጥ ያሉት ቁልቁለቶችም ብዛት ባላቸው ቁጥቋጦዎች ተሸፍነው በጣም አረንጓዴ መስለው ይታያሉ፤ ከብርሀኑም ጋር ተጨማሪ የደስታ ስሜት ይፈጥራሉ፡፡ እኩለ ቀን ሲሆን ራያ ጉደ የሚባል ቦታ ደረስን፤ ለአንድ ስአት የሚሆን ካረፍን በኋላ የቁልቁለት መንገዳችን ቀጥለን ጠመዝማዛ መንገዶችንና መታጠፊያዎቸን በትግስት ካቆራረጥን በኋላ እንደል ዌልስ ደረስን፡፡

በሚቀጥለው ቀን፣ ገና ሳይነጋ፣ የተሠራ ቁርስ ከበላን በኋላ መንገዳችን ቀጥለን እኩለ ቀን ሲሆን የላይኛው ሶሮ የሚገኝ ጣቢያ ደረስን፡፡ በዚህ ቦታ፣ ከብቶቻችን ሲመገቡና የኛም ምሳ ሲሰራ ለሁለት ሰአታት አረፍን፡፡

ከቀኑ ሰምንት ስአት ሲሆን፣ የኔ ትንሹ መንገደኛ ቡድን እንደገና መንገዱን ቀጠለ፡፡ ከኋላችን ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ መኮንኖች ከነጭነት ከብቶቻቸው ይከተሉናል፤ እነሱም እንደኔ ዙላ ለመድረስ በጉጉት ላይ ነበሩ፡፡

ሙቀቱ በዚህ ስአት በጣም የተጠናከረ ነበር፤ ይህም፣ በተለያዩ ነጭ የአለት ግድግዳዎች ላይ የሚንፀባረቀው ብርሃን ስለተጨመረበት ነው፡፡ በነዚህ ግድግዳዎች መሀል ነው ጠመዝማዘው የሶሮ ማለፊያ የሚሄደው፡፡ ለሁለት ማይሎች ርቀት፣ የሶሮ የመንገዱ ስፋት ሰላሳ ጫማዎች ቢሆን ነው፤ ከዚያ በኋላ፣ ለአምስት ማይሎች ርቅት፣ የማለፊያው ጎን ስፋት በየሥፍራው ወደ ሃያ ጫማዎች ይጠባል፤ ቀጥ ያለው የአለት ግድግዳ ወይም ቋጥኝ ወደ ላይ ስምንት መቶ ጫማዎች ከፍታ አለው፡፡ መንገድ እየገፋን በሄድን ቁጥር ሙቀቱ እየጨመረ ይሄዳል፤ ፀሀይዋ ደግሞ በሚሸሸ ደመና ስትጋረድ አስተዋልኩኝ፡፡ የሚጋረፍ ነፋስ አልፎ አልፎ እኛን እያለበሰን ያልፋል፡፡

ከሶሮ መግቢያ ሶስት ማይሎች፣ የእውሎ ነፋስ መምጣትን የሚጠቁሙ እነዚህ ምልክቶች ከኋላችን በሚከተሉን ቡድኖች በጭንቀት ነበር የተስተዋሉት፡፡ ድንገት፣ የሚታጠፈውን፣ በሸለቆው ውስጥ ያለውን መንገድ

እንደዞርን፣ ብዛት ያላቸው ወደ ሺ የሚሆኑ መኮንኖችና ሲቪሊያኖች በነፍስ አውጭኝ አይነት ሩጫ ወደኛ ሲመጡ አገኘናቸው፡፡

እርስ በርሳችን እየተቀራረብን ስንመጣ፤ መኮንኖቹ ወደ ሶሮ ማለፊያ እንድንመለስ ወደኛ ይጮሃሉ፤ የሚሉትም፣ ከዚህ በፊት ውሃ ያልነበራቸው ጉድጓዶችና ሥንጥቆች በውሀ ስለተሞሉ ወደፊት መሄድ አይቻልም፡፡

እንደሚሉት ከሆነ፣ ከመንገድ ሠራተኞች ጋር በመሆን ጦሩ ከስናፌ ሲመጣ ማለፍ የሚችልበትን መንገድ እየሠሩ ነበር፤ ነገር ግን ወደላይ ወደ ጣቢያ እንዲመለሱ ተገደዋል፡፡ ምክንያቱም በዝናቡ ጊዜ ማንም ህይወት ያለው ፍጥረት በማለፊያው ውስጥ መቆየት አይችልም፤ ዝናብ ከጣለ፣ በሶስት ሰአታት ውስጥ የእስር ጫማዎች ጥልቀት ድረስ ጎርፍ ስለሚሞላውና በተጨማሪም መቶ ፓውንድ ድረስ የሚከብዱ ትልልቅ ድንጋዮችን ውሀው በድንገተኛው ጎርፍ እያንከባለለ ስለሚወስድ ነው፡፡

ጎላ ያሉት ደመናዎች፣ የተሸፋፈነው አየር፣ ባጠቃላይ የሚታየው ጨለማ ሁኔታ፣ ያለ ምንም ጥርጥር በቀን የሚከሰተው የዝናብ ማዕበል መምጣቱን ይጠቁማሉ፡፡ እናም አሉ፤ አሁንም ቢሆን ሶሮ ለመድረስ አዳጋች ነው ምክንያቱም በማለፊያው የውሃው ጥልቀት ሁለት ጫማዎች ይደርሳል፡፡ ከልባቸው የተቃወሙበት ሁኔታና የሚከሰተው ችግር በኔ ኮምፓኒ ውስጥ በነበሩ መኮንኖች ላይ ተገቢ ውጤት ነው ያሳየው፤ እናም ወደኋላ ወደ ዲፓው ተመለሱ፡፡ እኔ ግን ወደፊት ለመግፋት ወስንኩኝ፤ የነበረው ምክንያት ደግሞ፣ ደብዳቤ የምታመላልሰው መርከብ በሚቀጥለው ቀን ማታውኑ ከዙላ ወደ ሱዊዝ ስለምትሄድ ነው፡፡ ስለዚህ የግማሽ ቀን መዘግየት ደግሞ በጊዜ ዙላ ለመድረስና ለመጓዝ የማድርገውን ዝግጅት ስለሚያስተጓጉልብኝ ነው፡፡ የመንገዱ ርቀት ደግሞ ባልለሰለሰው መንገድ ላይ ሰላሳ ማይሎች ነበር፡፡ እንግዲህ እኔን ወደጥፋት የሚሄድ ሰው ነው ብለው በማመን መኮንኖቹ ወደ መንገዳቸው በፍጥነት ሄዱ፡፡

የአየርላንድ ወታደሮች ሁልጊዜም ቢሆን በነገር ለመጎሸም ዝግጁ ስለሆኑ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው የሹፈት ሰላምታ ሰጡኝ፤ ለሁሉም፣ መልሴ በደግ ሁኔታ በቀልድ መልክ ነበር፡፡ በእእምሯቸውም፣ ከአስር ሰአታት በኋላ እኔ ራሴን "በደቪ ጆንስ ሎከር" (Davy Jonese Locker)[165] ውስጥ ነው የማገኘው ብለው እምነዋል፡፡ አንዳንዶቹ ከሰተር ብለው ከኔ ጋራ በሀይል ተከራከሩ፡፡ ምናልባትም፣ "የወደደ ሰው በራሱ መንገድ ይሂድ"፤ የሚለውን አባባል አስታውሰው ይሆናል ትተውኝ ሄዱ፡፡ የጉልበት ሠራተኞቹም ቢሆኑ

---

165 የባህር ወለልን ለመጥቀስ የእንጋር ዘይቤ፤ ማለትም በባህር ውስጥ የሰመጡ መርከበኞች አሟሟትን ሁኔታ ለመግለፅ የሚጠቀሙበት አባባል ነው፡፡

ባንድ ደምፅ፣ ራህ ናሂን፣ ሳሂብ ሳሂብ፣ (ጌታው፣ መንገድ የለም) ብለው ጮሁ፤ ነገር ግን ጩኸታቸው በተደፈነ ጆሮ ማረፉን ሲያዩ፣ እነሱም ቢሆን የያንኪውን ጌታ ለመጨረሻ ጊዜ ነው የምናየው በማለጥ ስላረጋገጡ፣ ኩሁዳ ሃፊዝ፣ ሳሂብ፤ (ፈጣሪ ይጠብቅህ!) በማለት መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ስለፀሎታቸው አመሰግኘ፣ በፍጥነት እንዲጋልብ ፈረሴን መግረፍ ጀመርኩ፡፡

በሁለቱ የማለፊያው ግድግዳዎች ላይ ያለው የሰማይ ጥለት ጥቁር በሆነ የከፋይ መጋረጃ የተከተረ መሰለ፤ እናም የመንገድ ሠራተኞቹ የመጨረሻው ቡድን በማለፊያው ውስጥ ለእይታ ከመሰወሩ በፊት ዝናብ መጣል ጀመረ፡፡

ዝናቡ ቀስ እያለ መውረድ ጀመረ፤ በጠጠሮችና በድንጋዮች ላይ የሚያርፉት የዝናቡ ጠብታዎች የማር ተሬዛ ዶላር ያክክሉ ነበር፡፡ ቀጥሎ ግን ዝናቡ እየፈጠነና እየገዘፈ መሄድ ጀመረ፡፡ የሚያጉረመርመው ነጎድጓድ፣ መጀመሪያ፣ የእንጨት ደልድይ ላይ መድፍ ሲተኮስ እንደሚሰማው መርገብገብ ዝቅ ያለ ድምፅ ነበረው፤ ነገር ግን ድንገት ተለውጦ ከፍ ያለ ድምፅ ማሰማት ጀመረ፡፡ መንትያ ብልጭታዎች ገሃድና እስፈሪ መሆን ጀመሩ፡፡ ደመናዎቹ ራሳቸውን ሲገላለጡ የመንግሥተ ሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ፤ ዝናቡም ያለማቋርጥ እንደ ጎርፍ ወረደ፡፡

ለህይወታችን ስንል፣ ውሀ በሞላባቸው ጉደጓዶች እየተንቦራጨቅን፣ ውሀ ገና ያለሞላባቸውን ጉድጓዶችን በላያቸው ላይ እየዘለልን፣ በትልቅ ድንጋዮች ዙሪያ፣ በሚያዳልጥ አለት በግልቢያ ወደፊት ገሰገስን፡፡ ማዕበሉ እስከሚያልፍ መቆየት የምንችልበት ወጣ ያለ መጠለያ የሚሆን አለት ለማግኘት ሳናሰልስ ዙሪያውን እየተመለከትን ነበር፡፡

በቅፅበት ቆዳችን ድረስ ብስብስ ብለናል፤ የባህር እሳ ይመስል ውሀው ከላይችን ላይ ይወርድ ነበር፡፡ ዳዙም በዝናቡ በጣም ስለራሰ እንስሶቹ መሸከም የማይችሉት ጭነት እየሆነ መምጣቱ ግልፅ ሆነ፤ ድንኳን የተሸከመው በቅሎ በከብደቱ ምክንያት መንገዳገድ ጀመረ፡፡ የቴዎድሮስን ምንጣፍ የተሸከመውም ድንገት ጀርባው የተሰበረ መሰለ፡፡ መንገዱ በወራጅ ውሀዎች ተሞላ፤ የውሀው ፈሰስ ፍጥነት ጨምሮ እየገዘፈ በመምጣት በጥልቀት እየጠረገ መውረድ ጀመረ፡፡ እስካሁን ድረስ፣ እይጥ እንኳን መጠለል የሚችልበት ቦታ የሚሆን ምልክቱም የለም፤ በጎንና በጎናችን ያለው ግድግዳ ልክ በመሰመር ወደላይ የተገነባ ይመስል ቀጥ ያለ ነበር፡፡

ከእያንዳንዱ ግድግዳ እናት ላይ፣ ውሀው ቀጭን መስመር በመስራት የቀለጠ መስታውት መስሎ ወደታች ይወርድ ነበር፡፡ ነገር ግን ገና ሀሳባችን ሳንቀይር፣ እነዚሀ ቀጠን ብለው የሚወርዱት ውሃዎች ወደፏፏቴ በመቀየር በሁለቱም ግድግዳዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ይወርዱ ጀመር፤ በሚወርደው ውሀ

የተፈጠረው ነጎድጓድ የመሰለ ድምፅ ራሱ ጆሮ የሚያደነቁር ነው የሆነው፡፡ ይህ አዲስ የተፈጠረው አደጋ በቀጥታ አስጊ መሆኑን ግልፅ አደረገ፤ ዛሁሩካ የሚባለው አንደኛው የሂንዱስታን ሠራተኛዬ በግድየለሽነት ግድግዳውን ተጠግቶ ወደሚወርደው ወደ አንዱ ፏፏቴ ስር ሄደ፤ አናም አንደኛው ወራጅ ውሀ በቅፅበት ከመሬቱ ጋር አላተመው፤ የተፈጠረው ወራጅ ውሀ ጉልበት እያገኘ ስለነበር ልክ በቀስት አንተወረወረ ፍላጻ በትልልቅ አለቶች ላይ እየገፋ ወስዶ ከኛ ትንሽ ርቀት ላይ በሚገኝ የውሀ ኩሬ ውስጥ ወረወረው፡፡

በፍጥነት በተደረገለት ርዳታ ህይወቱ ተረፈች፤ ነገር ግን ጭንቅላቱ ላይ ቆስሎ ሰውነቱ ደግሞ ተላልጦ ነበር፡፡ የኩሬው ውሀ የኔን ቡድን አስቆመው፤ ወደፊት መሄድ አልቻልንም፡፡ ኩሬው ሲመረመር፣ የ8 ጫማዎች ጥልቀትና የ50 ጫማዎች ርዝመት ነበረው፤ ርዝመቱ ደግሞ ማለፊያውን ዳር አስከዳር ይሸፍናል፡፡ ዳሩና ጎኖች ለዘመናት በሚወርደው ጎርፍ ውሀ ምክንያት የለሰለሰ፣ አንደ ሀውልት የቆመ አለት ለአስር ጫማዎች የሚሆን ርዝመት ወደ ኩሬው ገባ ብሎ ይታያል፡፡ በዚህ አለትና በማለፊያው ግድግዳ መሀከል የአምስት ጫማዎች ስፋት ያለው ክፍት ቦታ ይገኛል፡፡ በቦታው ከፍ ባለው አካባቢ፣ መሬቱ በሚሸረሸር አሸዋማ አፈር ነው የተሞላው፤ የዚህ አሸዋማ አፈር ልል ስለሆነ በሀይለኛ ጎርፍ እየታጠበ በመሸርሸር ወደ ባህር ከመሄድ የሚያስጥለው መከላከያ የለውም፡፡

በዚህ አለት ላይ ቡድኔን ሰበሰብኩበት፡፡ ለኛ፣ የእውነትም የመዳኛ አለት ነው የነበረው፤ ነገር ግን የእንግሊዝ መኮንኖች እንዳሉት፣ ውሀው ማለፊያውን አጥለቅልቆ የአስር ጫማዎች ጥልቀት ያለው ጎርፍ ከፈጠረ፣ የነበረን አማራጭ ሌላ ሳይሆን ፈረሶቻችንን ከስር ሆነው በሰአት ሀያ ኖት[166] ፍጥነት መዋኘት ነበር፤ አለዚያ ደግሞ መስመጥ ነው፡፡

አእምሯችን ባጋጠመን አደጋ ተወጥሮ እያለ፣ አሁን መጠጊያ ስላገኘን የአደጋዎቹ ተፈጥሮና መጠን ግልፅ አልነበረም፡፡ ስለዚህ የነበረን አማራጭ በዚህ መጠጊያ ሥፍራ ያለምንም አንቅስቃሴ መቆየት ነበር፡፡ ስለ አደጋዎቹ የነበረን ዕውቀት፣ አደጋ የተጋረጠ እንስሳ ጎርፉን እንዴት ማምለጥ እንደሚችል በሀሳብ የተወጠረ አንጎል ማሰብ የሚችለውን ያህል፣ ምንም በቅጡ የሚታወቅ ሁኔታ ሆኖ አልነበረም የቀረበልን፡፡ አሁን ግን መጠለያ ስላገኘንና ከድንገተኛ ሞት ስለተረፍን፣ አአምሮዬ ወዲያውኑ ስለዚህ የጎርፍ አደጋ ሁኔታ አመጣጥ ማንሰላሰል ጀመረ፡፡ ስለ ሁኔታው በጥልቅ ለመዘርዘር ቦታው አይደለም፤ ነገር ግን ለአንባቢ በሚበቃ ዝርዝር፣ ይህ ድንገተኛና ሀይለኛና የሚጠራርግ ጎርፍ፣

166 ኖት(knot) በውሃ ላይ የፍጥነት መለኪያ ነው፡፡ 1 knot 1.8 ኪሎሜትር በሰአት ነው፡፡ ስለዚህ በሰአት 38 ኪሎ ሜትር ፍጥነት መዋኘት ነበረባቸው፡፡

የ800 ጫማውች ጥልቀት ሲፈጥር ማረጋገጥ እንደቻልነው፣ እመጣጡ ከመቶ ማይሎች ርቀት ባሉ ቦታዎች የተጠራቀመ ዝናብ ነበር፤ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ፈፋዎችና ትንንሽ ሸለቆዎች የነበራቸውን ውሀ በሙሉ ወደዚህ ውሃ ወደ ባህሩ ለመውረድ ዋና መንገድ ወደሆነው ወደ ማለፊያው ስለተፉም ነበር።

በተፈጥሮው ሰው በአደገኛ ሁኔታ ሲከበብና በዚህም ምክንያት ሰውነትና እእምሮ መንዳት ሲጀምሩ፣ ለረዥም ጊዜ መፈላሰፍ አይችልም። የሚወርደው ውሃ የሚፈጥረው ጎርፍ ሀይል በፍጥነት ወደሚያጥለቀልቅ ትልቅ ውሀ ከፍ እያለ ሲሄድ ተመለከትን፤ ዝናቡ ካልቆመ በስተቀር በዚህ ሁኔታና ዕይታ የኛ ዕጣ እየተወሰነ ነው የሚሄደው። ምርር ባለ ሁኔታ፣ የሠራተኞቹ ቡድን የሠጡኝን ማስጠንቀቂያ ባለመስማቴ ያደረብኝን ፀፀት እኔ ራሴ ነው የማውቀው። ቦታውና ጊዜው በጣም መጥፎ ስለነበር፣ ትርጉም የሌለው ፀፀትን ለማስተናገድ የሚሆንም እልነበረም። ለኛ ማድረግ የምንችለው የቀረ ነገር ቢኖር በታቻለ መጠን ትግስተኛ መሆን ነበር፤ በሚቆረቁር አይን እየጨመረ የሚሄደውን ጎርፍ ማየት፤ የሚያሰማውን የሚያጓራ ድምፅ በሽብር መስማት፤ እናም የሁኔታውን ትልቅነት ሁላችንም እያደነቅን ነበር።

ዝናቡ ቁልቁል ያለማቋረጥ ይወርዳል፤ በላያችን ላይ ደግሞ ጆሮ የሚያደነቁረው የነጎድጓድ ድምፅ ይሰማል፤ ከግድግዳ ግድግዳ እየነጠረ ሲቀባበል ደግሞ በሺ ዕጥፍ ሆኖ ነበር የሚሰማው፤ ከዚህም ጋር ብልጭታው በአረንጓዴ ነበልባሎች በእያንዳንዱን የጋራ እናትና የገደል ጠርዝ ላይ ብርሃን ያበራ ነበር።

የውሀ ንጣሮች አሁንም ወደታች ይወርዳሉ፤ አሁን ግን ብርማ ቀለም ካለው አረፋ ጋር ነው። ወደፊትና ወደታች፣ ማለፊያው፣ የሚገነፍለውን ጎርፍ ያሽከረከረዋል። ከአሁን እሁን ወደላይ ከፍ ከፍ እያለ እኛ ከቆመንበት የእለት ንጣፍ በስተቀር በፊት ለፊቱ የሚየገኘውን ሁሉንም ነገር ተሸክሟል፤ አሽቀማውን መሬት በቶን በሚሆን መጠን እየሸረሸረ፤ በመታጠፊያ ቦታዎች እየተንበጫረቀና እየተወረወረ ሰብስብ ይልና የሚገደብው ነገር ካለ ደግሞ አረፋ ይፈጥርና በላዩ ላይ ፈጣን ፏፏቴ በመፍጠር ነጫጭ ቁልቁል የሚረወሩ የውሃ ወራጆች እየሰራ እንደገናም ኩሬዎች ይፈጥራል፤ ይህ ሁሉ ሲሆን፣ እሰር ሺ የሚሆኑ ለጦርነት የሚቀሰቅሱ ታምቡሮች ያክል የሚያጓራ ድምፅ ያሰማ ነበር።

እነዚህ የማያቋርጡ ድምፆችና በተራቸው በብዛት የሚነጥሩት ገደል ማሚቶዎች ጠንካራ የሚባለውን ሰው እንኳን የፍራቻ ስሜት ይፈጥሩበታል፡ የኔ፣ የአረብና የሂንዱ ሠራተኞች ከዚህ በምንም ርቀናል ማለት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ነው ያሉት። የነበረባቸውን ፍርሃትና መጠን እልባ የነበረውን ስጋት በማያቋርጥ ጩኸት ነበር የገለፁት።

አሁንም ቢሆን ዝናቡ ያለማቋረጥ እይወረደ ፊታችን ይገርፋል፤ በውሃ ፍንጣሪም አይናችን አውሮናል፡፡ የውሃው ማዕበል ከፍ እና ወደላይ ከፍ እያለ፣ በእያንዳንዱ ቅፅበት እየጨመረ፣ በእያንዳንዱ ጠብታ ደግሞ ጉልበቱንና እሸባሪነቱ እየጨመረ ነበር፡፡ በማለፊያው፣ ሰስት ጫማ ጥልቀት ያለው ወራጅ ውሀ ነበር፡፡

የጎርፉ ወራጅ ማዕበል ወደ ሀይለኛና ግዙፍ ወንዝ ተቀይሮ መገደብ በማይቻል ፈሰሰ ወደኛ እየወረደ ነው፡፡ ፀጥ ብሎ የሚወርደው ውሀ፣ እኛ እጠገብ ሲደርስና ከቆምነበት አለት ጋር ሲጋጭ መንቦራጨቅ ይጀምራል፡፡ ከዚህ በፊት እንደሆነው ሁሉ፣ ወደ እለቱ ለመምጣት የተራመድንበት አሸዋማ መሬት ጎርፉ ጉልበት ሲያገኝ ተሸርሽሮ ሄዷል፡፡ እኛም እንግዲህ በምንም መንገድ ቢሆን ከአደጋ ነፃ ነን ማለት አንችልም፡፡ ውሃው በፍጥነት ከፍ እያለ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ከአለቱ የሰምንት ኢንች ርቀት ነው ያለው፤ ግን በተደረገው ሰሌት ለግማሽ ሰአት ተጨማሪ ዝናብ ቢወርድ አለቱን በሶስት ኢንች ጥልቀት ያለብሰው ነበር፡፡

በነዚህ ከፍታዎች ተከበን፣ የአለም መጨረሻ በመሰለ ሁኔታ ሀይለኛ የሆኑ የፏፏቴ ወራጆች ጋርደውን፣ ወደላይ በግርማ ሞገሰ በሚተኑት ውሃዎችና በሚፈነጠቀው ውሀ ፅልመት ተውጠን፣ የኛ ሁኔታ በእውነት የሚያላዝን ነበረ፡፡

በሚታየው እሰቃቂ ሁኔታ ላይ ለመጨመር፣ ከሚገነፍለው ውሃ በላይ፣ እጃቸው የተዘረጋ የሰዎች እሰከሬኖች እየተንሳፈፉ እያለፉን ይሄዱ ጀመር፡፡ የበሬ፣ የፈረስና የበቅሎ ሬሳም ቢሆን እርሰ በርሰ እየተላተመና እንደመሰናከል ከተቀመጡ አለቶች ጋር በሀይል እየተጋጨ አብሮ ይወርዳል፡፡ የቴሌግራፍ ምሰሶዎችም ከኋላቸው የቴሌግራፍ ሽቦዎችን እየጎተቱ በብርሃን ፍጥነት አልፈውን ይሄዳሉ፡፡ ጋሪዎችና የጋሪዎች ጎማ እኛ ከተጠለልነበት አለት ጋር ይላተማሉ፡፡ ድርቆሽ፣ የገለባ ክምር፣ ቁጥቋጦዎች፣ እንደገናም የሰዎች እሰከሬኖች በሚገነፍለው ወራጅ ውሰጥ ተደበላልቀው ይመጣሉ፡፡

በዚህ አውሬ በሆነ ተፈጥሮ የሚታየው ጥፋትና ሞት እሰፈሪ ምሰክርነት የኔን ሠራተኞች ሽብር ጨምሮታል፤ እናም በሚያሰቀቅ ጩኸት ለአላህ የሚያሰሙት ፀሎት ከማዕበሉም ሆነ ከጎርፉ በላይ ይሰማ ነበር፡፡

ለአንድ ለአት ከአርባ አምስት ደቂቃዎች ያለማቋረጥ ከዘነበ በኋላ ለእፍታ ያህል ጋብ አለ፡፡ እንደገና ሲጀምር ግን ከመጀመሪያው በበለጠ ሀይለኛ ሆኖ ነበር የተመለሰው፡፡ ውሀው ከቆምንበት አለት ከፍተኛው ቦታ ጋር እኩል ሆነ፤ እንደገናም እየጨመረ ነበር፡፡ በውሀው የተፈጠረው ጭጋግ እየለቀቀ ሰለነበር ወደላይ አንጋጠን ተመለከተን፡፡ የፀሀይ ብርሃን ፍንጣቂዎች

ጨለም ባለው ጭጋግ በሰርቆሽ እየገቡ ያልፉ ነበር፤ እንደዛም ሲሆን የዝናቡን ጠብታዎች የተለየ የሚያንፀባርቅ ገፅታ እየፈጠሩባቸው ነበር፡፡ ከእናቱ ላይ የተወሰነ ቁጥቋጦዎች መኖራቸው ለኛ መታየት ጀመረ፤ ልክ በዘላለም ሞት አፋፍ ላይ እንደንተንጠለጠለ ነፍስ፣ በወጀቡ ምክንያት እየተርገፈገፉና እየተወዛወዙ ነበር፡፡ በዚህ በጨለማው ሁኔታ ድንገት ብልጭ ያለው ብርሃን መገለፅ የማይቻል ትልቅ ሁኔታ ነበረው፡፡

ውሀው አግራችን መንካት ጀመረ፤ አለቱ ላይ አሰቀምጠን የነበረውን ጓዛችንም ይዞት ሄደ፡፡ እንሰሶቹ ደግሞ መቁነጥነጥና በሚያሳዝን ሁኔታ ድምፅ ማሰማት ጀመሩ፤ ከብት ጠባቂዎቹም ቢሆን ባልተለመድ ከፍ ባለ ድምፅ ፀሎት ጀመሩ፤ እኔም ተሰፋ ቆረጥኩ፡፡ በርግጠኛነት የተሰማኝ ሰሜት ቢኖር በጥቂት ሰከንዶች ውሰጥ በዚህ እየጨመረ በሄደው ውሀ ውሰጥ ለሕይወታችን ሰንታገል ነው፡፡ ግን፣ ድንገት ዝናቡ ቆመ፡፡ የነበረው ጭጋግ ደግሞ ተመልሶ ለመጣው ፀሀይ ብርሃን ቦታውን በመልቀቅ ሟሸሸ፡፡ የቃል ኪዳን ቀሰተ ደመና አንድ ጎን በአድማሱ በከል መታየት ጀመረ፡፡ ተርፈናል!

በጥቂት ደቂቃዎች ውሰጥ ሲወርድ የነበረው ፏፏቴ ሀይሉ ቀንሶ ወደ ደካማ ወራጅ ውሃ ተቀይሮ ትንሽ ቆይቶ ጭራሹን አቆመ፡፡ በአሰር ደቂቃዎች ውሰጥ ደግሞ የውሀው ጥልቀት በሁለት ኢንቾች ቀነሰ፡፡

ከቀኑ አሰራ አንድ ሰአት ሲሆን፣ ከዚህ በፊት ወንዝ ይወርድባቸው የነበሩ ቦታዎች ትንንሽ ጨረቅረቅ የሚሉ ውሀዎች ሆነው ነው የሚታዩት፡፡

ነገር ግን ከዚህ ካለንበት የአለት ከፍታችን እንዴት ብለን ነው የምንወርደው? ቦታው ከውሃው በላይ አራት ጫማ ከፍ ይላል፡፡ እኔም፣ አምሰት የጭነት ከብቶችና የምጋልበው ፈረስ፣ ከሁሉም ጓዜ ጋር ዙሪያውን የስምንት ጫማዎች ጥልቀት ባለው ውሀ በተከበበ ደሴት መሀሉ ላይ ነው ያለሁት፡፡ የረጠበው ልብሳችን እንደለበለን በብርድ እየተንቀጠንቀጥን በዚህ ቦታ ማደሩ በጣም እሰቸጋሪ ነገር ነው፤ ነገሮች በፍጥነት ካልተንቀሳቀሱ በሰሰት ማይሎች ርቀት መንገድ ከሚገኘው የታችኛው የሰሮ ጣቢያ ከመድረሳችን በፊት ጨለማ ይሆናል፡፡ አብዛኛውን ጓዜን ጥዬ መሄድ እንዳለብኝ ግልፅ ሰለሆነ ወዲያውኑ መጣል የምችላቸውን ለመምረጥ ሥራ ጀመርኩ፡፡ ሰለዚህ ከጨረታው በሀምሳ ሩፒዎች የገዛሁት የቴዎድሮሰ ምንጣፍ አሁን 800 ፓውንድ መመዘን ሰለጀመረ፣ ተንከባሎ አጠገብ ወዳለ ኩሬ ተጣለ፤ ያም ሲሆን ላጠፋሁት ገንዘብና እዚህ ድረሰ እሰከምደርሰ የተጓዝኩት የ350 ማይሎች መንገድ እየቆጨኝ ነበር፡፡ ከዛም የሥራተኞቹ ድንኳኖች፣ ግማሽ የሚሆነው የአልጋ ልብሳቸው ተጣለ፡፡ ከዚህም ጋር፣ ሣጥን ሙሉ ልብሰ፣ አንዳንድ ብርቅ ነገሮች፣ የአንበሳ ቆዳዎች፣ የካምፕ ጀበናዎች አብረው ተጣሉ፡፡ ለሁለት ቀን የሚሆን ምግብና ሁለት ሣጥኖች ከነዕቃቸው ቀለል እያደረግኩ

ለነበሩት የጋማ ከብቶች ለጭነት አከፋፈልኩ፡፡ ቀጥሎም የኔ የራሴ ድንኳን ነበር፣ ከሁለት ተቀዶ ምሰሶዎቹ ከተወረወሩ በኋላ ሸራውን ብቻ ማጓጓዝ ቀላል ነበር፡፡

ለኔ አሁን የቀረኝ ሥራ፣ እንስሶችን ከእለቱ ማውረድ ነበር፡፡ የእለቱ ጎኖች ቀጥ ያሉና እንደጠርሙስ ለስላሳ ስለነበሩ፣ እንስሶቹ በራሳቸው መሄድ አልቻሉም፤ እንዲሄዱ ማስገደዱም አልሰራም፡፡ ተሞክሮ ነበር፤ ነገር ግን ውጤት አልባ ነው የሆነው፡፡

ስለዚህ የነበረኝ አማራጭ ተገፍተው እየዋኙ ወደ መንገዱ እንዲሄዱ ነበር፤ መንገዱም ከኛ 15 ያርዶች ርቀት ላይ ነው፤ የመጀመሪያ ሙከራ የተደረገባት የአቢሲኒያ ፈረስ ነበረች፡፡ ውሃ ውስጥ በትልቅ መንቦጫረቅ ዘፍ አለች፤ ሆኖም በድፍረት እየዋኘች ወደ ታች ካለው ወደ ውሀው ዳርቻ በጥሩ ሁኔታ ደረሰች፡፡ የሚቀጥለው ደግሞ በቅሎ ነበር፤ የጠጠረ ጭንቅላት ነው የነበረው፤ እናም በሚያደርገው ነገር ሁሉ የበቅሎ ባህሪ ነው የሚያሳየው፡፡ እሱን ከእለቱ ገፍቶ ለማውረድ ሁሉም ሠራተኞቼ መተባበር ነበረባቸው፡፡ ሲወድቅ እግሮቹን ወደላይ ገልብጦ በከባድ ድምፅ ነበር ውሀው ውስጥ የወደቀው፤ ከዛ በኋላ ተመልሶም አልታየም፡፡ ሁሌም፣ ድርቅ ያለ ደደብነት ይኸው ነው ውጤቱ፡፡ የቀሩት ሶስት ከብቶች በደህና ሁኔታ የውሃው ዳርቻ ደረሱ፡፡ ቀጥሎ ጓዙ ላይ የመጎተቻ ገመድ ከታሠረ በኋላ ውሀው ውስጥ ተወርውሮ በሰላም ወደ ዳር ተጎተተ፡፡

መተኪያ የሌለው የኔ ረዳት አሊ፣ የአረቡ ፈረሴ ሰይድና እኔ ነበርን እለቱ ላይ የቀረነው፡፡ ስለዚህ ሰይድን ከእለቱ ማውረዱ የኔና የአሊ ሥራ ሆኖ ተገኘ፡፡ ኮርቻውን ካወረድን በኋላ፣ ልጓሙን አንገቱ ላይ አሰረን ወደ እለቱ ጠርዝ ከመራነው በኋላ ለመግፋት ሞከርን፤ ነገር ግን፣ ይህ ሥራ በሰይድ የኩራት መንፈስ የሚያዋርድ ነገር ሆኖ የተገኘው፤ ስለዚህ በኮቴውና በጥርሱ መሄድ የማይችልና የማይፈልግ መሆኑን በመግለፅ የሚደረገውን ነገር የሚቀበለው አለመሆኑን ማሳየት ጀመረ፡፡

ስለ ፈረሶች፣ በተለይም ስለ አረቢያ ፈረሶች ዕውቀት ያለው አሊ ጋር ከተማከርን በኋላ፣ ውሳኔው "የያንኪው ሳሂብ"[167] ፈረሱን እንዲጋልብ ተወሰነ፡፡ እኔ እንኳን፣ በደልዳላ ሜዳዎችና በአቢሲኒያ መንገዶች ታላቅ ፈረስ ጋላቢ ብሆንም፣ ከፈረስ ጋር ዘሎ ጥልቀት ወዳለው ውሀ መግባት ሌላ ነገር ነበረ፤ ስለዚህ በትልቅ ቅሬታ ነበር ፈረሱ ላይ የወጣሁት፡፡ መጀመሪያ ግን፣ አሊ በአረብኛ ፈረሱን ሲያሞካክሽ ኮርቻው ትክክል መሆኑን ማየት ነበረብኝ፡፡

---

[167] የአሜሪካው ጌታ ለማለት ነው

አሊ ዘሎ ውሀ ውስጥ እንዲገባና እንዲዋኝ ከጠየቅሁ በኋላ፣ በጥንቃቄ ልጓሙን በመያዝ፣ ሰይድን ወደ አለቱ ዳርቻ መራሁትና ውሀውን እንዲያሸት፣ አፍንጫውን እንዲያናፋና እንደፈለገው እንዲሆን ሰሶሰት አራት ደቂቃዎች የሚሆን ፈቀድኩለት። ከዛም ሁለት እርምጃዎች ወደኋላ ከሳብኩት በኋላ ራሴንም በኮርቻው ላይ ካስተካከልኩ በኋላ፣ ባንድ ጊዜ በሁለት ጎኖቹ በመኮልኮያዎች ኮረኮርኩት፤ ያን ጊዜም ልጓሙን በመጎተት ወደላይ ሳብኩት። በዚህ ጠንካራ ፈረስ፣ የመኮልኮያዎቹ ውጤት ፈጣን ነበር፤ ልክ እንደ ግሥላ፣ ለሰከንድ የሚሆን ካደባ በኋላ ከአለቱ ተነስቶ ወደላይ ወደአየር ዘሎ ውሀው ውስጥ ገባ። ሰይድ፣ ጆሮዎችን ካራገፈ በኋላ በከፊል እየዋኘ ወደ ውሀው ዳርቻ አመራ።

ዳርቻው ሲደርስ፣ የተደሰተው አሊ፣ ምርጡ የአረብ ፈረስ በአሸናፊነት ለመወጣቱ ክብር ሲል ሰይድን አቀፈው፤ በፈረሱ ድፍረትም ያልተጠበቀ አድናቆቱን ቢዘህም በዚያም አያለ ገለፀ።

ጓዛችን አንደገና ጠፍረን ጉዟችን ቀጠልን፤ በዚህ ጊዜ ማለፊያው እየደረቀ ነበር። ለሁለት ማይሎች፣ በትልልቅ ድንጋዮች፣ ጉድጓዶችና፣ ንጣፍ እለቶች ላይ ከታገልን በኋላ፣ ከፍተቱ ሰፍቶ ወደ ሸለቆ ተቀየረ። በጎንና በጎኑም ዳገታማ ኮረብታዎች፣ ርጥብ ገደሎች፣ ውሃ የሚያንጠባጥቡ ደኖች፣ ተለይቶ በማይታወቅና ሚለጥራዊ ሁኔታ ወደፊት ተዘርግተዋል።

በግምት፣ ከምሽቱ አንድ ሰአት ሊሆን የታችኛው ሶሮ ጣቢያ ደረሰን፤ ምሽቱ ወደ ጨለማ እየተቀየረ ነበር። የጣቢያው ሀላፊ የሆን መኮንን በማለፊያው ከነበረው አደጋ ተርፈን በመምጣታችን በጣም ተደነቀ። ጎርፉ ሀይለኛ በነበረበት ሰአት፣ የአምሰት ሰዎች አስከሬን ሲንሳፈፍ አግኝተው ስለነበር፣ የጣቢያው ሰዎች የበለጠ ጥፋት ይደርሳል ብለው ገምተው ነበር። ሁኔታውን አውርቼ ስጨርስ፣ መኮንኑ፣ "ከሚገባው በላይ ተጨንቄ ነበር።" አለ፤ "ሰውነትህን ለማሞቅ፣ መጠጥ ወይም አንድ ነገር፣ ታውቃለህ፣ ወይም አንድ ብርጭቆ ብራንዲ ዋይን እና ሶዳ ላንተ ጥሩ ነው፣ ታውቃለህ" በማለት ጋበዘ።

የአንግዳ ተቀባዩን መኮንን የመጠጥ ግብዣ ከብዙ ምስጋና ጋር ነው የተቀበልኩት፤ ነገር ግን መጀመሪያ ድንኳናችን መወጠር ነበርብን፤ ከዛም የደመቀ እሳት አንድደን ጥሩ ራት በመብላት ሰውነታችን መልሰን፣ ትኩስ ቡና ጠጥተን፣ የጋያ ትምባሆ ለኩሰን፣ በግድግዳ ስለታጠረው ማለፊያ፣ ስለ አደገኛው ጎርፍ፣ እና ስለ አሰቃቂ የታላቁ ሶሮ አደጋዎች በመዝናናት ካወራንና ከሳቅን በኋላ ነበር።

በሚንበገበገው አሳት ሙቀት ካገኘን በኋላ፤ ትኩስ መጠጥ በመጠጣት ከሚመጣው ቁርጥማት ራሳችን ከተከላከልን በኋላ፤ አንድ ላይ ቁጭ ብለን በተሰባበረ እንግሊዝኛ ማውራት ጀመርን፡፡ ምክንያቱም ሠራተኞቼ ጥሩ ነገር በሥሩ ቁጥር ወዳጅነት ስለማበዛም ነበር፡፡ በደበዘዘው የአለቶቹ ጥላ ስር ሆነን ለስሕታት አወራን፤ ያም ሳናውቀው ወደ እንቅልፍ አለም ተሻግረን፣ መንገድ የለሽ በሆነው የእንቅልፍ በረሀ ድብን ብለን እስከንተኛ ድረስ ነበር፡፡

በሚቀጥለው ቀን፣ ከንጋቱ አስር ሰአት ሲሆን ወደ ቁማይሌ መንገድ ጀምረናል፤ ከአንድ ሰአት በኋላ ከሶሮ ማለፊያ መውጫ ካምፕ ደረስን፡፡

ቁርስ በልተን፣ ቁማይሌን አልፈን ሄድን፡፡ ሙሉ ቀን ሲሆን፣ በግራና በቀኛችን በተንጣለለውና ፊት ለፊታችን ለአስራ ሁለት ማይሎች በተዘረጋው ግለታም የዙላ ሜዳ ብቅ አልን፡፡ እንደ በረዶ ከሚነጣው ጊዜያዊ የወታደሮች ካምፕ ባሻገር የቀይ ባህር ሰማያዊ ውሃ ያብረቀርቃል፤ በላዩም በሚያለገርም አስላለፍ የባህር ጥልቅ እንስሳዎች ሲጋልቡ ይታያል፡፡

እኩለ ቀን ሲሆን ሁላችንም ዙላ ደረስን፤ ወደፊት የምናገኘውን ዕረፍት በማሰብ ከልባችን ደስተኛ ነበርን፡፡

ዙላ፣ በመጀመሪያ ሳርፍ ከነበረው የተወሳሰበ፣ ግርግርና ጩኸት ስፍኖበት ከነበረበት ሁኔታ ይለያል፡፡ ትልልቅ መካዝኖች ተሠርተዋል፣ በወስጣቸውም በቶኖች የሚቆጠሩ በጥንቃቄ የታቀደ ዘመቻ የሚያስፈልገው ነገሮች በሙሉ ተደርደረዋል፡፡ የገበያ ቦታዎች በብዛት ነበሩ፤ ግማሽ ምግብ ቤትና በግማሽ መጠጥ ቤት የሆኑ፣ በቅጽል ሰም "የአነስሊ አዳራሽ" ተብለው የሚጠሩ ቦታዎች እስከ 120 ዲግሪ ፋራናይት በሚደርሰው ሙቀት ለሚሰቃዩ መኮንኖች ማስተናገጃዎች ተሠርተዋል፡፡ በውስጣቸውም መጠጠ የያዙ የእንጨት በርሜሎች፣ ሶዳ ውሀ፣ ብራንዲ ዋይን እናም ከፈገግታ ጋር ሰውነት የሚያዝናኑ መጠጦች ነበሩ፡፡ ሁሉም ሆስፒታሎች ወደ ቁማይሌ ተወስደዋል፤ ቦታውም በደጋው በሰናፌና በባህሩ መካከል ስለሆነ ለህክምና ጥሩ ቦታ ነበር፡፡

ከምሽቱ 12 ሰአት ሲሆን፣ የጭነት ከብቶቼን በቅናሽ ዋጋ ሸጥኩኝ፤ ሠረተኞቼንም አሰናበትኩ፤ አሊንና ሰይድ የሚባለው የአረብ ፈረሴ ኢንዶር በተባለች መርከብ ውሥጥ መሳፈራቸውን አረጋገጥኩ፡፡ *(ሰይድ የአረብ ፈረሴ ወደ ኒው ዮርክ በመርከብ ተልኮ፣ ከአቢሲኒያው ችግር ተርፎ የክብር ኗሪ በመሆን በሚመች ጋጣ በምቾት ይኖራል)* መርከቧ፣ በጠዋቱ፣ ኮሎኔል ሚልዋርድንና የሮያል መድፈኛውን ቡድን በመያዝ ወደ ሱዊዝ ካናል ልትሄድ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች፣ የዘገየውን የጄኔራል ናፒየር ሪፖርትና የአፄ ቴዎድሮስን አራት ዘውዶች ለእንግሊዝ ንግሥት እንዲያደርሱ የተመረጡ ነበሩ፡፡

የኮሚሳሪያቱ የጋራ ጓደኞቻችንና ካፒቴን ደውስ፣ ለሚመለሱት የከሩሴድ ተዋጊዎች ያልተጠበቀ ድግስ አዘጋጅተዋል፡፡ ከመሳፈሬ በፊት፣ በመሀከላችን በጓደኝነት መንፈስ እንድንቀጥል ርስ በራሳችን ቃል ገብተናል፤ ቃለ መሀላውን የገባነው የመጨረሻውን የመጠጥ በርሜል እውርደን እየጠጣን ነበር፤ በህይወት እስካለን ድረስ ደብደቤ እንድንፃፃፍ ነበር፡፡ ከዛ በኋላ ደግሞ ለሜት የሚነካ መለያየት ነበር፤ ታምናላችሁ? ከበሩ አሰር ያርዶች ርቀት ከመሄዴ በፊት፣ እንደገና ተመልሼ ለመልካም መንገድ እንድ መጠጣት ነበረብኝ፤ እናም ሆነና፣ ሁላችንም የመጨረሻ ደህና ሁኑ ስንብት ተነፈስን፡፡

በሚቀጥለው ቀን ሲነጋ፣ ኢንዶር የተባለችዋ መርከብ ጉዞ ጀመረች፡፡ ፀሀይዋም በምስራቁ አድማስ በኩል በመነሳት፣ በላያችንና በዙሪያችን ያለውን ደመና፣ ደመቅ ያለ ቀይ ቀለም እየቀባች በመንገዳችን ላይ ታጅበን ነበር፡፡ ዝቅተኛው የእነስሲ ወሽመጥ እሸዋማ ቦታ፣ ሰፊው የዙላ ካምፕ እና ኩሩዎቹ የእንግሊዘ መርከቦች ወደኃላ እየራቁን ሄደው በመጨረሻም ከዕይታ ተሠወሩ፡፡ ነገር ግን፣ የሰናፌና የሶሮ ሸለቆዎች በውስጣቸው የሚሄዱባቸው ትልልቆቹ ወይም ከፍታ ያላቸው የሃዳስ እና የእዞርታ ተራራ ሰንሰለቶች፣ ከዕይታችን የተሠወሩት ከሶስት ሰአታት በኋላ ነበር፡፡ ሲሰወሩም ተለይተው በማይታዩበት ሁኔታ ከኑቢያ ተራራ ሰንሰለቶች ጋር በመደባለቅ ነበር፡፡

ጦሩ በሰላም ቁማይሌ ደረሰ፣ በሰኔ ፲፣ በባቡር ወደ ዙላ መጣ፡፡ በጉርፉ ባጠቃላይ ፲ ሰዎች አጥቷል፡፡ ከሰምንት ቀን በኋላ የተለያዩት ሬጅመንቶች ወደየ መድረሻ ቦታቸው ወደ ሱዌዝና ወደ ቦምቤይ መንገድ ጀመሩ፡፡

ከአንድ ወር በኋላ፣ በአቢሲኒያ የነበረው ያ ትልቅ ካምፕ እከተመ፡፡ የማጓጓዣ መርከቦችም ከአቢሲኒያ ባህር ለዘላለም ለመለየት ከንፋቸው ዘረጉ፡፡ ስለዚህ ይህ ዘመናዊ የከሩሴድ ዘመቻ፣ ከሌሎች ካለፉ ሁኔታዎች፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር ለመታወስ፣ በሁሉም ስፍራ እናም በተሳካ ሁኔታ ከተጨረሱ ዘመቻዎች ጋር በቁጥር የሚጨመር ሆነ፡፡

ፍፃሜ

# የምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች

*__ቁጥር 161፤__ አቴጌ ጥሩ ወርቅ ስለ ልዑል አለማየሁ ስትጠየቅ፤ የሰጠችው ቃል፣ አባቱ እንደተመኙለት ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሄድ ነበር፡፡ ሌላ የጨመረችው ነገር ቢኖር፣ ልዑሉ የአማርኛ ቋንቋ እንዳይረሳ፣ አለቃ ዘነብ በአስተማሪነት አብረው እንዲሄዱ ጠይቃ ነበር፡፡ ሆኖም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ አለቃ ዘነብ ከመንገድ ተሰናብተዋል፤ ምክንያቱ ግን አልታወቀም፡፡ እኚህ አለቃ ዘነብ፣ የቴዎድሮስ ታሪክ በሚል ፅሁፍ የተውልን ሰው ሳይሆኑ አይቀርም፡፡ አፄ ቴዎድሮስ፣ አለማየሁ ብቻ ሳይሆን ትልቁ ልጃቸው መሸሻም እንግሊዝ አገር እንዲሄድ ምኞታቸው ነበር፡፡ መሸሻ ግን መቅደላን እንደለቀቀ ወደ አብሮ አደጉ ወደ ምኒልክ ወደ ሸዋ ነው የሄደው፡፡ ቴዎድሮስ፣ በመቅደላ፣ አለማየሁን አስጠርተው ከራሳም ጋር በደንብ እንዲተዋወቅ ማድረጋቸው ተዘግቧል፡፡ ለራሳም አደራ መስጠታቸው ነበር፡፡ ራሳም ሲገልፅ፣ ትንሹ ልጅ የተደገፍኩትን ትራስ ሳመ ይላል፡፡ ቴዎድሮስ ከነበሯቸው ስድስት ልጆች፣ ሁለቱ ወደ በጌምድር ሲሄዱ፣ ከሌላ አሮሞ ሴት የተወለደው ሀይሉ የሚባለው ከእናቱ ጋር ወደ የጁ ሄዷል፡፡ የምኒልክ ሚስት የነበረችው አልጣሽ ደግሞ ለትግሬው ባላባት ለደጃች ባርያው ጳውሎስ ተድራ ነበር፡፡*

*__ቁጥር 162፤__ ልዑል አለማየሁ በእንግሊዝ አገር ሲኖር፣ የእናቱ እናት፣ የደጃች ውቤ ሚስት፣ አያቱ የፃፉለትን ደብዳቤ መመልከት በዚያን ጊዜ፣ አፄ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም በህዝቡ ላይ የነበራቸውን አመለካከት ያስረዳል፡፡ በዚህ ደብዳቤ ላይ፣ እናትየዋ አቴጌዋን ጥሩነሽ ሲሉ ይታያል፡፡ ፀሐፊዎችም ሁለቱን ስም፣ ጥሩነሽንና ጥሩ ወርቅን ሲጠቀሙ ይታያል፡፡ አቴጌዋ ስሟ ጥሩነሽ ሲሆን፣ አፄ ቴዎድሮስ ናቸው ጥሩ ወርቅ የሚለውን መጠሪያ የሰጧት፡፡*

*ደብዳቤው እንደሚከተለው ነው፡፡*

*ይህ፡ ቃል፡ ይድረስ፡ ከደጃዝማች አለማየሁ፡፡*
*የተላከ፡ ከወይዘሮ፡ ላቃየ፡ ከቴየ፤ ጥሩነሽ እናት፡*
*እኔም፡ ያለሁ፡ ከናትህ፡ አገር፡ ከዳጃዝማች፡ ውቤ፡ ደብር፡ ነው፡፡*
*ልጄ፡ ወዳጄ፡ አጅጉን፡ እንዴት፡ አለህ፡*
*ከተለያየን፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡*
*ምነው፡ ወረቀት፡ አትሰደልኝ፡ በኃዘን፡ በልቅሶ፡ ሰምት፡*
*ካላንተ፡ በቀር፡ ሊላ፡ ልጅ፡ ሊላ፡ ተስፋ፡ የለኝም፡፡*

*አሁንም፡ ተሎ፡ ወረቀት፡ ሰደድልኝ*
*መልክህን፡ በሥዕል፡ አድርገህ፡ ዘወትር እንዳየው፡፡*
*ክርስቶስ፡ ስመገናኘት፡ ያብቃን፡ አሜን፡፡*

*ከንግሊዚቱ፡ ንግሥት፡ ከማስኮብ፡ ንጉሥ፡ ከፈረንሳዊ፡ ንጉሥ፡*
*ከነገሥታቱ፡ ሁሉ፡ ወዳጅ፡ ሁን፡ ወረቀት፡ ላክ፡*
*የሀበሻ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ እንተን፡ ይጠብቃል፡ ይመኛል፡ ብልህ፡ ሁን፡*
*ለሀበሻ፡ ሰው፡ ዓይን፡ አውጣለት፡ ዕውር፡ ሁኗል፡*
*ጥበብ፡ አውጣለት፡ እንዲህ፡ ዕውር፡ እንደሆነ፡ ኢይቅር፡፡*

*በዘመነ፡ ዮሐንስ፡ በጥር...ቀን፡ ተጻፈ*

***ቁጥር 163፡*** *የአቴጌ ጥሩ ወርቅ ሁለት ወንድሞች በመቅደላ በእስራት ይኖሩ ነበር፤ ከተለቀቁ በኋላ ራሳቸው ወደ አገራቸው መመለስ ሲፈልጉ አቴጌዋን ማስተዳደር እንደማይችሉ፣ ልዑሉን ደግሞ፣ ለመንገስ ያሰበ ሰው ይገለዋል በማለት እናትና ልጁ ከእንግሊዞቹ ጋር እንዲሄዱ ተስማምተው ነው የተለያዩት፡፡*

# ዋቢ መፃሕፍት
(ለግርጌ ማስታወሻዎች)


1. Record of the Expedition to Abyssinia
2. Narrative of A Journey Through Abyssinia In 1862-3 (Henry Dufton)
3. Narrative of 8ritish Mission to Theodor, King of Abyssinia, Hormuzd Rassam
4. የቴዎድሮስ ታሪክ፣ በደብተራ ዘነብ፣ በዶክተር ኢኖ ሊትማን አሳታሚነት፣ በርሊን፣ 1902 ዓም
5. The 8arefoot Emperor (Philip Marsden)
6. The Prince Who Walked with Lions (Eliabeth Liard)
7. አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት በተክለፃድቅ መኩሪያ
8. አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት በተክለፃድቅ መኩሪያ
9. አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት በተክለፃድቅ መኩሪያ
10. አጤ ቴዎድሮስ ከጳውሎስ ኞኞ
11. የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983፣ ባህሩ ዘውዴ
12. Dairy of a Journey to Abyssinia, 1868, With the expedition under Sir Robert Napier
13. A History of of The Abyssinian Expedition Clements R. Markham
14. http://www.royalark.net/Ethiopia/tewodros.htm Christopher buyers
15. The 8ritish expedition to Abyssinia Henry Montague Hozier, January 1, 1869
16. The Abyssinian Expedition (Roger Acton) with engravings from illustrated London News

# መቅደላ!

መቅደላ
አንቺ ሰው በላ
ደግሞ እንደ ገደልሽ
እንደ አቀበቱ፣ እንደ ዳገትሽ
ወደላይ እንደሚወጣው
የበላሽው ሽቅብ ቢልሽ ምነው?

አንቺን አምኖ፣ እንቺን ብሎ
መንገዱን ጠርጎ ቢመጣልሽ
ምነው በንዴት መቃጠልሽ።

የተበተነውን በየሥፍራው
ሰፍቶ ላሰበሰ ሰው
ምን ብትሰለቺ ነው
መከለያ የነሳሽው።

አንቺን ያመኑማ፣ አንቺን የወደዱ
አንለይም ብለው፣ በሮኬት ነጎዱ።
አልቆርጥሰት ያለው፣ ካንቺ መለየቱ
አንድ ወዳጅ ቢኖርሽ፣ የነበረ ብርቱ
ካንቺው ጋር አደረ በገዛ ብረቱ።

ደግሞ እንደ ሰውየው ከፍ ብለሽ
እትታይም ብለው በሳት አደመቁሽ።

መቅደላ! አንቺ ንቁግ፣ አንቺ ስስታም
ለብቻሽ ለትወሰጅ፣ ህፍረት የለሽም
መሬትም እንደሰው፣ ለካስ ይቀናል
የወደደውን ሰው፣ ይዞ ያስቀራል።

በዚህ እንኳን ላመሰግንሽ
አሳልፈሽ ባለመስጠትሽ።

ገበየሁ ተፈሪ


# መዝጊያ

ይኸው እንግዲህ ባንድ ሰው እድሜ፣ ለዘመናት የነበረች ሀገር፣ ብዙ ፈተና የተመላበት ታሪክ አስመዘገበች። ታሪኩ፣ የንጉሡ የቴዎድሮስ፣ አነሳስና ፍፃሜ ቢሆንም፤ በጥሞና ለመረመረው ሰው፣ ታሪኩ በርግጥ የህዝቡ ነው። ህዝቡ በተለያዩ ገፅታው፣ በተለያየ ጊዜ፣ የሚጠበቅና የማይጠበቅ ሥራዎችን ሠራ። እንደ ንጉሡ አርቆ አለማሰቡም ግልፅ ነበር። ባላባቶችና መሳፍንቶችን፣ ልጓም ያልነበረው ሥልጣን ሠጥቶ በላዩ ላይ እንዳልተፈጠረ አድርገው ኖሩበት። ካሳን አስነስቶ፣ ቴዎድሮስ ብሎ አሰይሞ ታሪክ ሠራ። ተመልሶም ለቴዎድሮስ ያላቢቃው ይመስልና፣ በየጎጡና በየግዛቱ የነበረው የባላባት ኑሮ የናፈቀው ይመስል፤ አገር ማለት፣ እሱን በቅርቡ የሚመስሉ ዘመዶቹና ያደገበት ቀዬ ብቻ የመሰለው የሚመስለው ህዝብ፣ በጠባብ ጎዳና በመጨናነቅ ለሰውዬው ፍፃሜ ምክንያት ሆነ። ሊቀይሩት ያሰቡትን ንጉሥ በተገላቢጦሽ የቀየረ ህዝብ ነው።


እፄ ቴዎድሮስ ህዝቡን ያዩበትን አይን የበለጠ በመረዳት፣ ዋናው ጥያቄ መቅረብ ያለበት ለህዝቡ ነው። ለደግም ሆነ ለክፉ የሚንቀሳቀስ ሀይል ሁልጊዜም ቢሆን ጭፍራ አለው። ጭፍራ ደግሞ ከህዝብ ነው። ህዝብ ያነሳል፣ ህዝብ ይጥላል። እንደ ቴዎድሮስ ጊዜ ሁሉ፣ እርቆ ማሰብ ካልተቻለ ድካሙ ብዙ ነው። ሌላው ጥያቄ፣ በህዝብ ደረጃ፣ እኛ ሰለኛ ከሚገባው በላይ ራሳችን ከፍ አድርገን እያየን ይሆን? ከሆነ ደግሞ፣ አደጋው ይጨምራል እንጂ አያንሰም።

የማይነቃነቅ ሀይል የነበራቸው የሚመስሉ ብዙ ሀያላን ስርወ መንግስታት፣ ጠንካራ የነበሩ ህዝቦች፣ ታላቅ የሚባሉ ሀገሮች መጥተው ሄደዋል። አሁን ያለንበት አለም፣ ለጊዜው ዘመናዊና ሰላማዊ ቢመስልም፣ ሰው በመሠረታዊ የተፈጥሮ ባህሪው ለራሱ ብቻ ማሰቡ አንግዳ አይሆንም። ሰለዚህ በረቀቀ መንገድ ቀለብና ንብረት ለራሱና ለወገኖቹ ለማሰብሰብ በየክፍለ አለሙ የተበተነው ሀይል፣ የጎደለ ለት፣ ያከማቸውን ነፍጥ ይዞ ደከም ያለውን ላለማጥቃቱ ዋሰትና የለም። ይህ እንኳ ለኢትዮጵያ እንግዳ አይሆንም። በአጭሩ፣ ደከመን ከተገኘን በራሳችን ውህም እናልቃለን። አሁን ከንፈር የሚመጥልን ከሌለ፣ ከዚህ በፊትም ካልነበረ፣ ወደፊትም አይኖርም። እንደ ሀገር ለመኖር አማራጩ ግልፅ ነው። ሰብሰብና ጠንክር ማለት ነው። ሰብሰብ ማለትና መጠንከር ደግሞ የቴዎድሮስ ነበር።

አሜን
ገበየሁ ተፈሪ



ከዙላ እስከ መቅደላ ከእንግሊዝ ጦር ጋር የተጓዘ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ የዘገበው ታሪክ፡፡
በአፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዋ ሰአት በቦታው የነበረ የአይን ምስክር፡፡
አንድ ጊዜ ተወዳጅ ሀይለኛና ገናና የነበሩትን ንጉሥ የመጨረሻ ምዕራፍ ግልፅና ጥልቅ
በሆነ ሁኔታ ያቀርባል፡፡
ከመቅደላ በፊት የነበሩ ሁኔታዎችን ያስገነዝባል፡፡
መቅደላ እንደዚህ በዝርዝር ቀርቦ አያውቅም፡፡
ስለ አፄ ቴዎድሮስ መነበብ የሚገባው ፅሁፍ፡፡



ISBN 978-0-692-92203-3 $20.00
52000>
9 780692 922033